ገ
ፅ
1




# ለቅዱስ ቁርባን እንድበቃ ምን ላድርግ?

«ጽዋንም አንሥቶ፣ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ፡ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለብዙዎች ኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው»
ማቴ. 26፡27

በዲያቆን የሺጥላ ሞገስ
2011 ዓ.ም.

መብቱ በሕግ የጠበቀ ነው
All Right Reserved

ያለ አዘጋጁ ፈቃድ በሙሉም ሆነ በከፊል
መልሶ ማሳተም በሕግ ያስጠይቃል

## የመጽሐፉ ስጦታ

ከ____________________

ለ____________________

_______ ቀን 20 ___ የተሠጠ

ፊርማ____________________

አስተያየትዎን ሊለግሱኝ ፈቃደኛ ከሆኑ
በዚህ አድራሻ ያገኙኛል

ዲያቆን የሺጥላ ሞገስ
ሞባይል 0911 64 47 81
0922 87 04 47
ፖስታ 120434
E-mail:yesh_mo@yahoo.com

## መታሰቢያነቱ

ለብዙ ክርስቲያኖች በጾምና ጸሎት ከእግዚአብሔር ጋር መገናኛ ለሆነውና የእግዚአብሔር ድንቅ ሥራ በእመቤታችን ድንግል ማርያም ቃልኪዳንና አማላጅነት እየተገለጠ ለሚታይበት ለታላቋ «የጻድቃኔ ማርያም ገዳም» እና በታላቅ ሐዋርያዊ ተልዕኮ ላይ ሳሉ እረፍተ ሥጋ ሩጫቸውን ለገታባቸው «ለብፁዓን ሊቃነ ጳጳሳት» አባቶቼና እንዲሁም ለእውነተኛይቱ የወንጌል አገልግሎት ለሚደክሙ ቤተ ክርስቲያን ላፈራቻቸው «ሰባኪያነ ወንጌልና ዘማሪያን» በተጨማሪም ለአደኩበት «ለደብረ ናዝሬት ቅዱስ ዮሴፍ ቤተ ክርስቲያን» ትሁንልኝ።

## ምስጋና

በመጀመሪያ ደረጃ ይህን ሁለተኛ መጽሐፍ ለማጠናቀቅ ደካማ ልጁን ለረዳኝና መንገዴንም ሁሉ ላቀናልኝ ምስጋና የባሕሪይ ገንዘብ ለሆነ በመከራዬ ሁሉ የረዳኝ የቅዱሳን አምላክ ልዑል እግዚአብሔር አምላክ የተመሰገነ ይሁን።

በዚህ መጽሐፍ ዝግጅቴ በማንኛውም መልኩ በሚያስፈልጉኝ ነገሮች ለረዳችሁኝ ሁሉ፣ እንዲሁም ለማኅበረ ቅዱሳን ንዋየ ቅድሳት መሸጫ ክፍል እና የኮምፒዩተር ለቀማ ሥራ ላከናወነችልኝ ለወ/ሮ ሠናይት መላኩ የአባቶቻችን አምላክ የሠራዊት ጌታ ልዑል እግዚአብሔር ዋጋችሁን ይክፈልልኝ እያልኩ ምስጋናዬን አቀርባለሁ።

ዲያቆን የሺጥላ ሞገስ

ይህ መጽሐፍ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ሥርዓት መሠረት ተዘጋጅቶ ታተመ

## ማውጫ

መግቢያ

ገጽ

ምዕራፍ አንድ ____ 1
ምስጢረ ቁርባን ____ 1-2
❖ የሥርዓቱ አጀማመር ____ 2-3
ምዕራፍ ሁለት ____ 4
ምሣሌና ትንቢት ____ 4
❖ የምሣሌያት ዓይነቶች ____ 4-5
❖ የትንቢት ፍጻሜ ____ 5-6
ምዕራፍ ሦስት ____ 7
የምስጢረ ቁርባን መገኛ ድንግል ማርያም ናት ____ 7-10
❖ ቅዱስ ቁርባን ምስጢር የመባሉ ምክንያት 11-12
ምዕራፍ አራት ____ 13
ቅዱስ ቁርባን ስለፈለጉ ብቻ የሚገቡበት
ሕይወት አይደለም ____ 13
❖ ምክረ ካህን ____ 13-15
❖ ሰው ግን ራሱን ይፈትን ____ 15-17
ምዕራፍ አምስት ____ 18
ቅዱስ ቁርባን ለማን? ____ 18-20
❖ ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል የተወሰነ
እድሜ አለን? ____ 20-21
❖ ቅዱስ ቁርባን መቀበል የማይገባቸው
እነማን ናቸው? ____ 22-24
❖ ባልና ሚስት ተለያይተው ቢቆርቡስ? ____ 24-27
❖ ያላገባ ወጣት መቁረብ ይችላልን? ____ 27
❖ ቆራቢ የሆነ ሰው የትዳር ጓደኛውን በሞት
ቢያጣ ደግሞ ሌላ ማግባት ይችላል? ____ 28-29
❖ ሕጻናትን ማቁረብ ____ 29-31
ምዕራፍ ስድስት ____ 32
ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል የሚደረግ ዝግጅት ____ 32-33

ገፅ 3


❖ ከመቁረብ በፊት ---------- 33-35
❖ በመቁረብ ጊዜ ---------- 35
❖ ከመቁረብ በኋላ ---------- 35-37

ምዕራፍ ሰባት ---------- 38

ከቅዱስ ቁርባን የሚያርቁ ---------- 38
❖ ስለ እምነት ምንነት አለመረዳት ---------- 38
❖ እምነት ምንድን ነው? ---------- 38-45
❖ ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም ---------- 46-54

ምዕራፍ ስምንት ---------- 55

ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው ---------- 55-58
❖ በእምነት መዛል ---------- 58-62
❖ እምነትን ማሳዳግ ---------- 62-64
❖ መናፍስትን የሚገዛ የእምነት ኃይል ---------- 65-66
❖ የዲያቢሎስ ሽንገላ ---------- 66-69

ምዕራፍ ዘጠኝ ---------- 70

ባርነት ወይስ ነፃነት ---------- 70-72
❖ ጥሪውን መስማት ---------- 73
❖ ወደ እርሱ መመለስ ---------- 74-75
❖ የሕይወት ጎዳና ---------- 75-77
❖ አውጣ ---------- 77-79
❖ ተከተለኝ ---------- 79-81
❖ አልለቅህም ---------- 81-84
❖ ሽሽተህ አምልጥ ---------- 84-86

ምዕራፍ አስር ---------- 86

ንጹህ ያልሆነ ቢኖር አይቅረብ ---------- 86-87
❖ ሳይገባው ማለቱ ምን ማለቱ ነው? ---------- 88
❖ ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት ---------- 88-89

ምዕራፍ አስራአንድ ---------- 89

የተማሟቱ አባባሎችና የመንደር ወሬ ---------- 89-90
❖ የታመመን ሰው ቢያቆርቡት ቶሎ ይሞታል ---------- 90-92
❖ የቆረበ ሰው ብቻውን ቢሆን ሰይጣን ያገኘዋል ---------- 94
❖ ያላገባ ሰው መቁረብ አይገባውም ---------- 94-96
❖ ነፍሰ ጡር ሴት መቁረብ አይገባትም ---------- 96-97
❖ ጋብቻቸውን በሥርዓተ ተክሊል ያልፈጸሙ ሰዎች መቁረብ አይችሉም ---------- 97-98
❖ ፍቅረኛሽ እንዳይክድሽ ተያይዛችሁ ቁረቡ ---------- 98-101

ምዕራፍ አስራሁለት ---------- 102

ቅዱስ ቁርባንን እንደ ጉጂ መቁጠርና ሸሽቶ መኖር ---------- 102-103
❖ ትዕግሥቱን መናቅ ነው ---------- 103
❖ ቸርነቱን አለመታመን ነው ---------- 103-105
❖ ፍቅሩን አለመረዳት ነው ---------- 105-106
❖ መድኃኒትነቱን አለማወቅ ነው ---------- 106

ምዕራፍ አስራሦስት ---------- 107

የቅዱስ ቁርባን ጥቅም ---------- 107
❖ ዘላለማዊ ድህነት እንቀበልበታለን ---------- 107
❖ ኃጢአታችን ይሰረይበታል ---------- 108-109
❖ ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ይኖረናል ---------- 109
❖ ኃይል መንፈሳዊ እንቀበልበታለን ---------- 109-110
❖ ክርስቲያኖችን ሁሉ እንደ አንድ አካል ያደርገናል---------- 110-112
❖ በሥጋ ወደሙ እንማጸንበታለን ---------- 112-115

ምዕራፍ አስራአራት ---------- 116

የቅዱስ ቁርባን ስጦታ በኛ ላይ ያለው የፍቅሩ ማረጋገጫ ነው ---------- 116-119
❖ በሥጋ ወደሙ ተወስነው ለሚኖሩ ---------- 119-120
❖ በሥጋ ወደሙ ለመወሰን ለተነሣሱ ---------- 120-121
❖ ከሥጋ ወደሙ ርቀው ለሚኖሩ ---------- 121-123
❖ ቅዱስ ቁርባን የምንቀበልባቸው ዕለታት ---------- 123
❖ ቅዱስ ቁርባን ከመቀበላችን በፊት የሚጸለይ ጸሎት ---------- 123-124
❖ ዋቢ መጽሐፎች ---------- 125


## መግቢያ

«ጊዜው ሲደርስ ሁሉ በእርሱ ፈቃድ ሆነ» በማለት ቅዱሳን መጽሐፍት እንደሚመሰክሩት እኔም ሁሉን በእርሱ ፈቃድ ጀመርኩ:: በዚህም ምክንያት በቅዱስ ቁርባን ዙሪያ ለመጻሕፍ ለረጅም ዓመታት በውስጤ ይመላለስ የነበረው ሐሳቤ ተወለደ::

ቅዱስ ቁርባንን በተመለከተ በብዙዎች መካከል የሚመላለሰውን ልዩ ልዩ ሐሳብ ወደ አንድ ለማምጣትና የቤተክርስቲያኗን ሕግ ሥርዓትና ትውፊት በጠበቀ መልኩ ቅዱስ ወንጌል የሚመሰክረውን እውነታ ለአማኙ ለመግለጥ የአብዛኛውን ክርስቲያን ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ተረድቼና በተለያዩ ጊዜያቶች በልዩ ልዩ አብያተ ክርስቲያናት አውደ ምሕረት ላይ ሳገለግል በዚህ ርዕስ ዙሪያ በምሰጠው ትምህርት የሕዝብን ስሜት ስለተገነዘብኩ ሰፊ ጊዜዬን በመሠዋት የእግዚአብሔርን ቸርነት ተደግፌ መጽሐፉን ለማዘጋጀት ጥረቴን ቀጠልኩ::

እግዚአብሔር ሕዝብ በተሳሳተ እውቀትና በተራም ወሬ እንዲጠፋ አይፈልግም! ስለዚህም ነገር መጽሐፍ ቅዱስ ብዙ እውነቶችን ይነግረናል:: ነቢዩ ሚልክያስ እንዲህ ይለናል «እግዚአብሔር እንደ ድሮው ዘመንና እንደ ቀደሙት አመታት በይሁዳና በኢየሩሳሌም ቁርባን ደስ ይለዋል» /ሚል. 3፥4/ ዛሬ ደግሞ ያለጥርጥር እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው ሕዝብ ከተራ ወሬ ርቆ ወደ አማናዊው ቁርባን ወደ ልጁ ወደ ክርስቶስ ኢየሱስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም መቅረብ ነው::

ይህ ደግሞ ቅዱስ ጳውሎስ እንደጻፈው በጌታችን በኢየሱስ ክርስቶስ አምኖ በሃይማኖት እስከ መጨረሻው መጽናቱ ነው «እንግዲህ ጌታችን ክርስቶስ ኢየሱስ እንደተቀበላችሁት በእርሱ ተመላለሱ ሥር ሰዳችሁ በእርሱ ታንጹ እንደ ተማራችሁም በሃይማኖት ጽኑ ምስጋናም ይብዛላችሁ» /ቆላ. 2፥7/ ተብለናል::

ገ
ፅ
4

ሃይማኖት ደግሞ እግዚአብሔርን አውቀን በእውነት የምናመልክበት ነው። ሐዋርያው እንደተናገረው በክርስቶስ አምነን ለመመላለስና ሥር ሰደን በእርሱ ለመታነጽ እኛ በእርሱ እርሱም በእኛ ሊኖር ይገባዋል። ይህን ነገር ጌታችን ሲያረጋግጥ «ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ» /ዮሐ. 6፥56/ በማለት ተናግሯል።

ስለዚህ «ያላመነ ያልተጠመቀ አይድንም» የሚለው ቃል የዘላለም ድህነት መሠረት እንደሆነ ሁሉ «ሥጋዬን ያልበላ ደሜን ያልጠጣ የዘላለም ሕይወት የለውም» የሚለው ከድህነት ጋር የተያያዘ ትዕዛዝ ስለሆነ ይህንን የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቃል በየትኛውም መልኩ ለድርድር አናቀርበውም።

እኔም ለብዙ ክርስቲያኖች የዕለት ተዕለት የሕይወት እንጀራና መመሪያ ይሆናል ብዬ በማመን በተጨማሪም ለካህናት መምከሪያ ለምዕመናን መመከሪያ አስተዋፅኦ እንደሚያደርግ በመረዳት «ቅዱስ ቁርባን የተቀበሉትን፣ ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል የሚያስቡትን፣ ከቅዱስ ቁርባን ርቀው የሚኖሩትን» ባካተተ መልኩ ሁሉም ማወቅና ማድረግ ያለባቸውን በከፊሉ በዚህ መጽሐፍ አካትቼ አቅርቤዋለሁ።



# ምዕራፍ አንድ

## ምስጢረ ቁርባን

ቁርባን ቃሉ የሱርስት ቃል ሲሆን ትርጉሙም ያለ ዋጋ በነፃ የሚቀርብ መባ አምሀ /እጅ መንሻ/ ማለት ነው። በብሉይ ኪዳን ዘመን እስራኤላውያን ስለ ኃጢአታቸው ሆነ ስለ እግዚአብሔር ክብር ብለው የሚያቀርቡት የእንስሳት ደም ሌላ እጅ መንሻ ሁሉ መሥዋዕት፣ ቁርባን ይባል ነበር።

በሐዲስ ኪዳን ግን ቁርባን ወይም መሥዋዕት ማለት እግዚአብሔር ራሱን ከሰው ልጆች ጋር ለማስታረቅ መባ፣ አምሀ አድርጎ ያቀረበው አማናዊው /እውነተኛው/ መሥዋዕት የእግዚአ ብሔር በግ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ይህንን ነገር ዮሐንስ በወንጌሉ እንዲህ አለ «በነገው ዮሐንስ ኢየሱስ ወደ እሱ ሲመጣ አይቶ እንዲህ አለ፡ እነሆ የዓለምን ኃጢአት የሚያስወግድ የእግዚአ ብሔር በግ» /ዮሐ.1÷29/ ደግሞ ለዓለሙ ደህንት ከእግዚአብሔር ፍቅር የተነሣ የተሰጠ ስለመሆኑ ሲጽፍ «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወድዷልና» /ዮሐ 6÷16/ የሰው ልጅ በምክረ ዲያቢሎስ ተገፋፍቶ ሕገ እግዚአብሔርን በማፍረሱ ሕይወቱ አድፎ አምላኩ አዝኖ የዘላለም ፍርድ ተፈርዶበት ኃጢአተኛ በነበረ ጊዜ ይህ መሥዋዕት ስለ ደካማው ሰው በመስቀል ላይ ቀረበ «ገና ደካሞች ሳለን ክርስቶስ ዘመኑ ሲደርስ ስለኃጢአተኞች ሞቶአልና» /ሮሜ 5÷6/ ስለኃጠ አት ስርየት ስለ ቁስለ ኃጢአት ፈውስ የተሰጠን መሥዋዕት መሆኑን ሲያረጋግጥ ነው። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ቃል ለሮሜ ክርስቲያኖች የጻፈላቸው።

በአጠቃላይ በዘመነ ሐዲስ ቁርባን ማለት የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም ሥጋውና ደሙ ነው። ብርሃነ ዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲጽፍ ለቆሮንቶስ ምዕመናን





እንዲህ ብሎአል «ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ደም የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት» /1ኛ ቆሮ 11÷27/ በተጨማሪም «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዶአልና» 1ኛ ቆሮ 5÷7/ በማለት እውነተኛው መሥዋዕት የሐዲስ ኪዳን ፋሲካ ክርስቶስ እንደሆነ አስገንዝቧቸዋል። በሰውና በእግዚአብሔር መካከል የነበረውን ልዩነት አስወግዶ የጸናውን የበደል ግንብ አፍርሶ ሰው በገዛ እጁ ያመጣውን ኃጢአት ለማስተስረይ መሥዋዕት አቅራቢው ሊቀካህናት ኢየሱስ ክርስቶስ ራሱን መሥዋዕት አድርጎ በመስቀል ላይ ያቀረበው ሥጋውን ቆርሶ ደሙን አፍስሶ የሰጠው ከባሕርይ አባቱ ከአብ ከባሕርይ ሕይወቱ ከመንፈስ ቅዱስ ከራሱ ለማስታረቅ ስለ ኃጢአተኞች መሆኑ ለዕብራውያን ሰዎች ተጽፎላቸዋል /ዕብ 10÷12/ «እርሱ ግን ስለኃጢአት አንድን መሥዋዕት ለዘላለም አቅርቦ በእግዚአብሔር ቀኝ ተቀመጠ» ይላል።

## የሥርዓቱ ስጀማመር

አማናዊውን የቅዱስ ቁርባን ሥርዓት የመሠረተው ራሱ አምላካችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ሥርዓቱንም የጀመረበት ዕለቱ የስቅለት ዋዜማ በጸሎተ ሀሙስ ነው። በዚህ ዙሪያ ወንጌላውያን የፃፉትን መመልከት ለአንባብያን ጥሩ ማስረጃ ይሆናቸዋል በመጀመሪያ ወንጌላዊው ማቴዎስ ሲፅፍ /ማቴ. 26÷26/ «ሲበሉም ሕብስቱን አንስቶ ይዞ ባረከ አከበረ ለወጠ፣ ጽዋውንም ይዞ አከብሮ ለውጦ ትኩስ ደም አድርጎ «ዝ ሥጋየ ዝ ደምየ» ይህ ሥጋዬ ይህ ደሜ» ብሎ ሰጥቷቸዋል።

አንድም ሕብስቱን አንስቶ ባረከ ቆረሰ ፈተተ ዓሥራ ሶስት አደረገ አንዱን እርሱ ተቀብሎ አስራ ሁለቱን ለሐዋርያት ሰጥቷቸዋል ይህ ለአብነት ነው ዛሬ ካህኑ መጀመሪያ እርሱ ቆርቦ በኋላ ምዕምናንን የሚያቆርበው ለዚህ ነው። ጌታ እንዲህ ባያደርግ





ኖሮ ካህናቱ እኛን ብቻ አቀብለው እነርሱ ሳይቀበሉ በወጡ ነበር ሲሰጣቸውም ሁላችሁም ከዚህ ጠጡ ብሎ እንደሆነ ወንጌላውያኑ ጽፈውታል /ማር 14÷22፣ ሉቃ 22÷19፣ 1ኛ ቆሮ 11÷23/

በዚህ መሠረት መሥዋዕተ ወንጌል ወልደ እግዚአብሔር ሰው በሆነ ጊዜ ወዶ ስላቀረበልን በሥጋ ወደሙ ቅዱስ ቁርባንነት ሁላችን እንከብር ዘንድ ለሚያምኑ ሁሉ መንጻትና ሕይወት የሚገኝበት አንዲት መሥዋዕት ለዘላለም የማትሻር የማትለወጥ አድርጎ ሠራ ይችም መሥዋዕተ ወንጌል ናት /ዕብ 10÷14/

እዚህ ላይ አንባብያን ልብ እንዲሉት የምገልጸው መድኃኒታችን ይህን ታላቅ ሥርዓትና ምስጢር ሲመሠርት ከእርሱ ጋር ያሉት አስራ ሁለት ደቀ መዛሙርቱ ብቻ ናቸው እንጂ እንደቀድምው ይከተሉት ለነበሩት ሕዝብ ሁሉ አልገለጸውም ዛሬም ቤተክርስቲያን በመጎናጸፍያ ሸፍናና አክብራ የምታቀርበው ለዚህ ነው። አንድም ጌታችን በመስቀል ላይ በተሰዋ ጊዜ ፀሀይ ጨልማ ጨረቃ ደም ለብሳ ከዋክብት እንደ ቃርያ ፍሬ እረግፈው ሸፍነውታል። መሥዋዕቱን እንኳን ተራ ተርታ ሰው የሰማይ መላዕክት አይነኩትም ይህ በስልጣነ ሐዋርያት ለተተኩ ለካህናት ብቻ የተሰጠ ነው።

ገ ፅ 5



# ምዕራፍ ሁለት

## ምሣሌና ትንቢት

ቅዱስ ቁርባን የተመሠረተው በዘመነ ሀዲስ ነው። ብንልም እንደ እንግዳ ደራሽ እንደ ውሀ ፈሳሽ በድንገት የተከሰተ አይደለም። በብሉይ ኪዳን በዘመነ ኦሪት ብዙ ምሳሌዎች ሲመሰሉለት ብዙ ትንቢት ሲነገርለት የቆየ ነው።

### የምሳሌ ስዩነቶች

መሥዋዕተ አቤል፣ የአዳም ልጅ አቤል ነጹህ ባሕርይ እግዚአብሔር ንጹህ መሥዋዕት ይገባዋል ብሎ ከበረት ከበጎቹ መልካሙን ጠቦት እንከን የሌለበትን በግ ማለት ቀንዱ ያልከረከረውን ጠጉሩ ያላረረውን ጥፍሩ ያልዘረዘረውን መርጦ ሰውቶ አቅርቧል።

ምክንያት ከአቤልና ከቃየን አብረው የተወለዱ መንትያ ሴቶች ነበሩ /ዘፍ.4÷17/ ወላጆቻቸው ለማራራቅ የአቤልን መንትያ ለቃየን የቃየንን መንትያ ለአቤል ለዋውጠው ቢያጋቡ ከቃየን የተወለደችው መልከመልካም ነበረችና ቃየን ቢከፋው እንግዲያውስ ለእግዚአብሔር መሥዋዕት አቅርብለትና እርሱ የተቀበለለት /የመሠከረለት/ መልከ መልካሟን ያግባት አሏቸው ያን ጊዜ አቤል በንጹህ ልብ ንጹህ መሥዋዕት አቀረበ «አቤልም ደግሞ ከበጎች በኩራትና ከሰቡ አቀረበ»። /ዘፍ. 4–4/ ደግሞም ቅዱስ ጳውሎስ ሲመሰክርለት «አቤል ከቃየል ይልቅ የሚበልጠውን መሥዋዕት ለእግዚአብሔር በእምነት አቀረበ» /ዕብ 11–4/ እግዚአብሔር የአቤልን መሥዋዕት ተቀበለ ቃየንም በዚህ ቀና ይህ የጥፋት ሰው ፊቱ ጠቆረ ወንድሙንም ገደለው። ይህ አቤል ያቀረበው እግዚአብሔር የተቀበለው ንጹህ መሥዋዕት የቅዱስ ቁርባን ምሣሌ ነው።





ስለ ይስሐቅ ፈንታ ለአብርሃም በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ የቀረበው በግ «ከእነዚህም ነገሮች በኋላ እግዚአብሔር አብርሃምን ፈተነው እንዲህም አለው አብርሃም ሆይ አብርሃምም እነሆ አለሁ አለ የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞርያም ምድር ሂድ እኤም በምነግርህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው» /ኦ.ዘፍ. 22÷1-2/

አብርሃምም ለዚህ ቃል ታዝዞ በስተ እርጅና የወለደውን ልጁን ይዞ ሔደ እንጨቱን ረብርቦ ይስሐቅን አጋድሞ ሾተሉን ካንገቱ አሳረፈው ልብን የሚያውቅ የእስራኤል አምላክ እግዚአብሔር የልቡን ውሣኔ ቁርጥ ሕሊናውን አይቶ «ተው ዓለም የሚድን በኃያሉ በኔ ልጅ ደም ነው እንጂ በደካማው ባንተ ልጅ ደም አይደለምና ተው» አለው ወዲያው አብርሃም ሽቅብ ቢያይ በግ በዕፀ ሳቤቅ ተይዞ ወረደለት ልጁን ፈትቶ በጉን ተቀብሎ ሰውቶታል ይስሐቅ የዚህ ዓለም በግ የጌታ ምሣሌ ነው። በግዕ ቤዛ ይስሐቅ ሁኖ እንደ ተሠዋ ጌታም ቤዛ ዓለም ሁኖ ተሰውቶልናል።

- ካህኑ መልከ ፃዴቅ ለአብርሃም ያቀረበው ሕብስትና ወይን /ዘፍ. 14–18/
- አምስቱ የቁርባን ዓይነቶች /ዘሌ. ከምዕራፍ 17../
- ከግብፅ የወጡ እስራኤላውያን የሠውት በግ /ዘፀ. 12፣ 1ኛቆሮ 5÷7/ እነዚህ ሁሉ የአማናዊው ቁርባን የድህነተ ሥጋ ወነፍስ መሥዋዕት የኢየሱስ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ምሳሌያት ነበሩ።

### የትንቢት ፍፃሜዎች

«ጥበብ ቤትዋን ሠራች ሰባቱንም ምሰሶዎችዋን አቆመች ፍሪዳዋን አረደች፣ የወይን ጠጅዋን ደባለቀች ማዕድዋን አዘጋጀች ባሪያዎችዋን ልካ በከተማይቱ ከፍተኛ ስፍራ ላይ ጠራች አላዋቂ





የሆነ ወደዚህ ፈቀቅ ይበል አእምሮ የጐደላቸውን ... እንዲህ አለች ኑ እንጀራዬን ብሉ የደባለቅሁትንም የወይን ጠጅ ጠጡ አላዋቂነትን ትታችሁ በሕይወት ኑሩ።» /ምሣሌ 9÷1-5 በዚህ ትንቢት ቃል መሠረት ጥበብ የተባለው መድኃኒት ዓለም ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። ቤት የተባለው ቤተክርስቲያን እንዲሁም የክርስቲያኖች ሰውነት ሲሆን ሰባቱ ምሶሶች የሰባቱ ምስጢራተ ቤተክርስቲያን ምሣሌ ናቸው። የታረደው ፍሪዳ ቅዱስ ሥጋው የተደባለቀው ወይን ደግሞ የክቡር ደሙ ምሣሌ ነው።

አዕምሮ የጐደላችሁ ኑ እንጀራዬን ብሉ የደባለኩትን የወይን ጠጅ ጠጡ ማለት ኃጢአተኞች ሁሉ የፅድቅ መንገድን ማስተዋል የተሣናችሁ ኑ ንስሀ እየገባችሁ ከበደል እየተመለሳችሁ ሥጋዬን ብሉ ደሜንም ጠጡ ማለት ነው፣ በእውነት ይህ እንዴት ያለ ግብዣ ነው። ስለዚህ ግብዣ ምን ይባላል! እውነተኛ ወዳጅ ለልጆቹ ፈውስ ያዘጋጀዉን የሕይወት ግብዣ። /ዮሐ. 21–12፣ ራእይ 3÷20/





# ምዕራፍ ሦስት

## የምስጢረ ቁርባን መገኛ ስመቤታችን ድንግል ማርያም ናት

«ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ /ሕብስት/ እኔ ነኝ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው።» /ዮሐ. 6÷51/

ይህንን ቃል መርምራችሁት ታውቃላችሁ? የሚያስተላልፈው ስ ምሥጢራዊ መልዕክት ምን እንደሆነ አስተውላችኋል? እውነት እላችኋለሁ የዘላለም ሕይወት ስለሚገኝበት ስለ ክርስቶስ ሥጋ ይናገራል። ይህ ሥጋ ደግሞ የተገኘው ከድንግል ማርያም ነው።

ከሰማይ የወረደ ሥጋ ሳይሆን ቃል /ወልድ/ ስለ መሆኑ እንደማትጠራጠሩ እርግጠኛ ነኝ። የዮሐንስ ወንጌል መጀመሪያ እንዲህ ይጀምራል «በመጀመሪያ ቃል ነበረ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ... ቃልም ሥጋ ሆነ» /ዮሐ. 1÷1ና14/

«ቃልም ሥጋ ሆነ» ሲል በትክክል የእግዚአብሔር ልጅ /ወልደ እግዚአብሔር/ ከሰማያት ወርዶ ከድንግል ማርያም ከሥጋዋ ሥጋ ከነፍሷ ነፍስ ነስቶ ሰው ሆኖ መገለጡን ማረጋገጡ ነው።

መልአኩ ገብርኤል ለድንግል ማርያም ባበሠራት ጊዜ እንዲህ አላት «እነሆም ትፀንሻለሽ ወንድ ልጅም ትወልጃለሽ ስሙንም ኢየሱስ ትይዋለሽ፣ እርሱ ታላቅ ነው። የልዑል ልጅም ይገባል» /ሉቃ. 1÷31/

ይህን የመልአኩን ቃል ከመሠረቱ ለመረዳት የብሉያትን ታሪክ የነቢያትን ትንቢት እንድንመለከት እንገደዳለን። ነቢዩ የአሞጽ ልጅ ኢሳይያስ በትንቢቱ ስለ እርሷ እንዲህ አለ «... ስለዚህ ጌታ ራሱ ምልክት ይሰጣችኋል፣ እነሆ ድንግል ትፀንሳለች

ገ ፅ 6



ወንድ ልጅም ትወልዳለች፡ ስሙንም አማኑኤል ብላ ትጠራዋለች።» /ኢሳ. 7÷14/

ይህን የነቢዩን ቃል ልብ በሉት! ለዚህ ነው እኛ ስለ ድንግል ማርያም ባለን አስተምህሮት የመዳን ምክንያት /የመዳን ምልክት/ የምንላት ነቢዩ ጌታ አምላክ ምልክት ይሰጣችኋል ብሎ «እነሆ» የሚለውን አያያዥ ቃል በመጠቀም ድንግል ትፀንሳለች ወንድ ልጅም ትወልዳለች በማለት እግዚአብሔር ለዳዊት ቤት ለመሚው መገለጥና ለሰው ልጆች መዳን ምልክቲቱ ድንግል መሆኗን በድንግልና መጽነሷ መሆኑን ገልጧል።

በኋላም ጊዜው ሲደርስ ትንቢቱ ሲፈጸም መልአኩ ገብርኤል ከእግዚአብሔር ዘንድ የተላከው «ወደ አንዲት ድንግል» እንደሆነ ወንጌላዊው ሉቃስ ከነቢዩ ከኢሳይያስ ቃል አገናኝቶ ሲጽፍ «የድንግሊቱም ስም ማርያም ነበር» /ሉቃስ 1÷27/ በማለት ገልጧታል።

ይህ መልአክ በፊቷ ያቀረበውን ሰላምታ ታስተውሉታላችሁ? «ደስ ይበልሽ ጸጋ የሞላብሽ ሆይ ጌታ ካንቺ ጋር ነው» /ሉቃ. 1÷28/ አላት እንጂ «ጸጋ የምትምይ» ብሎ ገና ስለሚሰጥ የወደፊት ስጦታ አልነገራትም ሰውና እግዚአብሔር በተለያዩበትና እርቅ ባልተፈጸመበት ጊዜ እርሷ ግን ጸጋን ተሞልታ ከእግዚአብሔር ተመርጣ ለተነገረላት ትንቢት ፍጻሜ «ያመነችና ብፅዕት ነበረች» ዘመዷ ኤልሳቤጥ ወደርሷ በመጣች ጊዜ እንደሰው ሰውኛው አባባል ባልቴቷ ሴት ማለት የነበረባት ልጄ ሆይ እንዴት ወደኔ መጣሽ? ነበር እርሷ ግን «የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል?» /ሉቃ. 1÷43/ አለቻት እንጂ. ስለ ድንግልም ስትመሰክርና ስታመሰግናት «ከጌታ የተነገረላት ቃል ይፈጸማልና ያመነች ብፅዕት ናት።» /ሉቃ. 1÷35/ ብላለች።





መድኃኒተዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ ከእርሷ ስለነሳው ስለ ተዋሃደው ለዓለም መዳን ስለሚሰጠው ቅዱስ ሥጋው ክቡር ደሙ ሲያስተምር «... እውነት እውነት እላችኋለሁ የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም።» /ዮሐ. 6÷53/ ብሏል።

ለዚህ ነው ድንግል ማርያም የምሥጢረ ቁርባን መገኛ፣ መገለጫ ናት የምንለው እርሷን ሳይዙ በወላዲተ አምላክነቷ፣ በንጽሕናዋ በድንግልናዋ፣ በክብሯ፣ ባማላጅነቷ ሳያምኑ ማቁረብም መቁረብም አይገኝም። አማናዊውን መሥዋዕት ማግኘት አይቻልም። ባለቤቱም ክርስቶስ «የሰውን ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ» በማለት የተናገረው ቃል የሥጋ መገኛ፣ ፍጹም ሰው ሆኖ መገለጡ መሆኑን ያረጋግጥልናል። ይህም የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ የተሰኘ /የሆነ/ ከሰው ወገን ከሆነች በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ነፍስ ከጸናች ከድንግል ማርያም በመወለዱ መሆኑን ጭምር የሚገልጽ ቃል ነው።

በዚህ ምክንያት እመቤታችን የምሥጢረ ቁርባን መገኛ እየተባለች በአበው ተመሰገነች ከአበው ወገን /አባ ሕርያቆስ/ በቅዳሴው እንዲህአመሰገናት «ማርያም ሆይ ስለዚህ እንወድሻለን ከፍ ከፍም እናደርግሻለን እውነተኛ የጽድቅ መብልንና እውነተኛ የሕይወት መጠጥን ወልደሽልናልና።» /ቅዳሴ ማርያም ቁ. 9/

ምስጋናውንም በመቀጠል ከላይ ዮሐንስ 6÷53 ጠቅሼ ማብራሪያ የሰጠሁበትን ነጥብ በምታገኙበት መልኩ ሊቁ አባታችን እንዲህ ይላል «ድንግል ሆይ የሚበላውን ያፈራሽልን የሚጠጣውን ያስገኘሽልን ወዮ ካንቺ የተገኘ ኅብስት በማመን ከርሱ ለሚቀበሉ ሕይወትንና ደኅንነትን የሚሰጥ ነው። ወዮ ከአንቺ የተገኘ ኅብስት በማመን ከርሱ ለማይቀበሉ ሰዎች የማይላመጥ ጽኑ ነው። ይኸውም ኃያል የሚሆን የአድማስ ደንጊያ ነው፤ ወዮ ከአንቺ የተገኘ ጽዋ በማመን ከእርሱ ለሚጠጡ ሰዎች ጥበብን የሚገልጽ ሕይወትንም የሚሰጥ ነው፤ ወዮ ከአንቺ የተገኘ ጽዋ በማመን





ከእርሱ ለማይጠጡ ሰዎች የሚያሰክርና የሚያፍገመግም የሚጥልና ኃጢአትን ስለማስተሠርይ ፋንታ ኃጢአትን የሚጨምር ነው።»

ልጇ. ክርስቶስም ከእርሷ ስለነሳው አምነው ለሚቀበሉት ሕይወት ስለሚሰጠው ለዓለም ድህነት ስለሚቆርሰው ክብር ሥጋውና ቅዱስ ደም «ይህ ሰው ሥጋውን ልንበላ ይሰጠን ዘንድ እንዴት ይችላል?» ብለው እርስ በርሳቸው ለተከራከሩ አይሁድ /ዮሐ. 6÷52/ መልስ ሲሰጥ እንዲህ አላቸው «ከሰማይ የወረደ እንጀራ ይህ ነው፤ አባቶቻችሁ መና በልተው እንደሞቱ አይደለም ይህን እንጀራ የሚበላ ለዘላለም ይኖራል» /ዮሐ. 6÷58/

እንዲሁ ደግሞ በቅዳሴ ካህኑ በመባረክ ሰዓት እንዲህ ይላል «አምናለሁ አምናለሁ እስከ መጨረሻይቱም እስትንፋስ እታመናለሁ በሁለት ወገን ድንግል ከምትሆን ከሁላችን እመቤት ከቅድስት ማርያም የነሣው የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችንም የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው ደሙ ይህ እማሬ እንደሆነ ያለመቀላቀልና ያለትድምርት ያለመለወጥና ያለመለየት ከመለኮቱ ጋር አንድ ያደረገው የጳንጤናዊ ጲላጦስም ዘመን ባማረ ምስክርነት ምስክር የሆነ ስለ እኛና ስለ ሁላችንም ሕይወት አሳልፎ የሰጠው» ሕዝብም ሁሉ «አሜን» በማለት በዚህ ቃል መታመናቸውን ይመሰክራሉ።

ስለዚህእኛ ክርስቲያኖች እንዲህ እናምናለን እንዲህም እንታመናለን የበጉን መገኛ የድኅነታችንን ምክንያት በክብሯ ሁሉ እናከብራታለን ያዳኛችንን እናት ጸጋን የተመላሽ ሆይ ደስ ይበልሽ ስንላት እንኖራለን «ትውልድ ሁሉ ብፅዕት ይሉኛል» /ሉቃ. 1÷48/ እንዳለች በአንድ መልአክ ገብርአል በአንዲት ባልቴት ኤልሳቤጥ ብቻ ተመስግና አትቀርም። የልጅ ልጆቻችን ሁሉ ያመሰግኗታል።





## ቅዱስ ቁርባን ምሥጢር የመባሉ ምክንያት

«ይህንም ስታነቡ የክርስቶስን ምሥጢር እንዴት እንደ ማስተውል ልትመለከቱ ትችላላችሁ» /ኤፌ. 3÷4/

የቅዱስ ቁርባን ሥርዓት ምሥጢር መባሉን ለራሳቸው የክህደት አስተምህሮቶ /እንድምታ/ የሚሰጡት ሰዎች አሉ። ምእመናንን ግራ ለማጋባት ቁርባንን ለምን ምሥጢር ነው ይሏችኋል? እያሉ ያልተባለ የሚሉ ያለተጻፈ የሚያነቡ ለራሳቸው ሃሳብ ወንጌልን የሚያጣምሙና እውነትን የሚቃወሙ ናቸው።

ቅዱስ ቁርባን ምሥጢር መባሉ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ስለሰው ልጆች ኃጢአት በዕለተ ዓርብ ከመስቀሉ በፊት በዋዜማው ሐሙስ ማታ ከአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ ኅብስቱን አንስቶ ባርኮና ቀድሶ ለደቀመዛሙርቱ «ይህ ሥጋዬ ነው» ብሎ ሰጣቸው ስለዚህ ኅብስቱ ተለውጦ ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ወይኑም ተለውጦ ደመ ወልደ እግዚአብሔር መሆኑ ታላቅ ምሥጢር ነውና ምሥጢር የሚለውን ስያሜ ያገኘው ለዚህ ነው /ማቴ. 26÷26፣ ማር. 14÷22/ ዛሬ ቀሳውስቱ ኅብስቱን በጻሕል ወይኑን በጽዋዕ አድርገው የሚያቀርቡት ቁርባን ተለውጦ ኅብስቱ ሥጋ አምላክ ወይኑም ደመ አምላክ ለመሆን የሚለወጠው ቄሱ «አእኰተ ባረከ ወቀደሰ» ብሎ በባረከው ጊዜ የካህኑ ሥልጣን፣ ቃለ እግዚአብሔር፣ ግብረ መንፈስ ቅዱስ ኅብስቱን ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር /ሥጋ አምላክ/ ወይኑንም ደመ ወልደ እግዚአብሔር/ ደመ አምላክ አድርጎ ይለውጠዋል። ይህም ለአማኞች ብቻ በእምነት ዓይን የሚታይ ለማያምን የተሰወረ ስለሆነ ቅዱስ ቁርባንን ምሥጢር ያሰኘዋል።

በተጨማሪ በሚታይ አገልግሎት የማይታይ ጸጋ ስለሚገኝበት ምስጢር ተሰኝቷል ማለት ካህኑ የሚፈተተው አማኙ የሚቀበለው የቀረበው መሥዋዕት ሕብስቱና ወይኑ የሚታይ ሲሆን

ሲለወጥ በመቀበላችን የመንፈስ ቅዱስ ጸጋ በኛ ሲያድር አይታይምና ነው::

በመጽሐፈ ግብረ ሕማማት ዘሐሙስ ገጽ 192 ላይ /በአራት እምላካችን «ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት» ብሎ አንድ ጊዜ በተናገረው ቃል በዓለም የሚገኙ ፍጥረታት ሁሉ ሲዋለዱና ሲራቡ እንደሚኖሩ ሁሉ አሁንም እንደዚሁ «ይህ ሥጋዬ ነው ይህ ደሜ ነው» ብሎ የተናገረው ቃል በታቦት ላይ የሚቀመጠውንና በየቤተ ክርስቲያኑ ዘወትር የሚቀርበውን መሥዋዕት ሥጋ ወልደ እግዚአብሔር ደመ ወልደ እግዚአብሔር ወደ መሆን ይለውጠዋል ሲል ታላቁ የቤተ ክርስቲያን አባት /ቅዱስ ዮሐንስ አፈወርቅ/ ይህን ምሥጢር ገልጾ ጽፏል::

በሐዲስ ኪዳን የቅዱስ ቁርባን አፈጻጸም ጊዜ የማታዩ የሚጨበጡ የሚዳሰሱ ሁለት ነገሮች አሉ:: እነርሱም ኅብስቱና ወይኑ ናቸው: ኅብስቱ የሚዘጋጀው ከንጹህ ስንዴ ብቻ ነው:: ወይኑ የሚዘጋጀው ከንጹህ የወይን ፍሬ ወይንም ዘቢብ ብቻ ነው:: በስንዴውም ሆነ በወይኑ ላይ ሌላ ምንም ነገር አይጨመርም:: ስለዚህ የቤተ ክርስቲያን ቀኖና /ሕግ/ እንዲህ ሲል ያስጠነቅቃል «ንጹሕ ከሆነ ከስንዴ ንጹሕ ከሆነም ከወይን በቀር ሌላ በቤተ ክርስቲያን አይሠው::» /ዲጥ. ረስጠጅ 3/ ፍትሕ መንፈሳዊ ገጽ 138

እስኪ አንድ ነገር አንባቢያንን ላስታውሳችሁ ምሥጢ ራችሁን የምትነግሩን ለማን ነው? ለምትወዱት ጓደኞችሁ አይደለምን? እንዲሁ ነው ምሥጢር ለሚወዱት ጓደኛ እንጂ ለማንም እንደማይነግሩት ሁሉ ይህም የኅብስቱና የወይኑ መለወጥ የሚገለጸው ለመንፈስ ቅዱስ ምስጢረኞች ለአማኞች ብቻ የተሰጠ ጸጋ ስለሆነ ምሥጢረ ቁርባን ተሰኝቷል::





# ምዕራፍ አራት

## ቅዱስ ቁርባን ስለ ፈሰጉ ብቻ የሚገቡበት ሕይወት አይደለም

«ሰው ግን እራሱን ይፈትን እንዲሁም ከእንጀራው ይብላ ከጽዋውም ይጠጣ ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና» /1ቆሮ. 11÷27/

በዚህ ርዕሳችን በሰፊው የምንመለከተው ተያይዞ የተጠቀሰውን የሐዋርያውን መልዕት ተንተርሰን ሲሆን በዚህ ሥር ከ2 ያላነሱ ነጥቦችን ጨምረን እንመለከታለን::

ማንኛውም አማኝ ስለፈለገ ብቻ ተንደርድሮ የሚገባበት ሕይወት ሳይሆን ቅዱስ ቁርባን አስቀድሞ ወደ ቅዱስ ቁርባን ሕይወት ሲገባ የሚከተለውን ነገር ጠንቅቆ ማወቅና ወድዶና ፈቅዶ ስለ ቅዱስ ቁርባን የሚደርስበትን መከራና ፈተና ለመቀበል መወሰንና መዘጋጀት ይኖርበታል:: ለዚህም ደግሞ ወሳኙ ምክረ ካህን ነው::

### ምክረ ካህን

ምክረ ካህን ማለት አማኙ በኃጢአቱ ከተናዘዘ በኋላ ቀኖና መስጠት ማለት ብቻ ሳይሆን ይህ የመጀመሪያ ደረጃ ሆኖ ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል ጥያቄ ላቀረበው ወይም ለተዘጋጀው አማኝ ከካህኑ ጥልቅ ምክርና የተብራራ ምሪት ሊሰጠው ክርስቶስ ለደቀመዛሙርቱ የእርሱ በመሆናቸው የሚገጥማቸውን አስቀድሞ እንዲያስተውሉ አድርጎ እንዳዘጋጃቸው ካህኑም አማኙን ሊያዘጋጀው ይገባል::

ምክረ ካህን ማለት በአጠቃላይ መልኩ አማኙን ከመቁረቡ በፊትና ከመቁረቡ በኋላ ያለውን ሕይወት ሁሉ ያጠቃልላል እንጂ





ኃጢአትን መናዘዝና የመስዋዕቱን መለወጥ እንዲያምን ማስተማር ብቻ ማለታችን አይደለም:: አብነት እንዲሆን ከዚህ በታች እንደጠቀስነው ሊሆን ይገባል::

አንድ አማኝ ወደ ቅዱስ ቁርባን ከቀረበ በኋላ ስለሚጠብቀውና ስለሚመራው ሕይወት ካህኑ በዝርዝር ይግለጽለት:: ክርስቶስን መከተል ማለት ወደዚህ ሕይወት መግባት ማለት ባለቤቱ እንደተናገረው መስቀሉን መሸከም ማለት ስለመሆኑ ይግለጽለት:: ምን አልባትም አማኙ በቅዱስ ቁርባን ተወስኖ ሲኖር በዓለሙ ዘንድ የተጠላና የተተቸ ሊሆን ይችላል:: ይህን ነገር ክርስቶስ እንዲህ በማለት ተናግሯታል:: «ስለእኔ በዓለም ውስጥ የተጠላችሁ ትሆናላችሁ» /ዮሐ. 15:18-23/ ምክንያቱም የዓለምን ሥራ ስለምናልክስበትና ስለ ምንንቅበት አለም ሊጠላን ሊተቸን ምክንያት ሊፈልግብን ይችላል ሁሉም የሚወደው ወገን ወገኑን ነውና

ደቀመዛሙርቱ እርሱን በመከተላቸው ዓለም የአበባ ምንጣፍ እንጥፎ ውዳሴ አዘጋጅቶ አይደለም የተቀበላቸው ለአንገታቸው ሰይፍ ለሰውነታቸው እሳት እንጂ /ማቴ. 24÷9/ ስለዚህ አንተም ሠሰል መከራዎች በደረሰብህ ጊዜ የተቀበልከውን ታውቀዋለህና ስለ እርሱ ራስህን ክደሃልና ስለሥሙና ስለ ቅዱስ ቁርባን በሚደርስብህ ደስ ሊልህ ይገባል ምርጫህ ሕይወት በመሆኑ ሰይጣን መቸነፉንና ባንተመቅናቱን እወቅ ስለዚህ ካህኑ ይህንና መሰል ጉዳዮችን ሊያሳውቀው ይገባል እንዲህ እያለ ልጄ በርታ አይዞህ ዓለም ቢጠላህ አትደነቅ ደግሞም የገዛ ሃሳብህ ዕር ይሆንብሃል ይህንን አይነቱን ፈተና በዚህ በዚህ መልክ ተቋቁመው ይህ ቢገጥምህ እንዲህ ተወጣ የሰዎች ባንተ ላይ መለወጥ አይደንቅህ ምክንያቱም ሰይጣን አንተን ለመፈተን ሊጠቀምባቸው ይችላል የሰይጣንን የውጊያ ባህርያት እወቅ ሊለው ይገባል::

በሌላ መንገድ ሰይጣን እራስህን በማይገባ ክስ እንድትከስና በጀመርከው ሕይወት እንዳትገፋበት በአሉባልታዎች ሊያውክህ





ይችላል:: አንተ ግን ስለተቀበልከው በቂ ዝግጅትና እውቀት ካለህ መልስትሰጥበታለህ::«በእናንተ ስላለ ተስፋ ምክንያትን ለሚጠይቋችሁ ሁሉ መልስ ለመስጠት የተዘጋጃችሁ ሁኑ» /1ጴጥ. 3÷15/ ይሔውም «አንተ ቁርበህ እንዲህ ትሆናለህ» «ይህ ሰው ከቆረበ ጀምሮ አቅበዘበዘው» «መቁረብ በማይገባት ጊዜ ቁርባ አደብ አጣች» የመሳሰሉትን ይህ አይነት አሉባልታ ሌሎችን በአንተ ላይ አነሳስቶ የመክሰስ የዲያቢሎስ ውጊያ ነገ ደግሞ ራስህን በራስህ ላይ አነሳስቶ ለመክሰስ የሚደረግ ቅድመ ዝግጅት መሆኑን ልብ በልና ለአሉባልታ ሳትገዛና እነርሱ ባሉህ /ባሙህ/ ነገር ሳትገኝ ተገቢውን መልስ በትህትና መስጠት ይገባል:: ይኸውም እኔ የተቀበልኩት ሰላም ነሺውን ሳይሆን፣ አደብ የሚያሳጣውን፣ ሳይሆን የሚያቅበዘብዘውን ሳይሆን፣ የሰላሙን አምላክና ሕይወትን የሚቀድሰውን ጌታ ነው /ኢሳ. 9÷6/ በማለት ደግሞ::

አንተ ወገኔ የምትናገረውንና እንዲህ የምትተቸውን ታውቃለህ ሰላም ነሺ አቅበዝባዥ፣ የምትለውን ሥጋውን በመቁረስ ደሙን በማፍሰስ ለዓለም ሰላም የሰጠውን ኢየሱስ ክርስቶስን ነው እኮ! ልክ እንደ አይሁድ ሕዝቡን ሰላም ነሳ ብለው ለቄሳር እንደከሰሱት በማለት ምስጢሩ ያልገባውን ወገንህን ማስተማርና ሰይጣንን ማሳፈር ይገባሀል::

### ሰው ግን ራሱን ይፈትን

ሐዋርያው ይህን ኃይል ቃል የተናገረበትን ቁም ነገር ስንመረምር ፊታችንና ኋለኛ ሕይወታችንን አጢነን የምናስተካክልበት በሁለት ክፍል የምንመለከተው ጉዳይ እንዳለ ያመለክተናል እነርሱም፣

ሀ. ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል እስክተነሣሣንበት ጊዜ ድረስ ያለውን ሕይወትትንን እንዴት እንዳሳለፍን

ገ
ፅ
8



ለ. ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል ያደረግነው ዝግጅት ምን እንደ ሚመስልና ስለተቀበልነው ምስጢር ያለንን እውቀት እንድ ንመረምር የሚያደርገን ነጥብና ስለ ሕይወታችን ትኩረት እንድንሰጥ የሚያደርግ ኃያል ቃል ነው።

ሀ. የመጀመሪያውን ነጥብ ስንመለከት ወደ እግዚአብሔር እስከተጠራንበት ለቅዱስ ቁርባን ዝግጅት እስከጀመርንበት ገዜ ድረስ ሕይወታችንን እንዴት እንዳሳለፍነው ልንመረምር ይገባል የሐዋርያውም ቃል «በሃይማኖት ብትኖሩ እራሳችሁን መርምሩ» /2ቆሮ. 13÷5/ ነው የሚለው ምክንያቱም ቀድሞ የተበላሸ፣ ያልተስተካከለ፣ እግዚአብሔር የማይፈቅደውና ያዘነበት ሕይወት ሊኖረን ይችላል።

ስለዚህ በዚህ ደረጃ የምናደርገው አትኩሮት ይህ ሕይወት እግዚአብሔር እንደሚወደው፣ እንደሚፈቅደው ሆኖ ሊስተካከል እንደሚችል ትምህርት የምንወስድበትና በወሰድነው ትምህርት ራሳችንን ልናስተካክልበት ነው።

በሌላ መልኩ ሕይወታችንን በማስተካከልና ንስሐ በመግባት የተውናቸው የራቅናቸው ክፉ ሥራዎች ምን ያሕል ከሕይወታችን እንደራቁና በፊታችን እንደተጠሉ በፈተና መልክ ወደ ፊት በሚቀርብልንና በሚያጋጥሙን ጊዜ ምን ያህል የመቋቋሙ ብቃት እንዳለንና የዚህ ብቃት ምስጢሩ ዓለምን ያሸነፈውንና ሁሉን ሊያስችለን የሚችለውን አምላክ ምን ያሕል በፍጹም እምነት እንደተከተልነው ልናረጋግጥ ይገበናል ምክንያቱም ያለ እርሱ አንዳች ማድረግ እንዳይቻለን ተጽፏልና። «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉም» /ዮሐ.15÷5 /

ለ. ሁለተኛው ደረጃ ቁረባን ለመቀበል ያደረግነውን ዝግጅት የምንፈተንበት ክፍል ነው ምክንያቱም ያደረግነው ዝግጅት ቅዱስ ቁርባንን ለምንቀበልበት በሰዓት ለተወሰነ ጊዜ ከኛ





ጋር የሚቆይ ብቻ ሳይሆን በቅዱስ ቁርባን ለተቀደሰውና ለተወሰነው ሕይወታችን ዋስትናነት ያለውን እስከ ሕይወታችን ፍፃሜ ድረስ ልንጸናበት የሚገባ ነው ክርስቶስ ከዓለም መርጦ እርሱን እንዲከተሉት ያደረጋቸውን ደቀ መዛሙርቱን እርሱን በመቀበላቸው ወደ ፊት በዓለሙ ውስጥ ከሚደርስባቸው መከራ የተነሳ መንገድ ላይ እንዳይቀሩ ሲያስጠነቅቃቸው «እስከ መጨረሻ የሚጸና ግን እርሱ ይድናል።» /ማቴ.24÷13/ ብሏቸዋል።

ብዙ ሰዎች ለጊዜው በግብታዊነት ተነሣስተው ይህንን ኃጢአት ደግሜ አላደርገውም ስላሉ ብቻ በቂ ዝግጅት አድርገው ይወስዱታል ወይም በዚያን ወቅት ኃይል የሆናቸው ከራሳቸው ጉልበት ከመነጨ ብርታት የወሰኑት ውሳኔ ዘላቂ ይመስላቸውና ወደቅዱስ ቁርባን የሚያደርጉትን ግስጋሴ «ይበል በለው» ያደርጉታል ነገር ግን ወደ ጠባብ ደጅ ከተገባ በኋላና ለጊዜው የታገሰው ጦር መልኩን ቀይሮ ሲመጣ በቀላሉ መዛልና አልፎም ውድቀት ይከተላል ይህ ሁሉ ሊመጣ የሚችለው ቃሉን ስለማናስተውል ነው ቃሉን ደግሞ የማናስተውለው ቃሉን ስለማንሰማ ሊሆን ይችላል ጌታችንም ለአይሁድ «ንግግሬን የማታስተውሉ ስለ ምንድር ነው ቃሌን ልትሰሙ ስለማትችሉ ነው» /ዮሐ. 8÷43/ ብሏቸዋል።





# ምዕራፍ አምስት

## ቅዱስ ቁርባን ለማን

«ኢየሱስም መልሶ ሕመምተኞች እንጂ ባለ ጤናዎች መድኃኒት አያስፈልጋቸውም ኃጢአተኞችን ወደ ንስሐ እንጂ ጻድቃንን ልጠራ አልመጣሁም አላቸው» /ሉቃ. 5÷31/

ይህን ቃል መድኃኒተ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ከኃጢያተኞች ጋር በማዕድ በመቀመጡ ፈሪሳውያን ለምን ከኃጢያተኞች ጋር ይበላል /በማዕድ ይቀመጣል/ ብለው በማንጐራጐራቸው የተነሳ ነው።

ለነዚያ ኃጢአተኞች የሚያስፈልጋቸው መድኃኒተ ሥጋ ወነፍስ እርሱ እንደሆነ መለሰላቸው እንጂ የመጣው ለጻድቃንና ለንጹሀን እንደሆነ አይደለም የተናገረው።

ቅዱስ ቁርባን ለማን የሚለው ጥያቄ በእያንዳንዱ አማኝ ሕይወት የራሱ የሆነ አንድምታ /ትርጉም/ የሚሰጠው ሲሆን የአብዛኛው አመለካከት አማኙን ከቅዱስ ቁርባን የሚያርቅና የወንጌሉ ቃል ተቃራኒ ሆኖ እናገኘዋለን።

ይሁንና በዚህ ምዕራፍ ቅዱስ ቁርባን የሚገባቸው እነማን እንደሆኑ በዝርዝር ለማቅረብ እንሞክራለን።

### ቅዱስ ቁርባን የሚገባቸው፣

ሀ. የመሥዋዕቱን መለወጥ ለሚያምኑ ሕብስቱ ተለውጦ ሥጋው ወይኑ ተለውጦ ደሙ መሆኑን ከልብ ያለ ጥርጥር አምነው ለሚኖሩ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸውን ቃል በእምነት ተቀብለው ለሚከተሉ።

«ሲበሉም ኢየሱስ እንጀራን አንሥቶ ባረከ ቆርሶም ለደቀ መዛሙርቱ ሰጠና እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ። ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ...ደሜ ይህ ነው» /ማቴ. 26÷26/





ለ. ይህ ቅዱስ ቁርባን ለኃጢአት እድፍ መንጺሒ ለኃጢአት ቁስል ፈውስ የተሰጠ መሆኑን ላመኑ ባጠቃላይ ኃጢአትን የሚያስተሰርይ መሆኑንና የዕለት የዕለት የኃጢአት በሽታ መድኃኒትነቱን ለተቀበሉ በተለይ የሚዘጋጀው ለፃድቃን ሳይሆን ለኃጥአን መሆኑን ከልብ ላመኑ ለተቀበሉ «በእውነት አምነው ከእርሱ ለሚቀበሉ ሕይወትና መድኃኒት የኃጢአት ማስተስረያም ሊሆን የሚሰጥ የጌታችንና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ደም ይህ «እማሬ ነው» /ቅዳሴ ሐዋርያት/

«እንዲህም አለ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው» /ማቴ. 26÷ 27

ሐ. የዘለዓለም ሕይወትን የሚያስገኝ መሆኑን አምነው የዘላለም ሕይወት ያሰጠኛል ብለው ለሚቀርቡ፣

«ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው እኔም በመጨረሻ ቀን አስነሳዋለሁ»።/ ዮሐ. 6÷53/

መ. በሚቀበሉት ቅዱስ ቁርባን ክርስቶስ ከእርሱ ጋር እነርሱ ከክርስቶስ ጋር አንድ ሆነው እንደሚኖሩ ሥጋው ከሥጋቸው ደሙ ከደማቸው ተዋህዶ አምላካቸው ከእነርሱ ጋር በጸጋ ተዋህዷቸው እንደሚኖር ለሚያምኑ።

«ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ» /ዮሐ. 6÷56/

በተጨማሪ በቀደመ ኃጢአታቸው ለተፀፁ ለተናዘዙ ለተመለሱ ከሚመጣው ኃጢአት ለሚጠበቁ ነው።

«ዮሐንስም አልፎ ከተሰጠ በኋላ ኢየሱስ የእግዚአብሔርን መንግስት ወንጌል እየሰበከና ዘመኑ ተፈጸመ የእግዚአብሔርም

መንግሥት ቀርባለች ንስሐ ግቡ በወንጌልም እመኑ እያለ ወደ ገሊላ መጣ::» /ማር. 1÷14/

ይህን ሁሉ እውነትና የወንጌሉን ቃል በተረትና በአጉል ባሕል እየሸፈኑ የራሳቸውን አስተሳሰብ ያስተጋቡ የነበሩ ሰዎች ሁሉ ይህንን ጺጋ የተጋፉ ናቸው እንግዲህ ቅዱስ ቁርባን ለማን ለሚለው ከላይ የቀረበው ማብራሪያ የማያንስ ቢሆንም በምዕመናን ውስጥ ለሚነሱ ልዩ ልዩ ጥያቄዎች ከዚህ በታች በርዕስ በርዕስ ማብራሪያ እናቀርብበታለን::

## ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል የተወሰነ እድሜ አለን?

ብዙ ጊዜ ህፃናት እስከ ሰባት ዓመት ሲያቆርቡ ኖረው ከዚህ እድሜ ሱገፋ ወንዱን «ለአቅመ አዳም» ደርሰሀል መቁረብ አይገባህም ሴቷን «ለአቅመ ሔዋን» ደርሰሻል መቁረብ አይገባሽም የሚለውን አባባል በአንዳንዶች ዘንድ ከአባበል አለፎ እንደ ቀኖና /ህግ/ ተወስዷል:: ወጣቶች በእድሜያቸው /በወጣት ነታቸው/ ምክንያት ብቻ ወደ ቁርባን መቅረብ እንደሌለባቸው ሲነገርባቸው እንሰማለን::

ራሳቸው ወጣቶች በዚህ ሰው ሰራሽ ትምህርትና ተራ አባባል ታምነው «ለአቅመ አዳም» «ለአቅመ ሔዋን» ደርሻለሁ ወደ ቁርባን መቅረብ አይገባኝም ሲሉ ይደመጣሉ::

የሚገርመው ወጣትነትን በራሱ ብቻ እንደ ኃጢአተኝነት ወይም ለቅዱስ ቁርባን ብቃት የሌለው ሕይወት አድርጎ መውሰድ በራሱ ትልቅ ስህተት ነው:: እንዲህ አይነቱን አባባል የሚቀበሉና እንዲህ አይነት አስተሳሰብ ያላቸው ሰዎች ወጣቶች ወደ ሥጋ ወደሙ መመለስ የሚገባቸው በስተርጅና /አይን ሲፋዝ ጉልበት ሲደነዝዝ/ እንደሆነ ይስማማሉ:: ይህንም አስተሳሰብና አባባላቸውን ለማጠናከር የሚጠቀሙበት ቢሂል አለ እርሱም «ጣጣውን ሲጨርስ /ስትጨርስ/ የሚሉት ነው::





እዚህ ላይ ለአንባብያን ላስገነዝብ የምወደው እነዚህ ሰዎች በራሱ ኃጢአት «ጣጣ» መሆኑን መመስከራቸውን ወይም መንፈስ ቅዱስ እንዳስመሰከራቸው ልብ እንድትሉት ነው::

ታዲያ በዚህ አባባል ሰው ኃጢአትን ሲሠራ እንዲኖር ወይም ኃጢአት ለመሥራት ተስማማው እድሜ ይህን ወጣትነት አድርጎ እንደ መመደብ የሚቆጠር አባባል ነው::

ለሁሉም መልሱን የሚሰጠው የወንጌሉ ቃልና የቤተ ክርስቲያኒቱ ህግና ሥርዓት ስለሆነ ከዚህ በታች በአጭሩ እንመልከት::

ታላቁ ሰው ንጉሱና ነብዩ ሰሎሞን «በጉብዝናህ ወራት ፈጣሪህን አስብ» /መክ. 12÷1/ በማለት ሰው በጉብዝናው እድሜ ራሱን ለአምላኩ እንዲያቀርብ በቅዱስ ቃሉ ይጣራል ቤተ ክርስቲያኒቱም ብትሆን መሥዋዕቱ በሚለወጥበት በታለቁ ጸሎት /በጸሎተ ቅዳሴው/ ለተዘጋጀውና ለቀረበው የሕይወት ማዕድ ምዕምናኗን ስታዘጋጅ ካህኑ የሚለው «በወጣትነት እድሜ ያላችሁ አትቅረቡ» ሳይሆን «ንጹህ ያልሆነ ግን አይቅረብ» ነው እንግዲህ ባጠቃላይ ከነቢያት ወገን ወጣቶች እሉ እግዚአብሔር እነ ሶምሶንን እነ ጌድዩንን ለሚፈልገው አምላካዊ ዓላማው የጠራቸው በጉብዝና እድሜያቸው ነው:: ጌታ የቁርባንን ሥርዓት ሲሠራ ከነበሩት ከአስራ ሁለቱ ደቀ መዛሙርት ወጣቶች ነበሩበት በየትኛውም እድሜ ለሚገኙ ክርስቲያኖች ኃጢአት የሚሰሩበት እድሜ ስላልተመደበላቸው ወደ ቅዱስ ቁርባን ለመቅረብና ላለመቅረብ የተመደበም እድሜ የለም ወደ ሕይወት እንጀራ ወደ ሥጋ ወደሙ ለመቅረብ መስፈርቱም እድሜ ሆነ መወሰድ የለበትም::





## ቅዱስ ቁርባን መቀበል
## የማይገባቸው እነማን ናቸው?

ይህን ርዕስ ሥጋ ወደሙ ለማን? የሚለው ርዕስ በከፊሉ የሚዳስሰው ቢሆንም በራሱ ቁም ነገር የሚያስጨብጥ ሆኖ ስላገኘሁት በአጭሩ ከዚህ በታች ማብራሪያ አቅርቤበታለሁ::

በመሠረቱ ቅዱስ ቁርባን ለሰው ልጆች መዳን የተሰጠ ጺጋ ቢሆንም ወደዚህ የሕይወት እንጀራ መቅረብ የማይገባቸው አሉ፡ ክርስቶስን በወቅቱ ማን እንደሆነ ያላወቁና የተቃወሙ እንዳሉ ሁሉ የቅዱስ ቁርባን ምስጢር የልገባቸውና ለቅዱስ ቁርባን ተቀራኒ ሕይወት ያላቸው ናቸው እነዚህም፣

ሀ. በልዩ ልዩ የክህደት ጐራ የተሰማሩና ወንጌል ያልደረሳቸው በክርስቶስ የማያምኑ አምነውም ያልተጠመቁ::

«ኢየሱስም መለሰ እንዲህ ሲል እውነት እውነት እልሃለሁ ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም::» /ዮሐ. 3÷5/

ለ. ሕብስቱ ተለውጦ ሥጋ አምላክ ወይኑ ተለውጦ ደመ አምላክ መሆኑን ያላመኑ አምነው የሚጠራጠሩ::

«ኢየሱስም ስለ አየኸኝ አምነሃል ሳያዩ የሚያምኑ ብፁአን ናቸው» አለው:: /ዮሐ. 20÷29/

ሐ. ቅዱስ ቁርባን ኃጢአትን የሚያስተስርይ መሆኑን ያልተረዱና በተለይ ቅዱስ ቁርባን የሚዘጋጀው ለጻድቃን ሳይሆን ለኃጥአን እንደሆነ ያልገባቸው::

«የሰውን ልጅ የጠፋውን ሊፈልግና ሊያድን መጥቶአልና አለው» /ሉቃ. 19÷10/





መ. በቅዱስ ቁርባን የዘላለም ሕይወት የሚገኝ መሆኑን ተምረው ያላወቁ አውቀውም ለዚህ ጺጋ መንፈሳዊ ፍላጐት ጉጉት ለሌላቸው

«ኢየሱስም እንዲህ አላቸው የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ ወደ እኔ የሚመጣ ከቶ አይራብም በእኔ የሚያምንም ሁልጊዜ ከቶ አይጠማም::» /ዮሐ. 6÷35/

«በእውነት አምነው ከርሱ ለሚቀበሉ ሕይወትና መድኃኒት የኃጢአት ማስተስርያም ሊሆን የሚሰጥ የጌታችንና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ደም ይህ «እማሬ» ነው:: /ቅዳሴ ሐዋርያት/

ሠ. ከኃጢአታቸው ያልተመለሱ ያልተጸጸቱ ያልተናዘዙ በማን አለብኝነት ለመቀበል የሚፈለጉ በሰሩት ኃጢአት ንስሀ ያልገቡ

«አሁንስ ይላል እግዚአብሔር በፍጹም ልባችሁ በጾምም በልቅሶና በዋይታ ወደ እኔ ተመለሱ::» /ት.ኢዩ. 2÷12/

«ኃጢአታችሁ ይደመሰስ ዘንድ ንስሀ ግቡ ተመለሱም» /ሐዋ. 3÷20/

ረ. ቆራቢ ለመባል ለታይታ ለከንቱ ውዳሴ ሰው ይየኝ ብለው ለመቁረብ የሚፈልጉ ግብዞች

«ለሰዎች ትታዩ ዘንድ ምጽዋታችሁን በፊታቸው እንዳታደርጉ ተጠንቀቁ ያለዚያ በሰማያት ባለው አባታችሁ ዘንድ ዋጋ የላችሁም» /ማቴ. 6÷1/

ሰ. የቅዱስ ቁርባን ጸጋና ምስጢር ሳይገባቸው ባልንጀሮቻችውን አይተው እንመሳሰል ብለው ለመቀበል የሚፈልጉ

ሸ. የመናፍቃን ትምህርት የበረዛቸው የሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት ቅዱስ ቁርባን አማናዊ /እውነተኛ/ አይደለም መታሰቢያ ነው እንጂ የሚሉ

ቀ. መስለው ገብተው የክርስትናን ኃይማኖት የክርስቶስን ቤተ ክርስቲያን እናፈርሳለን ብለው ቅዱስ ቁረባንን እንይ ምስጢሩንም እናውጣ ብለው ለመቀበል የሚፈልጉ፡፡

«ከውሾች ተጠበቁ ከክፉዎች ሠራተኞች ተጠበቁ ከሐሰተኞችም መገረዝ ተጠበቁ» /ፊልጵ. 3፡2/

በ. ያለ እምነት በድፍረት ያለ ንስሀ በኃጢአት መሥዋዕቱን በመናቅ እንደ ምድራዊ ማዕድ በመቁጠር ለሚደፍሩ እግዚአብሔርን መፍራት በሕይወታቸው ለሌለ

«የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» /ምሳ. 1፡7/

እንግዲህ በነዚህ በተዘረዘሩና በሌሎች ምክንያት ቅዱስ ቁርባንን ሳይገባቸው በድፍረት የሚቀበሉ ቢኖሩ ስለ በረከት ፈንታ መርገምን ስለ ሥርየት ኃጢአት ፈንታ ገሀነመ እሳትን ከክርስቶስ ዘንድ ይቀበላሉ፡፡

## ባልና ሚስት ተነጣጥለው ቢቆርቡስ?

«ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ወደዚህ ነይ» /ዮሐ. 4÷16/

ይህንን የጌታችንን ቃል አስተውላችሁት ታውቃላችሁ? ውሃ ለመቅዳት የመጣችው ሳምራዊቷ ሴት «ጌታ ሆይ እንዳልጠማ ውኃም ልቀዳ ወደዚህ እንዳልመጣ ይህን ውሃ ስጠኝ» ባለችው ጊዜ «ሂጂና ባልሽን ጠርተሽ ነይ» ብሎ መለሰላት፡፡ በዚህ ቃል መሠረትነት ነው ቤተ ክርስቲያን ባልና ሚስት ተነጣጥለው መቁረብ የሌለባቸውም የምትለው፡፡





ለዚህ ጥያቄ በቂ መልስ ለማግኘት ለአንባብያን ተጨባጭ ማስረጃ ለማቅረብ በጋብቻ ዙሪያ የእግዚአብሔር ቃል ምንድን እንደሚል መመልከት አስፈላጊ ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡

«...ፈጣሪ በመጀመሪያ ወንድና ሴት አደረጋቸው አለም ስለዚህ ሰው አባቱንና እናቱን ይተዋል ከሚስቱም ጋር ይተባበራል ሁለቱም አንድ ሥጋ ይሆናሉ የሚለውን ቃል አላነበባችሁምን ስለዚህ አንድ ሥጋ ናቸው እንጂ ወደ ፊት ሁለት አይደሉም እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው» /ማቴ. 19÷4-6/

በዚህ አምላካዊ ቃል መሰረት ባልና ሚስት አንድ ሥጋ ናቸው፡፡ ጋብቻ ከልዑል እግዚአብሔር ዘንድ ለሰው ልጆች ከተሰጡ ታላላቅ ስጦታዎችና በረከቶች አንዱና የመጀመሪያው ነው፡፡

ገና መጀመሪያ እግዚአብሔር አምላክ ከምድር አፈር አዳምን አበጅቶ በአፍንጫው የሕይወትን እስትንፋስ እፍ ብሎ ህያው ካደረገው በኋላ ስለ አዳም አስቦ ያለው እንዲህ ነበር

«አዳም /ሰው/ ብቻውን ይኖር ዘንድ መልካም አይደለም የምትረዳውን እንፍጠርለት» /ዘፍ. 2÷18/ በዚህ መሰረት ከአዳም አጥንት ነስቶ ሔዋንን ፈጠረለት አዳምም ከአካሉ የተፈጠረችውን ሴት ተመልክቶ እንዲህ አለ፣

«ይህች አጥንት ከአጥንቴ ይህች ሥጋ ከሥጋዬ ናት እርስዋ ከወንድ ተገኝታለችና ሴት ትባል» /ዘፍ. 2÷23-25/

ደግሞም ጋብቻ በረከት ሆኖ ለሰው ልጆች እንደተሰጠ እንዲህ ተፅፏል «እግዚአብሔር እምላክ ሰውን በመልኩ ፈጠረ ወንድና ሴት አድርጐ ፈጠራቸው፡፡ ከዚያም እንዲህ ብሎ ባረካቸው «ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት ግዙአትም የባሕርን ዓሶችና የሰማይን ወፎች በምድር ላይ የሚንቀሳቀሱትንም ሁሉ ግዙአቸው» /ዘፍ. 1÷26-31/

መድኃኒተዓለም ኢየሱስ ክረስቶስ ከድንግል ማርያም ተወልዶ በዚህች ዓለም ወንጌለ መንግስቱን በሚሰብክበት ጊዜ





ጋብቻ እጅግ የተቀደሰ ባልና ሚስትም አንድ ሥጋ መሆናቸውን አስተምራል እንዲህ ብሎ፣

«እግዚአብሔር ያጣመረውን እንግዲህ ሰው አይለየው» /ማቴ. 19÷6/

አምላካዊ ቃሉ እንዲህ እያለ አንድ ሥጋ በሆኑ ባልና ሚስት መካከል ተነጣጥሎ መቁረብ ለምን ታሰቦ? ለመቁረብ እንቢ በሚለው ሰው ውስጥ ያለው ምክንያት ምንድን ነው? የሚሉትንና የመሳሰሉትን ጥያቄዎች እንድናነሳ ያደርገናል በቅድሚያ አልቆርብም ባዩ ሰው በኃጢአት የመኖር እቅድ እንዳለውና የሚያስጠይቀውም መሆኑ ግልጽ ሲሆን በቃሉ መሠረት ግን ተነጣጥሎ መቁረብ ተገቢ አይደለም የቤተ ክርስቲያን ህግና ሥርዓትም አይፈቅደውም ምክንያቱም አንዱ ሲቆርብ ሌላው ሲቀር አንድ ሥጋ ተለያየ ማለት ነው፡፡ ሌላው በቅዱስ ቁርባን የአንዱ ሕይወት የተቀደሰ ከቅዱስ ቁርባን የራቀው የአንዱ ሕይወት ያልተቀደሰ በመሆኑ በግንኙነት ጊዜ የተቀደሰው ሕይወት ይረክሳል ቅዱስ ጳውሎስ ስለዚህ እንዲህ አለ፣ «ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆነ አታውቁምን ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሁናሉ ተብሎአልና» /1ቆሮ. 6፡15-16/

ይሁንና ሁለቱም በመስማማት በመምህረ ንስሐቸው ምክር በመመራት አንዴ ከቆረቡ በኋላ /ቆራቢ ከሆኑ በኋላ/ ግን በተለያየ ምክንያት ለምሳሌ በሥራ ጉዳይ በመራራቅ፣ ሴቷ/ሚስቲቱ/ ሥርዓተ አንስት ላይ በመሆን/በወር አበባዋ ጊዜ/፣ ወልዳ በምትታረስበት ጊዜ ወንዱ/አንዱ/ መቁረብ ቢፈልግ ቢቆርብ እንደመለያየት የሚቆጠር አይደለም ምክንያቱም ሁለቱም ቆራቢዎች ናቸው ይህ የመነጣጠል ጉዳይ ሳይሆን በቀን ልዩነት የመቀበል ሁኔታ ነው ነገር ግን በተቀበሉ ቀን አብሮ መተኛት የተከለከለ ሲሆን ከዚያም በኋላ በልዩ ምክንያት ሳይቀበል የቀረው ሁኔታዎች ሲስተካከሉ ተዘጋጅቶ በመቀበል ሊቀጥሉ ይችላሉ በተረፈ እንዲህ አይነት ምክንያቶች ካላጋጠሙ በስተቀር የመጀመ





ሪያ ቀን በአንድነት በአንድ ቀን እንደተቀበሉ ሁል ጊዜ በአንድ ቀን መቀበላቸው ለፈተና ከመጋለጥ ይጠብቃቸዋል፡፡ /1ቆሮ. 7÷5/

## ያላገባ ወጣት መቁረብ ይችላል?

ለዚህ ርዕስ በቂ ማብራሪያ ለአንባብያን ከማቅረቤ በፊት አንድ ነጥብ አስቀድሜ ልገልጽ እወዳለሁ፡፡

ይኼውም ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል በራሱ ያገባ ወይም ያላገባ ብሎ እንደ መስፈርት መውሰድ ትልቅ ስህተት መሆኑን፡፡ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የሞተ ለሁሉ ነው ስለዚህ አምነው በተጠመቁና ለቅዱስ ቁርባን በተዘጋጁ መካከል «የማግባትና ያለማግባት»፣ «የዘርና የቀለም»፣ «የጾታና የዕድሜ»፣ ልዩነትን እንደመመዘኛ የሚወስድ ካለ ትልቅ ስህተት ውስጥ ገብቷል፡፡

«በአይሁዳዊና በግሪካዊ ሰው መካከል ልዩነት የለምና አንዱ ጌታ የሁሉ ጌታ ነውና» /ሮሜ. 10÷12/

በማለት ቅዱስ ጳውሎስ ለሮማውያን ክርስቲያኖች የጻፈላቸው ይህን ያረጋግጥልናል፡፡

በተረፈ የዚህ ርዕሳችን መሠረታዊ ነጥብ ግን ይህ ነው ማንኛይቱም ኦርቶዶክሳዊት ሴት ከልጅነቷ አንስቶ እስክታገባ ድረስ ካገባችም በኋላ ከሕግ ባሏ ጋር በአንድነት እስከ እለተ ሞቷ ድረስ ስትቀበል መኖር ይገባታል እንደዚሁ ወንዱ ከልጅነት አንስቶ የህግ ሚስቱን እስካገባበት ቀን ድረስ ካገባም በኋላ ከህግ ሚስቱ ጋር እስከ እለተ ሞቱ ድረስ ቅዱስ ቁርባን በመቀበል ሊኖር ይገባዋል፡፡

## ቆራቢ የሆነ ሰው የትዳር ጓደኛውን በሞት ቢያጣ ደግሞ ሴሳ ማግባት ይችላል?

በሥጋ ወደሙ /በቅዱስ ቁርባን/ ተወስነው ከሚኖሩ ባልና ሚስት መካከል አንዱ በሞት ከዚህ ዓለም በሞት ቢለይ ቀሪው ሊያገባ አይችልምና የሚል አባባል የተለመደ ሲሆን ከዚህ የተነሳ በአማኙ መካከል ብዙ ጥያቄ ያስነሳል::

በቅድሚያ በዚህ ውስጥ ሊገለጥ የሚገባው ስለሟች ድህነት ሲሆን ሟቹ ከህግ የትዳር ጓደኛው ጋር ጸንቶ የክርስቶስን ሥጋን ደም ሲበላና ሲጠጣ /በቅዱስ ቁርባን ተወስኖ/ በመኖር ለድህነቱ ዋስትና ይዟልና የዘላለም ሕይወት ባለቤት ነው «ሥገዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው እኔም በመጨረሻ ቀን አስነሳዋለሁ» /ዮሐ. 6÷53/

ጌታችን ይህን የጠቀስነውን ቃል የተናገረውም ይህንኑ ለማረጋገጥ ነው በክርስቶስ ወንጌል ለሚያምንና የተናገረውን እንደማያስቀር ተስፋ ለሚያደርግ ይህንን እውነት ሊቃወምና በዚህ ቃል ሊጠራጠር አይገባውም «የዘላለም ሕይወት አለው» የሚለው ቃል የእራሱ ሁሉን ማድረግ የሚችለው የክርስቶስ ቃልና ቃሉም የሚፈጸምና ነብዩ ኢሳይያስ እንደተናገረው ሥራ ሳይሰራ የማይመለስ ቃል ነው:: /ኢሳ. 55÷11/

ይሁንና የትዳር ጓደኛው የሞተበትን ሰው ከሟች የትዳር ጓደኛው ጋር ሲቆርብ በመኖሩ ብቻ ሊያገባ አይችልም ብሎ መወሰን አይቻልም በቤተ ክርስቲያንም እንደ ህግ ወይም እንደ ሥርዓት በዚህ ጉዳይ የሚከለክል ትምህርት የለም::

የትዳር ጓደኛው የሞተበት ቆራቢ ምዕመን ከሆነ በፈቃድ «ወንዱ ከሴት እርቆ ንጽህ ጠብቆ»፣ «ሴቷ ከወንድ እርቃ ንጽህ ጠብቃ»፣ ለመኖር እንጂ ለማግባት ባይፈልጉ ፈቃዳቸው አይከለከልም መልካምም አድርገዋል ቅዱስ ጳውሎስ «ነገር ግን ያለ አሳብ ልትኖሩ እወዳለሁ ያላገባው ጌታን እንዴት ደስ እንዲያሰኘው





የጌታን ነገር ያስባል» በማለት ለቆሮንቶስ ምዕመን ጽፎላቸ ዋል /1ቆሮ. 7÷32/

በሌላ መልኩ ግን ቀሪው ማግባት ቢፈልግ አይከለከልም ወንዱ ቆራቢዋን ፈልጎ ወይም በድንግልና የኖረችዉን በንጽህና የምትመላለሰውን አጭቶ ወደ ቆራቢነት ሕይወት አድርሶ ሊያገባ ይችላል ሴቷም እንዲሁ ልታገባ ትችላለች በዚህ ዙሪያ ሐዋርያው ጳውሎስ የተብራራ መልዕክት ጽፎልናል እንዲህ በማለት «ሴት ባልዋ በሕይወት ሳለ የታሰረች ናት ባልዋ ቢሞት ግን በጌታ ይሁን እንጂ የወደደችውን ልታገባ ነጻነት አላት:: እንደ ምክሬ ግን እንዳለች ብትኖር ደስተኛ ናት እኔም ደግሞ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ያለ ይመስለኛል::» /1ቆሮ. 7÷39-40/ /ይህ ቃል ለወንዱም እንዲሁ ነው/

## ህፃናትን ማቁረብ

«ልጆች የእግዚአብሔር ስጦታዎች ናቸው» /መዝ. 126÷3/

ቤተ ክርስቲያን ህፃናትን ካጠመቀች በኋላ እንደሌሎች ወደ ቤታቸው እንዲሔዱ አታደርግም ወዲያውኑ የክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደም ታቀብላቸዋለች ከዚያን ጊዜ ጀምሮ ከእግዚአብሔር ዘንድ እነዚህን ታላቅ ስጦታዎች /ልጆች/ የተቀበሉ ወላጆች እየተከታተሉ በማቁረብ ያሳድጓቸዋል ከፍ ሲሉም እያስተማሩም እንዲቀበሉ ያደርጓቸዋል::

ሕፃናትን በማጥመቅና በማቁረብ ዙሪያ ጌታችን «ያመነ የተጠመቀ ይድናል» በማለት የተናገረውን በመንተራስ ኘሮቴስታ ኖች ከማጥመቅ ይልቅ እምነት ይቀድማል በማለት ሕፃናትን ማጥመቃችን ስህተት እንደሆነ ይናገራሉ በማቁረባችንም አንዳን ዶች ይህንን ይጠቅሳሉ ብዙዎችም መሰረታዊ ጥያቄ የሚያደርጉት ጥምቀት ቁርባን ያለ እምነትና እውቀት እንዴት ይከናወናል? ሀፃኑ እምነትም ሆነ እውቀት ሊኖረው አይችልም የሚል ነው::





እኛ ግን የምናስበው ስለ ሕፃናት ሰማያዊ ሕይወት ነው ይኸውም ጌታችን «ከውሃና ከመንፈስ ያልተወለደ የእግዚአብሔርን መንግስት ሊያይ አይችልም» /ዮሐ. 3÷5/ «ያላመነ ያልተጠመቀ አይድንም» /ማር. 16÷16/ «ሥጋዬን ያልበላ ደሜን ያልጠጣ የዘላለም ሕይወት የለውም» /ዮሐ. 6÷53/ በማለት ለሰው ልጅ ድህነትን ሊያስገኙ ወይም ድህነቱን ሊያሳጡ የሚችሉ ነገሮችን ስለተናገረ ነው እንዲህ ከሆነ ስለምን ሕፃናትን አናጠምቅም አናቆርብም? ስለምንስ ለእግዚአብሔር ፍርድ አሳልፈን እንሰጣቸ ዋለን? ጌታችን የጠቀስኳቸውን ኃይለ ቃላት ሲናገር ሕፃናትን አልተዋቸውም ወይም በሌላ አባባል «ከህፃናት በቀር» አላለም አልያም ህፃናት ስለሆኑ ለእግዚአብሔር ማንነታቸው አይጠፋም ነቢዩ ኤርሚያስን ለአገልግሎት ሲጠራው ዛሬ ሳይሆን በእናትህ ማህፀን ሳልሰራህ አውቅሀለሁ አለው ይህንንም ነገር ነቢዩ ሲመሰክር «የእግዚአብሔር ቃል ወደ እኔ እንዲህ ሲል መጣ በሆድ ሳልሠራህ አውቄአለሁ ከማህፀንም ሳትወጣ ቀድሼሃለሁ ለአሕዛብም ነብይ አድርጌአለሁ» /ኤር. 1÷4-5/ ብሏል::

ሕፃናት በመጠመቃቸው የቤተክርስቲያንን ሕይወት ይለማመዳሉ በቅዱስ ቁርባንም መንፈሳዊ ጥቅምና የሰማያዊውን ምስጢር በረከት ያገኛሉ ከቤተክርስቲያን ካገለልናቸውና ከሚስጢራት ከከለከልናቸው እምነትንና የጸጋ ምክንያቶችንም መከልከላችን ነው:: ጌታችን ስለ ሕፃናት እንዲህ አለ «ሕፃናትን ተውአቸው ወደ እኔም ይመጡ ዘንድ አትከልክሏቸው መንግሥተ ሰማያት እንደነዚህ ላሉት ናትና» /ማቴ. 19÷14/

ህፃናትን ከማጥመቅም ሆነ ከሌሎች ከሚገባቸው ምስጢራት የሚከለክል አንድ ጥቅስ እንኳን በመጽሐፍ ቅዱስ የለም እንዲያውም በመጽሐፍ ቅዱስ የሙሉ ቤተሰብን መጠመቅ ወይም አንድ ሰው ራሱን ቤተሰቡን ሁሉ ሲጠመቁ ተጽፏል:: ታዲያ በነዚህ ቤተሰቦች ሕፃናት እንደነበሩ ምንም ጥርጥር የለውም





1. የወህኒ ጠባቂው ከነቤተሰቡ ተጠመቀ /ሐዋ. 16÷32/
2. ቀይ ሐር ሻጭዋ ሊዲያ ከነቤተሰቧ ተጠመቀች /ሐዋ. 16÷15/
3. የእስጢፋኖስ ቤተሰብ ተጠመቁ /1ኛቆሮ.1÷16/
4. በዕለተ ጴንጤ ቆስጤ ብዙዎች ተጠመቁ

እንደዚህ ከነቤተሰቦቻቸው ስለተጠመቁ ሰዎች በተፃፈው በጠቀስኳቸው ጥቅሶች «ከህፃናት በቀር» አልተባለም ቤተሰብም የሚለው ቃል ልጆችን ሁሉ ሊያጠቃልል እንደሚችል የሚያጠራጥር አይደለም ወይም ህፃናት አለመኖራቸው ተለይቶ አልተጠቀሰም በታሪክም ህፃናትን ማጥመቅ ተጽፎ ይገኛል::

የኦሪት ግዝረት የጥምቀት ምሳሌ ነው የተገረዘው ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር ይቆጠሩ ነበር:: ኪዳኑ ግን የተሰጠው ለአብርሃም ነው /ዘፍ. 7÷11/ ግዝረት ግን የሚደረገው ህፃኑ ከተወለደ በ80 ቀን መሆኑ የታወቀ ነው ታዲያ በአብርሃምና በእግዚአብሔር መካከል ስላለው ኪዳን የ80 ቀን ህፃን ምን ያውቃል? ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር አንድነት መደመሩንስ ያውቃልን? ስለተሰጠው ተስፋ ምን ያውቃል?

እንደደመና ዙሪያችንን የከበበን ምስክር ካልሆንን ህፃኑን በማቁረባችን መች አመነና ምኑን ያውቀዋል የሚለው ጥያቄ ከሰዎች የሥጋ አስተሳሰብ የሚፈልቅ ጥያቄና ፍልስፍና ስለመሆኑ አያጠራጥርም::

ስለዚህ ህፃኑን ለቅዱስ ቁርባን ማዘጋጀቱና ከቆረበም በኋላ አስፈላጊውን ክትትል ጥበቃ ማድረግ የወላጆቹና የመንፈሳውያን አገልጋዬች ግዴታ ነው::

ብዙ ጊዜ ወላጆች ክትትል ባለማድረጋቸው ልጆች ከቅዱስ ቁርባን እርቀው ሲያድጉና እያደጉም ሲሔዱ በንጹህ አእምሮአቸው ላይ የሚቀበሉት ምን እንደሆነና ስለ መንፈሳዊ ጥቅሙ ሊቀርጹባቸው ሲገባ ማቁረቡን እንጂ ማስተማሩን ችላ ሲሉት ይስተዋላል ይህ ደግሞ ህፃኑ ካደገ በኋላ በራሱ ለቅዱስ ቁርባን ፍቅር እንዳይኖረውና ማድረግ ያለበትን እንዳያውቅ ስለሚያደርግ በሚገባው ቋንቋ እያስተማሩ ማቁረብንና ማሳደጉን መዘንጋት የለበትም::

ገፅ 12



# ምዕራፍ ስድስት

## ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል የሚደረግ ዝግጅት

«ቅዱስ ቁርባንን ለመቀበል የሚደረገውን ዝግጅት በሁለት ከፍለን እንመለከተዋለን

ሀ. ውሳጣዊ ዝግጅት /የመንፈስ ዝግጅት/
ለ. አፍአዊ ዝግጅት /የሚታይ ውጫዊ ዝግጅት/

ሀ. <u>ውሳጣዊ ዝግጅት</u> የምንለው ቆራቢው ያለውን እምነትና የመንፈሱን ዝግጅት ያመለክታል በቅዱስ ወንጌል ወደ ክርስቶስ ቀርበው በፊቱ ለቀረበለት የእምነት ልመና «እምነትሽ ታላቅ ነው እንደወደድሽ ይደረግልሽ» /ማቴ. 15÷28/ የሚል መልስ ደጋግሞ ይመልስ እንደነበር ተጽፎ እናገኛለን::

ስለዚህ አማኙ ወደ ቅዱስ ቁርባን ሲቀርብ በውስጡ የተዛባ እምነት እንዳይኖረው ሊጠነቀቅ ይገባዋል የምቀበለው አማናዊውን በምሴተ ሐሙስ ለደቀ መዛሙርቱ የሰጣቸውን በዕለተ አርብ በቀራንዮ መስቀል ላይ ለድህነተ ዓለም የቆረሰውን ቅዱስ ሥጋና ክቡር ደሙን ነው:: በዚህ ለሠራሁትና ንስሐ ለገባሁበት ኃጢአት ስርየት አገኛለሁ፣ ከሚመጣ ኃጢአት የምጠበቅበት ኃይል አገኛለሁ፣ ክርስቶስ በእኔ እኔ በክርስቶስ እኖራለሁ፣ የዘላለምን ድህነት አገኛለሁ፣ ከደዌ ሥጋ ከደዌ ነፍስ እጠበቃለሁ፣ እያለ በፍጹም እምነት ሊዘጋጅና የተቀበለውን ከኃጢአት ርቆ በንጽህና ሊጠብቅ በእምነት መዘጋጀት ይኖርበታል::

ለ. <u>አፍአዊ ዝግጅት</u> ይህ አይነት ዝግጅት መሠረቱና ምንጩ ከላይ የጠቀስነው እምነት ሆኖ አማኙ ለሚቀበለው መለኮታዊ ሥጋና ደም ያለውን እምነት አክብሮት የሚገልጽበትና እንደ ማንኛዉም ምድራዊ ማዕድ እንዳልቆጠረው የሚመሠክርበት ጭምር ነው ይህም በቤተክርስቲያኗ የሥርዓት መጽሐፍ ላይ





ለምእመናኗ ተደንግጐ የምናገኘው ሲሆን አልፎ አልፎ አንዳንድ ሰዎች በዘልማድ የሚናገሩት ነገር እንደ ህግ ተወስዶ ተደባልቆ አማኙን ግራ ሲያጋባው ይስተዋላል በዚህ ክፍል ይህንን ለይተን በመግለጽ ለማሳወቅ እንወዳለን::

## ለመቀበል የሚያስፈልግ ግዴታና ጥንቃቄ

አማኙ ቅዱስ ቁርባን ለመቀበል የሚያስፈልገው ግዴታ ሕይወተ ሥጋወነፍስ አገኝበታለሁ ብሎ እስከመጣና የሚቀበለው አማናዊውን የክርስቶስን ሥጋና ደም እንደሆነ እስካመነ ድረስ መሥዋዕቱን ሰውታ በማቅረብ ወደ ሕይወት ግብዣ የጠራችውን ቤተክርስቲያን ትዕዛዝ መስማትና የደነገገችውን ሥርዓት መጠበቅና ማክበር ወደ ቅዱስ ቁርባን ለመቅረብ የሚያስፈልገው እምነታዊ ግዴታው ነው:: ከምን አለበትን ከግዴለሽነት እንዲርቅ መንፈሳዊ ግዴታውን መወጣቱ የሚቀበለው የክርስቶስ ሥጋና ደም እንደሆነ እንዲለይና ለፍርድ ከመብላትና ከመጠጣት እንዲድን ያደርገዋል ቅዱስ ጳውሎስ «ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና» /1ቆሮ. 11÷26/ በማለት ይህን ታላቅ መልዕክት ጽፏል::

ሌላው ነጥብ ደግሞ አማኙ ለመቀበል የሚወስደው ጥንቃቄ ሲሆን ይህ ከላይ አፍአዊ ዝግጅት ብለን እየተንደረደርን ያለንበት ነጥብ ነው ይህንን ለመቀበል የሚደረግ ጥንቃቄ ወይም ዝግጅት ከተቀበሉ በኋላ እስካለው ሕይወት ድረስ በሦስት ክፍል ከፋፍዬ አቀርበዋለሁ::

### ሀ. ከመቅረብ በፊት

አማኙ ወደ ቅዱስ ቁርባን ከመቅረብ በፊት ሊያደርጋቸው የሚገቡ ዝግጅቶች መንፈሳዊ ጥንቃቄዎች ይባላሉ እነዚህም ከዚህ በታች በዝርዝር ቀርበዋል::





ሀ. የሚቆርቡ ቅዱስ ቁርባን የሚቀበሉ ሰዎች በጋብቻ ሥርዓት የሚኖሩ ከሆነ ከመቁረባቸው በፊት 3ቀን ከሩካቤ ሥጋ መከልከል ይገባቸዋል:: ይህ ግንኙነት ኃጢአት ሆኖ ሳይሆን ግብረ ሥጋ /የሥጋ ሥራ/ ስለሆነ ለተቀበሉት ክብር ነው::

ለ. ማንኛውም ሰው ስለሚያውቀው ኃጢአት ተናዝዞ ስለማያውቀው ይቅር በለኝ እያለ ከኃጢአቱ ነጽቶ ልቡን ከቂም በቀል ሰውነቱን ከበደል ማራቅ ይገባቸዋል::

ሐ. ሥጋ ወደሙ ለመቀበል 18 ሰዓት ከእህል ከውሃ ተከልክሎ በመጾም አፍን ምሬት እስኪሰማው የበሉት ከሆድ እስኪጠፋ መቆየት ይገባል /ፍት.መን 13 ረስጠብ 46/

መ. ወንድ ዝንየት /ርስሐት/ /ህልመ ሌሊት/ ካገኘው በዚያ ቀን አይቆርብም ካህን ቢሆን እንኳ በሚቀድስበት ቀን እንቅፋት ቢያገኘው ማለት ነስር፣ ትውኪያ፣ ብስና፣ ማንኛውም የአካል መድማት መቁሰል ወደ አፍ የሚገባ እንደ ትንኝ ዝምብ ይህን የመሰለ ሁሉ ቢያጋጥመው በዚያን ዕለት መቀደስ፣ መቁረብ አይገባውም ይህ ለካህን ብቻ ሳይሆን ምዕመናንንም የሚመለከት ነው::

ሠ. በመቁረብ ዋዜማ ገላን መታጠብ የሚለብሱትን ንጹህ አድርጐ ማዘጋጀት ይገባል::

ረ. ቅዳሴ ከመገባቱ አስቀድሞ ከቤተክርስቲያን መገኘትና በሚገባ ሆኖ ቅዳሴውን ማስቀደስ ቅዳሴ ሲገባ ያልነበረ በመሃል የመጣ ሰው መቁረብ አይገባውም::

ሰ. ሴት በወር አበባ ላይ እስከ 7 ቀን መቁረብ አይገባም ከዚያ ሰውነቷን ታጥባ ትቀበላለች፣ በወሊድ ጊዜ ደግሞ የመታረስ ጊዜዋ እስኪፈጸም ድረስ እስከ ህፃኑ ክርስትና ድረስ





አትቀበልም:: «ሴት ከወለደች 80 ቀን ወንድ ከወለደች 40 ቀን ማለት ነው» /ዘሌ. 12÷1-5/

### ለ. በመቁረብ ጊዜ

ሀ. ሃሳብን በአንድ ሰብስቦ በፊሪያ እግዚአብሔር ሆኖ መድኃኒተ ሥጋ ወነፍስ አድርግልኝ እያሉ ወደ እርሱ በመቅረቤ እድናለሁ ብለው አምነው መቀበል ያስፈልጋል::

ለ. በሚቀበሉበት ጊዜ የሚደርስና የሚጸለየውን ጸሎት በልብ እየደገሙ መቀበል ይገባል:: እንደዚሁ በመቀበል ጊዜ «በሥጋው ላይ አንድ ጊዜ አሜን በደሙ ላይ ሁለት ጊዜ አሜን» እያሉ መቀበል ይገባል:: /ቅዳሴ ሐዋርያት/

ሐ. እንደ ቤተክርስቲያን ሥርዓት የወጣውን ተራ ጠብቆ ከሊቃነ ጳጳሳት አንስቶ እስከ ዲያቆናት በማዕረጋቸው ደረጃ ይቀበላሉ ምዕምናንም እንደ ደረጃቸው ይቀበላሉ::

መ. ተቀብሎ ሲያበቁ ጠበል /ማየ መቁረር/ መጠጣት ተሐዋስያን ወደ አፍ ገብተው እንዳያውኩ አፍን መሸፈን ይገባል /ፍት.መን.13 ክርስጣ 65/

### ሐ. ከቆረቡ በኋላ

ከመቁረብ በፊትና በመቁብ ጊዜ እንደወሰዱት ዓይነት መንፈሳዊ ጥንቃቄ ከቆረቡም በኋላ መወሰድ ተገቢ ነው እነዚህም፣

ሀ. ቆራቢው ሰው በጋብቻ ሥርዓት የሚኖር ከሆነ ከቁርባን በኋላ ሁለት ቀን ከሩከቤ ሥጋ መከልከል ይገባዋል::

ገፅ 13



ለ. የቆረበ ሰው ካለመጠንቀቅ ነስር ትውኪያ የአካል መድማት መቁሰል ወደ አፍ የሚገባ እንደ ትንኝ ዝምብ ቢያጋጥመው ንስሐ ሊሰጠው ስለሚገባ ለንስሐ አባቱ መናገር ይኖርበታል ንስሐውንም ሳይፈጽም እንደገና መቁረብ አይችልም::

ሐ. ከቆረቡ በኋላ በዚያው ዕለት ወደ ፍርድ ቤት መሔድ መሟገት ክልክል ነው /ጉባኤ ኒቂያ/

መ. ከቆረቡ በኋላ በቆረቡበት ቀን ከሚስት መገናኘት፣አብዝቶ መብላት፣ መጠጣት፣ ጥፍርን መቁረጥ፣ ጠጉር መላጨት፣ መስገድና መንበርከክ ፣ ምራቅን መትፋት፣ በውሀ መታጠብ፣ ከልብስ መራቆት፣ ክልክል ነው::/ሥርዓተ ቅዳሴ ቁ166/

ሠ. ከመንፈሳዊ ሕይወት ጋር ወደሚቃረን ቦታ ከዚህ በኋላ መሔድና ለኃጢአት ከሚያጋልጥ ሁኔታ ጋር መወዳጀት ፈጽሞ ተገቢ አለመሆኑን ማወቅና ከፉውን ሁሉ መቋቋም ተገቢ ነው::

ይሁንና በዘልማድ በአባባልና አማኙ በግምት የሚጨምራቸውን ነገር ግን ስህተት የሆኑ ነገሮች መኖራቸው የማይካድ ሀቅ ነው:: ለምሳሌ የቆረበ ሰው የቀረበለትን ማስተረፍ የለበትም ጨርሶ መብላት፣ ጨርሶ መጠጣት አለበት እያሉ ማስጨነቅና ሳያውቁት አብዝቶ አይብላ መጥኖ ይብላ የሚለውን ሥርዓትና ትዕዛዝ መጋፋታቸው በተጨማሪ ከሰው አይበላም እርሱ በበላበት ሌላ አይብላ አይጠጣ የሚሉትና የመሳሰሉት ተጠቃሾች ናቸው::

ይህን ነጥብ በዚህ እያጠቃለልኩ ለአንባቢያን ለማስገንዘብ የምፈልጋቸው በሥርዓተ ቤተክርስቲያን የታዘዘ በልዩ ልዩ ምክንያቶች መቀበል የሚፈቀድላቸውና መቀበል የሚከለከሉትን ቀጥዬ እገልጻለሁ::





ሀ. ቅዳሴ ሲጀመር ያልነበረ ሰው ቅዳሴ ሲጀመር ያልነበረ ካህን እነዚህ ሁለቱ ሥጋ ወደሙ ሊቀበሉ ሊያቀብሉ አልተፈቀደላቸውም:: /ፍት.መን. 12 በስ 97/

ለ. ያላመኑ ሰዎች ሥጋ ወደሙ እንዳይቀበሉ መጠበቅና መቆጣጠር ያስፈልጋል::/ፍት.መን. 23 ረስጠብ 44/

ሐ. በንስሐ ላይ ያለ ሰው የንስሐ ጊዜውን ሳይፈጽም ለሞት የሚያበቃ ደዌ ቢታመም ሥጋ ወደሙ ከመቀበል አይከለከልም:: ሥጋ ወደሙ ተቀብሎ ከዳነም ከምዕመናን ጋር በጸሎት ይሳተፋል በንስሐ ወደ ተለዩ ሰዎች አይመለስም:: /ፍት.መን. 13 ዕንቁ 15/

መ. ካልታመመ በቀር በንስሐ ላይ ያለ ሰው የተቀበለውን ቀኖና ሳይጨርስ መቀበል አይችልም::

ሠ. ጋኔን የሚጥለው ሕመም ያለበት ሰው እረፋ የሚያስደፍቀው የሚያስተፋው ከሆነ ሥጋ ወደሙ ከመቀበል አይከለከልም:: /ፍት. መን. 13/





# ምዕራፍ ሰባት

## ከቅዱስ ቁርባን የሚያርቁ

## ስለ እምነት ምንነት ስለመረዳት

## እምነት ምንድን ነው?

እምነት የሚለው መሠረታዊ ቃሉ ግዕዝ ሲሆን የቃሉ ፍቺ ማመን መታመን ተስፋ ሐሴት ማድረግ ማለት ነው:: ማመን ደግሞ ስለ እግዚአብሔር የሰሙትን የተረዱትን እንዲሁም የተቀበሉትን ትምህርት እውነት ነው ብሎ በልብ መቀበል ነው:: መታመን ደግሞ ያመኑትን የተቀበሉትን በሰው ፊት ሳይፈሩ መመስከር ነው:: /ማቴ. 10÷23/ «በሰው ፊት የሚመሰክርልኝ ሁሉ እኔ ደግሞ በሰማያት ባለው አባቴ ፊት እመሰክርለታለሁ» እንዳለ በተጨማሪም ሰው እግዚአብሔርን ተስፋ ማድረጉ በእርሱም መደሰቱ በማያወላውል ጽኑ ውሳኔው ሲከተለው የማመኑም ውሳኔ ለሚጠይቀው ግዴታ ሲገዛና የሚጠይቀውን መሥዋዕትነት በመክፈል ከእግዚአብሔር ጋር ሕብረት ፈጥሮ በመታዘዝ ሲኖር እምነቱ ተመሰከረ ተገለጸ ማለት ነው::

በአጠቃላይ መልኩ እምነት የሰውን የውስጥ መንፈሳዊ ሕይወትን ሕልውና የሚዳስስና የሚቆጣጠር ስሜትን የሚቀሰቅስና ከተሰጡት የሚመራ ታላቅ ኃይል ነው:: እምነት ለሰው ልጆች ከተሰጡት ታላላቅ በረከቶች መሐል አንዱና ዋናው ለሌሎችም በረከቶችና ጸጋዎች መገኘት መሠረት ነው::

እንግዲህ እምነት ከላይ ከፍ ብሎ የተጠቀሰው ትርጓሜ ሲኖረው እምነት በተአማኒው ሕይወት ውስጥ የሚኖረው ተግባራዊ የሕይወት ትርጉም ከዚህ በታች የሚከተሉት ፍቺዎች ይዞ ይገኛል::





## እምነት ብርሃን ነው

ተአማኒው ሰው እግዚአብሔርን ካለማወቅ ጨለማ የሚወጣበት እምነት ብርሃን ነው:: ስለዚህ ተአማኒው ሰው ወደ እግዚአብሔር የሚደረስበት መንገድ እምነት ሲሆን እምነቱ ደግሞ የብርሃን ሕይወት ስለሆነ እምነት ብርሃን ነው:: ከላይ እንደገለፅነው ተአማኒው እምነቱን የጣለበት እምነቱን የመሠረተበት እግዚአብሔር ብርሃን ነው:: /መዝ. 26÷1/ አባታችን ቅዱስ ኤፍሬም በውዳሴ ማርያም ላይ «ብርሃን ዘበአማን ዘያበርህ ለኩሉ ሰብእ ለእለ ይነብሩ ውስተ ዓለም» በማለት ይህን ይመሰክራል ትርጓሜውም አማናዊ ብርሃን /ጠፈር የማይከለክለው የሌሊት ጨለማ የማይሸፍነው/ በዓለም ላሉት ሁሉ የሚያበራ ማለት ነው:: ሐዋርያው በመልእክቱ እንዲህ ጽፏል «ከእርሱ የሰማናት ለእናንተ የምናወራላችሁ መልእክት እግዚአብሔር ብርሃን ነው ጨለማም በእርሱ ዘንድ ከቶ የለም የምትል ይህች ናት» /1ዮሐ. 1÷5/ ወደዚህዘለዓለማዊ ብርሃን የሚጓዙበትና የሚደርሱበት ከእርሱም ጋር ሕብረት የሚያደርጉበት የሰው ልጅ የአእምሮ ብርሃን እምነቱ ነው ጨለማ በማያሸንፈው «ብርሃን ዘዘልፈ ያበርህ» ዘወትር የሚያበራ በተባለው አምላክ በመድኃኒት ዓለም በኢየሱስ ክርስቶስ ማመኑ:: ዮሐንስ በመልእክቱ «ኅብረት አለን ብለን በጨለማ ብንመላለስ እንዋሻለን:: እውነትም አናደርግም ነገር ግን እርሱ በብርሃን እንዳለ በብርሃን ብንመላለስ ለእያንዳንዳተን ኅብረት አለን» /ዮሐ. 1÷6/ በማለት ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን /ቅዱስ ቁርባን/ በሰጠን በሕይወት ብርሃን በኢየሱስ ክርስቶስ ወንጌል አምነን ብርሃን ለብሰን ብርሃን ተጎናፅፈን ከወሉደ ብርሃን ጻድቃን ጋር በእግዚአብሔር ቀኝ ለመቆም እንድንተጋ ያስጠነቅቀናል::

እንግዲህ እምነት ከብርሃናዊ አምላክ ጋር ኅብረት የምናደርግበት እንደሆነ በወንጌል ተረጋግጦልናል:: በእምነት ሕይወት የሚመላለሱ ሰዎች በብርሃን የሚመላለሱ ሰዎች ናቸው::

የእግዚአብሔርን ሕልውና በእምነት የተረዱና ያወቁ በእርሱም የተገኙትን ምሥጢራት ለመቀበል የሚተጉ የእግዚአብሔር ብርሃንነት የተገለጠላቸው ናቸው:: መዝሙረኛው «አቤቱ የፊትህ ብርሃን በላያችን ታወቀ» ይላል:: /መዝ. 4÷6/ ደግሞም «እግዚአብሔር ብርሃኔና መድኃኒቴ ነው» /መዝ. 27÷1/ ያለው የራሳቸው የሆነውን ነገር ትተው በስብከት ሞኝነት በማመን እግዚአብሔርን በእምነት የሚከተሉት አማኞች እግዚአብሔር የሕይወት ብርሃን እንደሆነ እምነታቸው የብርሃን ሕይወት እንደሆነ የተረዱ ናቸው::

በእርሱ የሚታመኑ በእምነት የሚገሰግሱ ፈጽሞ ጨለማ ወደማይደርስበት ዓለም ለመግባት በዓለም ብርሃን በኢየሱስ ክርስቶስ አምላክነት አምነው ቅዱስ ቁርባን የተቀበሉ ብርሃን ሊመሰክር ዮሐንስ ተላከ ሲመሰክርም «ለሰው ሁሉ የሚያበራ እውነተኛ ብርሃን ወደ ዓለም መጣ» ብሎ መሰከረ ይኸም ብርሃን በልቦናችን ውስጥ የሚያበራ ነው:: /2ጴጥ. 1÷19/ ስለዚህ የዓለም ብርሃን በእምነት ለሚከተሉት ብርሃን ይሆንላቸዋል:: እርሱንም የሚከተሉበት ብቸኛው መንገድ እምነት ነው:: ዮሐንስ በወንጌል የጻፈው የጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ የተናገረው ይህን ያረጋግጣል «ደግሞም ኢየሱስ እኔ የዓለም ብርሃን ነኝ የሚከተለኝ የሕይወት ብርሃን ይሆንለታል እንጂ በጨለማ አይመላለሱም» ብሎ ተናገራቸው /ዮሐ. 8÷12/ በእምነት ብርሃን የሕይወት ብርሃን የሆነውን አምላክ የተመለከቱ ባለማመን ጨለማ የማይመላለሱ እውነተኛ ምእመናን ናቸው:: በመዝሙር «በብርሃንህ ብርሃን እናያለን» /መዝ. 36÷9/ እንደተባለ ሕዝቡን ከባርነት በሙሴ እጅ ነጻ ያደረገው የእስራኤል አምላክ በጉዞ ላይ የነበረውን የእስራኤልን ሕዝብ ሌሊት በብርሃን ይመራቸው ነበር:: በእርሱ የሚታመኑት ጨለማ አያሸንፋቸውምና በብርሃን ያመላልሳቸዋል:: በብርሃን የሚመላለሱ ብቻ ሳይሆኑ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንደተናገረው ለሌሎች የሚያበሩ ብርሃኖች ናቸው::





«እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ» /ማቴ. 5÷14/ ብርሃንነታቸውም እርሱን ከማመንና በእምነት ብርሃንነት በመመላለሳቸው ወይም በሃይማኖት ጸሎት ላይ የተደነገገውን የሃይማኖት መግለጫ ውሳኔዎች ከማወቃቸው ብቻ የመነጨ ሳይሆን ሐዋርያው እንደተናገረው ከእርሱ ከብርሃናት አባት ስለተወለዱ ጭምር ነው «ከብርሃናት አባት ይወለዳሉ» /ያዕ. 1÷17/ በተጨማሪም ቅዱስ ዮሐንስ «እነርሱ ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፈቃድ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም» /ዮሐ. 1÷13/ ይላል:: እነዚህ በትክክል የእግዚአብሔር ጥሪ የደረሳቸውና ወደ ዓለም በላከው ልጁ አንቀጸ ብርሃን ከተባለች ከእመቤታችን ድንግል ማርያም በተወለደው አማናዊ ብርሃን በኢየሱስ ክርስቶስ የባሕሪ አምላክነት ያለ መጠራጠር የሚያምኑ ቅዱስ ጴጥሮስ እንደፃፈው ወደ ሚያስደንቅ ብርሃን የተጠሩ ናቸው:: /1ጴጥ. 2÷9/ ይህ እምነት ደግሞ የዘላለም ሕይወት የሚያስገኘውን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋ ለመብላት ክቡር ደሙን ለመጠጣት ዝግጁ ያደርጋቸዋል::

ነቢየ እግዚአብሔር ኢሳይያስ ለያዕቆብ ቤት ያቀረበው ጥሪ በእግዚአብሔር ብርሃንነት እንመላለስ የሚል ነው:: «እናንተ የያዕቆብ ቤት ኑ በእግዚአብሔር ብርሃን እንሂድ» /ኢሳ. 2÷5/ ነቢያት የሕይወት ብርሃን የኢየሱስ ክርስቶስን ወደዚህ ዓለም መምጣት ይጠባበቁ እንደነበረ ያረጋግጥልናል ልበ አምላክ ዳዊት «ፈኑ ብርሃነከ ወጽድቀከ» /ብርሃንህንና እውነትህን ላከ /መዝ. 42÷3/ በማለት በትንቢቱ ተማጽኗል:: በትንቢት መጽሐፍ ስለፅዮን «ብርሃንሽ መጥቷልና የእግዚአብሔርም ክብር ወጥቶልሻልና ተነሺ አብሪ» ኢሳ. 60÷1 ይህ ቃል አማናዊቷን ፅዮን የፀሐየ ጽድቅ የኢየሱስ ክርስቶስን መገኛ እመቤታችን ድንግል ማርያምን የሚመለከት ነው:: በተጨማሪም የሰው የሕይወት ብርሃን እግዚአብሔር እንደሆነ ምእመናንም ከእርሱ የተነሣ የሚያበሩ የብርሃን ልጆች መሆናቸውን ያረጋግጥልናል:: ጨለማ የሚያሸንፈው





አሕዛብን ነው:: በእምነት ብርሃን የማይመላለሱ ስለሆኑ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል:: «እነሆ ጨለማ ምድርን ድቅድቅ ጨለማም አህዛብን ይሸፍናል» /ኢሳ. 60÷2/

በዚህ ጽሑፍ መግለጽ የፈለግነው እግዚአብሔር ብርሃን ነው አማኞቹም የክብሩ ብርሃን የሚገለጽባቸው ብርሃናት ናቸው:: ስለዚህም የእግዚአብሔር ነቢይ በትንቢቱ «ከዚህ በኋላ እግዚአብሔር የዘላለም ብርሃንሽ አምላክሽም ክብርሽ ይሆናልና ፀሐይ በቀን ብርሃን አይሆንልሽም:: የጨረቃም ብርሃን በሌሊት አያበራልሽም እግዚአብሔር የዘላለም ብርሃንሽ ይሆናል» /ኢሳ. 60÷19/ እንግዲህ ወደዚህ የዘላለም ብርሃን የሚደርሱበት የሕይወት መንገድ ምን ሊባል ይችላል ጥበብ እንጂ::

## እምነት ጥበብ ነው

«ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያየውም አይችልም» /1ጢሞ. 6÷16/

በእርግጥ ተሰውሮና ማንም ሊያየው ሊደርስበትም የማይችለውን አምላክ በእምነት መከተል ጥበብ ነው:: ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ተሰውሮ ወደሚኖር ከሰው አእምሮ በላይ ወደ ሆነ አምላክ የሚደርሱበትና ከእርሱም ጋራ የሚኖሩበት ይህ የእምነት ሕይወት ጥበብ ነው:: ስለዚህ በእምነት የሚመላለሱ በማያምኑት ዘንድ በጥበብ የሚመላለሱ ናቸው::

የጥበብ ሁሉ መገኛ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው «ዓለም ሳይፈጠር ጥበብ በእርሱ ዘንድ ነበረች» /ሲራክ 1÷1/ እግዚአብሔርን በእምነት ሕይወት መከተል ደግሞ የጥበብ ሁሉ መጀመሪያ ነው አባታችን ኢዮብ እንዲህ አለ «ሰውንም እነሆ እግዚአብሔርን መፍራት ጥበብ ነው ከኃጢአት መራቅ ማስተዋል ነው» አለው /ኢዮብ 28÷28/ ከዓለሙ የተሰወረችን እግዚአብሔርን ማወቅና መፍራት የተገኘችው የእምነት ሕይወት ባላቸው ሰዎች ልብ ነው::





ይህ ደግሞ የዓለምን ጥበብ ከንቱ የሚያደርጉበት ነው:: ሐዋርያው ጳውሎስ «ዘመኑን እየዋጃችሁ በውጭ ባሉት ዘንድ በጥበብ ተመላለሱ» በተጨማሪ ለኤፌሶን ቤተ ክርስቲያን ሲጽፍ «እንግዲህ እንዴት እንድትመላለሱ በጥንቃቄ ተጠበቁ» /ኤፌ. 5÷15/ ይላታል:: ይኸውም እግዚአብሔር በማመንና በመፍራት ጥበብ ተመላለሱ ሲል ነው:: ጠቢቡ ሰሎሞን «የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው» /ምሳ. 1:7/ በማለት የተናገረው ይህን ያረጋግጥልናል::

እውነተኛ ምዕመናን የሚያምኑትን እግዚአብሔርን ከፍቅር በመነጨ ይታዘዙታል፣ ይፈሩታልም:: ተመልሰን የሐዋርያውን መልእክት እንድንመለከት የሚጋብዘን አንድ ቃል አለ «በውጭ ባሉት ዘንድ» የሚለው ኃይለ ቃል ከእምነት ሕይወት ውጪ ከብርሃን ተለይተው ባለማወቅ ጨለማ በሚመላለሱት ዘንድ:: በጥበብ ተመላለሱ የሚለው ይህም በቀናች ሃይማኖት ጸንታችሁ ኑሩ ሲለን ነው::

በብርሃን ተሰውሮና ከፍጥረታት እውቀት በላይ የሆነውን አምላክ በእምነት አግኝተዋልና እነዚህ የጥበብ ሰዎች ናቸው:: ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ሰዎች ሲጽፍ «በእግዚአብሔር ጥበብ ምክንያት ዓለም እግዚአብሔርን ስላላወቀው በስብከት ሞኝነት የሚያምኑትን ሊያድን የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆኗልና» /1ቆሮ. 1÷2/ ብሏቸዋል::

እግዚአብሔርን የሚያውቁበትንና የሚያገኙበትን በስብከት ሞኝነት ያመኑ እነዚህ እግዚአብሔር የዓለምን ጥበብ ከንቱ ወዳደረገበት ጥበብ የአምላክ ሰው የመሆን ምስጢር የደረሱና ያመኑ የጥበብ ልጆች ናቸው:: ይኸውም የእግዚአብሔር ጥበብ ቅዱስ ጳውሎስ እንደመሰከረው በሐዋርያት በተሰበከው ከድንግል ማርያም በተወለደው በክርስቶስ የባሕሪ አምላክነት ማመን ነው:: «የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው ይላል» /1ቆሮ. 1÷24/ ተብሎ ተጽፏልና:: ሌላው በእምነት

ገፅ 15



የሚመላለሱ ሰዎች የዓለሙ ጥበብ ተመራምሮ የማይደርስበት የሰማያዊው ጸጋ ባለቤቶች ናቸው:: በእምነት ኃይል ከእግዚአብሔር በተቀበሉት ጸጋ ዓለሙን ወደ እምነት የሚስቡበት ታላላቅ ድንቆች ያደርጋሉ የሐሰተኞችንም ድንቅ ማድረግ ያዋርዳሉ::

እግዚአብሔር ያዘዘውን ተቀብሎ ወደ ፈርኦን ቤተ መንግሥት የገባው ሙሴ በትሩን በመጣል በንጉሥ ፊት ወደ እባብነት ለወጠው ይህን ነገር የንጉሡ ጠንቋዮችና ሟርተኞች አድርገውታል:: ነገር ግን የሙሴ በትር የሟርተኞችን በትር በመዋጥ አሳፈራቸው የሙሴ ተዓምራት በእምነትና ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነች ነበረችና ሙሴም በፈርኦን ፊት በጥበብ ተገለጠ:: ሐዋርያው «እርሱን በማወቅ የጥበብና የመገለጥ መንፈስ እንዲሰጣችሁ እለምናለሁ» /ኤፌ. 1÷17/ በማለት ያስረዳናል:: ስለዚህ ሕይወትን መምረጥ ጥበብ ነው:: ሕይወትን የሚመርጥ ደግሞ እራሱን ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም ያቀርባል:: የዘላለማትን አምላክ በማመን የሚገኘው የዘላለም ሕይወት ነው:: እውነተኛ አማኝ ደግሞ የዘላለም ሕይወት ወራሽ ነው:: ስለዚህ ደግሞ እምነት ሕይወት ነው::

## እምነት ሕይወት ነው

«በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘለዓለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወድዷልና::» /ዮሐ. 34÷16/

ወንጌላዊው የተናገረው ይህን ቃል ልንመረምረው ግድ ይለናል «በየቀኑ ቅዱሳት መጻሕፍትን ይመረምሩ ነበር::» /ሐዋ 17÷11/ በእርሱ የሚያምኑ የዘላለም ሕይወት እንዲኖራቸው ነው ያለው በእርሱ ማመናችን ለዘላለም ሕይወት እንደሚያበቃ ከተመሰከረ እምነት ሕይወት እንጂ ሌላ ምን ልንለው እንችላለን?





ስለዚህ በእምነት የሚመላለሱ በሕይወት የሚመላለሱ መሆናቸውን ማስተዋል ይኖርብናል:: እዚህ ላይ እርሱን የማያውቁት አላለም:: የሚያምኑ እንጂ! የአይሁድ ችግራቸው ይኸው ነበር:: እርሱ በሚነግራቸው ቃል ማመን አለመቻላቸው:: በዓለማችን ክርስቶስን ከማወቅ የዘለለ ሕይወት የሌላቸው ብዙ ሰዎች ናቸው:: እነዚህ ሕይወት ወዳለበት ከእርሱ ለመወለድ ወደሚያበቃ የእምነት ሕይወት አልደረሱምና በመጨረሻ ከቶውኑ «አላውቃችሁም» ይላቸዋል:: ከእርሱም ባለመወለዳቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ወደሚያበቃቸው በመጠመቅም ወደሚያገኙት የልጅነት ሥልጣን አልደረሱም::

«ለተቀበሉት ሁሉ ግን በስሙ ለሚያምኑት ለእነርሱ የእግዚአብሔር ልጆች ይሆኑ ዘንድ ሥልጣንን ሰጣቸው እነርሱም ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከሥጋ ወይም ከወንድ ፈቃድ አልተወለዱም» /ዮሐ. 1÷12/ አሁን የእግዚአብሔር ልጅነቱን የባሕሪይ አምላክነቱን ለመቀበል አለመቻላቸው ባለማመናቸው እንደሆነ ፍርድም እንዳለባቸው ጌታችን አስተምሯል:: «ያለማመናችሁ የሚከሳችሁ እንዳይመስላችሁ አለ:: እነርሱም ተስፋ የምታደርጉት ሙሴ:: ሙሴንስ ብታምኑት እኔን ባመናችሁ ነበር:: እርሱ ስለእኔ ጽፏልና መጻሕፍትም ካላመናችሁ ግን ቃሌን እንዴት ታምናላችሁ» /54÷47/ በማለት አሳፍሯቸዋል::

በርሱ የሚያምን ግን ሕይወትን ይመርጣል:: ሕይወትን የመረጠ አማናዊውን ቁርባን ያለመጠራጠር ይቀበላል:: ለኃጢአት መንጽሒ መስጠቱን ስለሚያምን እራሱን በንስሐ በማዘጋጀት ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን እየተቀበለ ኃጢአትን ሁሉ በእምነት አሸንፎ ይኖራል::





## ያለ እምነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት አይቻልም

### ሀ. ለምንና ወዴት ሳይል ከሀገሩ ወጣ

አብርሃም የተባለው እርስት አድርጎ ሊቀበለው ወደ አለው ስፍራ ለመውጣት በእምነት ታዘዘ ወዴትም እንደሚሄድ ሳያውቅ ወጣ:: /ዕብ. 41÷9/

ይህንን ቃል ስለ ትክክለኛ የእምነት ሕይወት በእምነት ታዛዥነት እግዚአብሔርን ደስ ስለማሰኘት ለዕብራውያን ሰዎች ቅዱስ ጳውሎስ የጻፈላቸው ቃል ነው:: የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ሲል ታሪኩን ይጀምራል:: «ከአገርህ ከዘመዶችህም ከአባትህም ቤት ተለይተህ እኔ ወደማሳይህ ምድር ውጣ» /ዘፍ. 12÷1/ አባታችን አብርሃምን ግን ለምን? ወዴት? ብሎ አልጠየቀም ነገር ግን ታዘዘ እንጂ:: ይህ ነው ትክክለኛ በእምነት ሕይወትና በታዛዥነት እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት::

በተጨማሪ አብርሃም ልጅ እንዲወልድ እግዚአብሔር ተስፋ ሰጥቶት ነበር:: ተስፋውም ሲፈጸም ልጅ ወለደ:: ስሙንም ይስሐቅ አለው:: /ዘፍ. 21÷3/ ይስሐቅ አብርሃም ካረጀና ሚስቱም ሣራ በመካንነት ረጅም ጊዜ ከቆየች በኋላ የተወለደ ልጅ ስለሆነ የስስት ልጅ ነው:: ደግሞ አብርሃም ከእግዚአብሔር ለተቀበለው ተስፋ መፈጸም የተገኘ የተስፋው ልጅ «ዘርህን እንደ ምድር አሸዋ እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛዋለሁ» አለው:: ነገር ግን በአንድ ወቅት እግዚአብሔር አብርሃምን እንዲህ አለው:: «የምትወደውን አንድ ልጅህን ይስሐቅን ይዘህ ወደ ሞሪያ ምድር ሂድ እኔም በማሳይህ በአንድ ተራራ ላይ በዚያ መሥዋዕት አድርገህ ሠዋው አለ»:: /ዘፍ. 22÷2/

ይህ ሕይወትን አጣብቂኝ ውስጥ የሚጨምር ጥያቄ ነው ግን በእምነት ተመለሰ እግዚአብሔርም ባገኘው መልስ ተደሰተ አብርሃም አላንገራገረምና:: በገባህልኝ ቃል «ዘርህን እንደ ምድር





አሸዋ እንደ ሰማይ ከዋክብት አበዛዋለሁ አላልከኝምን?» ሲል አልጠየቀም:: እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ልጁን በእምነት አቀረበ «አብርሃም በተፈተነበት ጊዜ ይስሐቅን በእምነት አቀረበ»:: /ዕብ. 11÷17/ እግዚአብሔርም በአብርሃም በመደሰቱ እንዲህ አለው:: «ልጅህን አትሠዋው አንድ ልጅህን እንዳልከለከልከኝ አይቻለሁና» አለው::

ብዙ ሰዎች ለእግዚአብሔር ቤት መባ ያቀርባሉ:: አንዳንዶቹም እነርሱ ወደ ቤተ እግዚአብሔር ሳይመጡ በሰው በኩል መባቸውን ይልካሉ:: በስለታቸውም ብዛትና መጠን እግዚአብሔር ተገዶ እንዲፈጽም የሚከራከሩትም አሉ:: ስለ ቅዱስ ቁርባን ሲያስብ ሌላው ስለተቀበለ ብቻ ለመቀበል ይሻሉ:: ያለ እምነት ግን እግዚአብሔርን ደስ ማሰኘት እንደማይቻል አይገነዘቡም:: በኃጢአት እየተመላለሱና ከፈቃዱ ውጪ እየኖሩ በጭንቀት ጊዜ መሳልና በአስታወስን ሰዓት የምናቀርበው ስጦታ ምን ያህል እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘው ይሆን? የእግዚአብሔር ቃል «አቤል ከቃየል ይልቅ የሚበልጥ መሥዋዕት በእምነት አቀረበ» ነው የሚለው:: /ዘፍ. 11÷4/

እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት መታዘዝ ያስፈልጋል:: ለመታዘዝ ደግሞ ማመን:: ቅዱስ ጳውሎስ እንዲህ ይላል «ሰውነታችሁን ሕያውና ቅዱስ መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርህራሄ እለምናችኋለሁ»:: /ሮሜ. 12÷1/ ይህ ነው እንግዲህ እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኝና የመጀመሪያ መሥዋዕት:: ለእርሱ መሥዋዕት በሆነ ሰው የሚቀርብ ማንኛውም መባና ታዛዥነት እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘዋል:: ለዚህ ነው አብርሃም ለምንና ወዴት? ሳይል ከአገሩ የወጣው:: ራሱን መሥዋዕት አድርጎ ለማቅረብ ለእርሱም መሥዋዕት ሆኖ በቀረበ ሕይወቱ ልጁን ይስሐቅን ደግሞ በመሥዋዕትነት ለማቅረብ ታዞ ደስ አሰኘው:: እኛም ብንሆን በራሳችን የምንገምተውን መላምትና መንደር ወለድ ተራ ወሬዎችን ይዘን ቅዱስ ቁርባንን

ሽሽትን ከመኖር ይልቅ የሕይወታችን ማዕከል የሆነው ጌታ «ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው» ያለውን ቃል አምነን ለቤተ ክርስቲያን ጥሪ እንታዘዝ።

### ለ. ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶአልና

ቅዱስ ጳውሎስ ስለ እርሱ ሲጽፍ እንዲህ ይላል «ከግብጽም ብዙ ገንዘብ ይልቅ ስለ ክርስቶስ መነቀፍ እጅግ የሚበልጥ ባለ ጠግነት እንዲሆን አስቧልና ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኝ ደስታ ይልቅ ከእግዚአብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ። ብድራቱን ትኩር ብሎ ተመልክቶአልና።» /ዕብ. 11÷25/

ይህ ሰው የግብጻውያንን ጥበብ እየተማረ ያደገው ሙሴ ነው። ሙሴ ከእግዚአብሔር ወደ ግብጽ ሲላክ መጀመሪያ ወደ ፈርኦን እንዴት እንደሚገባ ተከራክሮ ነበር። በኋላ ግን በብዙ ምልክትና ተግሣጽ ወደ ግብጽ ወረደ። ግብጽ ለዚህ ሰው በሽሽት የተዋት ሀገር ናት። «የፈርኦን የልጅ ልጅ መባልን በእምነት እምቢ» ያለበት ምሥጢር ይህ ነው።

ሙሴ በተወለደ ጊዜ እስራኤል በግብጽ ባርነት ነበሩ። /ዘጸ. 2÷1/ በግብጽ ንጉሥ አዋጅ ምክንያትእንዳይሞት እናቱ ስለፈራች ሸሽጋ አሳደገችው። «ሙሴ ከተወለደ በኋላ ወላጆቹ ያማረ ሕፃን መሆኑን አይተው በእምነት ሦስት ወር ሸሸጉት»። የንጉሡንም አዋጅ አልፈሩም። /ዕብ. 11÷23/ ነገር ግን እናቱ ከሦስት ወር በኋላ ልትሸሽገው እንዳልቻለች ባወቀች ጊዜ አውጥታ ጣለችው። ይህ ደግሞ ሙሴ ወደ ፈርኦን ቤተ መንግሥት እንዲገባ በእምላክ እቅድ ስለነበረ ነው። የፈርኦን ልጅ ገላዋን ለመታጠብ ወደ ወንዝ ምንጭ በወረደች ጊዜ ያገኘችው ይህ ህፃን ልጅዋ ይባል ዘንድ ወደደች።

እህቱ ማርያም ተሸሽጋ ትጠብቀው ስለነበር ወደ ተርመት ቀርባ ሞግዚት ላምጣልሽ በማለት የገዛ እናቱን አምጥታ በእናቱ





እቅፍ እንዲያድግ አድርጋዋለች። በእውነት እንዲህ ያለው የእግዚአብሔር ጥበብ እንዴት የሚያስደስት ነው። ሙሴ እስቀድሞ በእናቱ እጅ በኋላም እንደ ፈርኦን የልጅ ልጅ ተቆጥሮ ቢያድግም እግዚአብሔርን መፍራት የግብጽንም ትምህርት እየተማረ አደገ። በቃሉም በሥራው የበረታ ሆነ። ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ሲመሰክር «ሙሴ ካደገ በኋላ የፈርኦን የልጅ ልጅ እንዳይባል በእምነት እምቢ አለ» ብሏል። /ዕብ. 11÷24/

ሙሴ 40 ዓመት ሲሞላው ወንድሞቹን ለመርዳት እስቦ ወደ እነርሱ ወጣ። ነገር ግን አንዱን ግብጻዊ በቁጣ ተነሳስቶ ከገደለ በኋላ ወደ ምድያም ሸሸ። የምድያምም ሴቶች ልጆች ስለረዳ የምድያም ካህን በቤቱ ተቀበለው ከልጆቹ አንዲቷን ዳረለት። ሙሴም የካህኑን በጎች በኮሬብ አጠገብ ሲጠብቅ ሳለ እግዚአብሔር ተገለጠለት። እስራኤልንም ከባርነት እንዲያወጣ ወደ ፈርኦን ላከው /ዘፀ. 3÷4/ ሙሴ ግን ወደ ፈርኦን እንዴት እንደሚገባ ተከራከረ። ነገር ግን በእምነት ሲያድግ ወደ ፈርኦን ደጋግሞ ለመግባት አልተከራከረም።

በእውነት ሙሴ የአገልግሎቱ ብድራት ከእግዚአብሔር ዘንድ ምን ሊሆን እንደሚችል ትኩር ብሎ በተመለከተ ጊዜ ያ በፈርኦን ፊት ለመናገር የተከራከረ ሰው ስለሚመራው ሕዝብ እራሱን አሳልፎ ሰጠ። እራሱንም ለእነርሱ አሳልፎ ለመስጠት በመዘጋጀት እግዚአብሔርን «እነርሱን ከምታጠፋ የእኔን ስም ከሕይወት መዝገብ ደምስስ» በማለት ለመነ /ዘጸ. 32÷11-14/ እውነተኛ አማኝ እንደዚህ ነው። እግዚአብሔርን በማመንና እርሱን ደስ ማሰኘት ፍቃዱን በመከተሉ የሚመጣበት መከራ በፊቱ ምንም እንዳይደለ ይቆጥራል። ምክንያቱም ይገለጥ ዘንድ ያለውን ክብር ከሚቀበለው ከዚህች ዓለም መከራ ጋር በፊቱ ሲያስተያየው ምንም እንዳይደለ ይቆጥራል። ሐዋርያው በመልእክቱ «ለእኛም ይገለጽ ዘንድ ካለው ክብር ጋር ቢመዛዘን ያሁኑ ዘመን ስቃይ





ምንም እንዳይደለ እስባለሁ» /ሮሜ. 8÷18/ በማለት የተናገረው ይህንን ይገልጽልናል።

ሙሴም እግዚአብሔርን ደስ ያሰኘበት የእምነት ሕይወት ይህን የገለጠ ነው። የፈርኦን የልጅ ልጅ ተብሎ ቤተ መንግሥት ከመኖር ይልቅ የእስራኤልን አምላክ ለማገልገል ከሚገለጥለት ክብር ጋር ቢመዛዘን ከምንም የማይቆጥረውን መከራ ከሕዝብ ጋር መቀበልን መረጠ። እግዚአብሔርንም ኢትዮጵያዊቷን በአገባ ጊዜ ለምን አገባት ብለው በሙሴ ላይ ባንጎራጎሩ ጊዜ ስለ እርሱ በመመስከርና በመቆጣት እህቱን ማርያምን በለምጽ መታት።

እውነተኛ አማኝ እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ይፈጥናል። በፊቱ የተወደደ ሥራ ለመሥራት ሁል ጊዜ የሚታየው የሚቀበለው መከራ ሳይሆን የሚገለጥለት ክብርና የተገባለት ተስፋ ነው። ስለዚህ ስለ ስሙ መከራ እየተቀበለና ደስ የሚያሰኘውን ፈቃዱን እየተከተለ የተስፋውን ፍጻሜ ይጠባበቃል። «የማይዋሽ እግዚአብሔር ተስፋ ሰጠን» /ቲቶ. 1÷2/ የሚለውን ቃል ልብ ብለን ከዚህ ታላቅ ነቢይ እንደምንማረው እኛም በቅዱስ ቁርባን ስለምናገኘው ዘላለማዊ ክብርየሰጠንን ተስፋ ለመቀበል «ብድራቱን ትኩር ብለን ልንመለከት ይገባናል» በመቀበላችን አምላካችን ከእኛ ጋር እኛ ከእርሱ ጋር መሆናችን ለቀደመው ኃጢአታችን ይቅርታ ከሚመጣው መጠበቃችን ባጠቃላይ «ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው» መባሉን የማያዘናጋ የእምነት ልብ ሊኖረን ይገባል። /ዮሐ. 6÷54/

### ሐ. በእስራኤልም ሁሉ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም

«ኢየሱስ ይህን ሰምቶ በእርሱ ተደነቀ ዘወርም ብሎ ለተከተሉት ሕዝብ እላችኋለሁ በእስራኤል እንኳ እንዲህ ያለ ትልቅ እምነት አላገኘሁም አላቸው»። /ሉቃ. 7÷9/

ይህ ምስክርነት የተሰጠው ለመቶ አለቃው ነው የሚወደው ባሪያው ታሞ ወደ ሞት በቀረበ ጊዜ በጭንቀት ላይ ወደቀ ነገር





ግን ስለ ኢየሱስም በሰማ ጊዜ የአይሁድን ሽማግሌዎች ወደ እርሱ ሰደደ መድኃኒታችንም ከአይሁድ ሽማግሌዎች ጋር ወደ መቶ አለቃው ቤት አመራ በዚህን ጊዜ ያ መቶ አለቃ መልእክተኛ ልኮ እንዲህ አለው። «ጌታ ሆይ በቤቴ ጣራ በታች ልትገባ አይገባኝምና አትድከም» አለው። ቀጠል አድርጎም «...ቃል ብቻ ተናገር ብላቴናዬም ይፈወሳል» አለ /ሉቃ. 7÷6/ ይህ ነው እንግዲህ ጌታችንን ያስደነቀ እምነት እንዲህ አይነቱን ትህትና የተሞላ እምነት ማን ሊያገኘው ይችላል? እራሳቸውን ከካዱ ሰዎች በቀር! የመቶ አለቃው እራሱን በመካዱ አምላኩን ደስ የሚያሰኝ በእስራኤል ሁሉ ጌታ የላገኘው እምነት ተገኘበት።

እርሱን ይከተሉት ዘንድ የሚፈልጉ ያደርጉት ዘንድ ጌታ ያስተማረውን ያገኘበት ይህ የመቶ አለቃ አንተን እቀበል ዘንድ አይገባኝም አለ። እንዲህ አይነቱን ነገር ኤልሳቤጥም ተናግራዋለች። እመቤታችን ቅድስት ድንግል ማርየም ወደ እርሷ በመጣች ጊዜ «የጌታዬ እናት ወደ እኔ ትመጣ ዘንድ እንዴት ይሆንልኛል» /ሉቃ. 2÷1/ አለች። ይህ ነው እንግዲህ እራስን መካድ «ለሁሉም እንዲህ አላቸው በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ እራሱን ይካድ» /ሉቃ. 9÷23/ እንዲህ ዓይነት ሰው ለእምነቱ በመታዘዝ ሁል ጊዜ የሚኖር ነው።

ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ሰጥቶ በፍቃዱ እየተመራ ራሱን በእምነት ለተወደደና አምላኩን ደስ ለሚያሰኝ ሥራ ሊያስገዛ ለገዛ ፈቃዱ የሞተ ነው። ለዚህ ነው ቅዱስ ጳውሎስ እኔ ሞቻለሁ ሕያው አይደለሁም ያለው ሙሉ ቃሉም እንዲህ ነው የሚለው «ከክርስቶስ ጋር ተሰቅያለሁ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል» /ገላ. 2÷20/። ደግሞም «ዓለም ለእኔ እኔም ለዓለም የተሰቀልኩበት ከጌታችን ከኢየሱስ ክርስቶስ መስቀል በቀር ሌላው ትምክህት ከእኔ ይራቅ» /ገላ. 2÷20/ ለዓለም እንዳይሆኑ ራሳቸውን የገደሉ ሰዎች እርሱን ደስ ያሰኘውን ነገር ለመረጡ ኪዳኑ የጸና ነው። በቤቱና በቅጥሩ የዘለዓለም ስምና

መታሰቢያን ይሰጣቸዋል «እግዚአብሔር ሰንበቴን ስለሚጠብቁ ደስ የሚያሰኘኝን ስለሚመርጡ ቃል ኪዳኔንም ለሚይዙ ጃንደረቦች እንዲህ ይላልና በቤቴና በቅጥሬ ውስጥ ከወንዶችና ከሴቶች ልጆች ይልቅ የሚበልጥ መታሰቢያና ስም እሰጣቸዋለሁ የማይጠፋ የዘላለም ስም እሰጣቸዋለሁ»:: /ኢሳ. 56÷4/ በእምነት ወደ እርሱ ስለመጣችና ደስ የሚያሰኘውን ስለመረጠችው ጌታችን ሽቱ ስለ ቀባችው ሴት ሲናገር «እርሷ ያደረገችው ለእርሷ መታሰቢያ ይሆን ዘንድ እንዲሁ ይህ የመንግሥት ወንጌል በተሰበከበት በየትኛውም ስፍራ ይነገርላታል» በማለት መታሰቢያ እንዲሆናት ይህን የጸና ኪዳንና የዘላለም መታሰቢያ የሰጣት ራሱ ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው:: ኪዳኑን የሚጠብቅ ከተናገረውም አንዳች የማያስቀር ራሱ ወዶና ፈቅዶ ለዓለም መዳን በመስቀል ላይ ያቀረበውን መሥዋዕት ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ለምንቀበል ሁሉ የገባልን ዘላለማዊ የሕይወትና የክብር ኪዳን ምን ያህል ይልቅ?

መ. የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት

«ኢየሱስም፥ ስለ እምነታችሁ ማነስ ነው እውነት እላችኋለሁ የሰናፍጭ ቅንጣት የሚያህል እምነት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ከዚህ ወደዚያ እለፍ ብትሉት ያልፋል የሚሳናችሁ ነገር የለም»:: /ማቴ. 17÷20/

እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት ትችል ዘንድ ተራራ የሚያህል እምነት አልተጠየክም ተራራውን የሚገፋ የሰናፍጭ ቅንጣት ያህል እምነት እንጂ/ እስኪ ይህን ነገር ልብ እንበለው ሰናፍጭ ፍሬዋ ትንንሽ ሲሆኑ ቁመቱ ግን ረጅም የሆነ ለምቾት ለምግብነት በቀመሙት ጊዜ አፍንጫን የሚሰነፍጥና የሚለበለብ የሚያስለቅስ ተክል ነው:: በላዩም አእዋፋት ይንጠለጠሉበታል /ማቴ. 13÷31፤ 17÷21/ ጌታችን የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል





እምነት የጠየቀበት ምክንያት ከማየታችን በፊት እምነት በሰናፍጭ ቅንጣት የተመሰለችበትን ጉዳይ እንመርምር:: ሰናፍጭ ከጥራጥሬ መደብ የማትቆጠር ትንንሽ ዘር ናት:: ድብልብልና በየትኛውም ቦታ ነቅ ወይም ፍንጭ የሌለባት ፍጽምት ናት:: እውነተኛ አማኝ የክርክር ወይም የኑፋቄ የፍርሃት ነቅ የሌለበት ነው:: ቅዱስ ጳውሎስ ስለሚመጣበት መከራ ፍርሃትን እንዳ ይፈጥሩበት ምእመናንን መክሯቸዋል:: «ጳውሎስ ግን መልሶ እያለቀሳችሁ ልቤንም እየሰበራችሁ ምን ማድረጋችሁ ነው? እኔ ስለ ጌታ ስለ ኢየሱስ ስም በኢየሩሳሌም ለመሞት እንኳ ተሰናድቻለሁ እንጂ» በማለት /ሐዋ. 21÷13/ በሌላው መልክ ሰናፍጭ ላይዋ ቀይ ውስጧ ነጭ ነው::

እውነተኛ ተአማኒም በእምነቱ በዚህች ዓለም መከራ ቢኖርበትም በውስጡ ግን ተስፋ መንግሥተ ሰማያት እና ከእምነቱ የተነሣ የሚመነጭ የውስጥ ሰላም አለው:: ሰናፍጭ ጣዕሙ መራሯን ያዘነጋዋል:: ክርስቲያንም እምነቱ በተስፋ መከራውን ያዘነጋዋልና በሰናፍጭ ቁስለ ሥጋ እንደሚደርቅ በእምነትም ቁስለ ነፍስ ትደርቃለች:: ሰናፍጭ ደም ትበትናለች:: እውነተኛ ክርስቲያ ንም በእምነት ኃይል አጋንንትን መናፍቃንን ይበትናል:: ስለዚህ እንደዚህች ቅንጣት ፍጹምነት ባላት እምነት እግዚአብ ሔርን ደስ እናሰኘው ጌታችን ይህችን እምነት ከክርስቲያኖች ይፈልጋታል::

ጌታችን በዚህች ዓለም እየተመላለሰ በሚያስተምርበት ዘመን የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት ያገኘባቸውን ብፁዓን ይላቸው ነበር:: «እምነትሽ ታላቅ ነው» «እምነትህ ታላቅ ነው» የሚላቸው ይህቺን ፍጽምት ጥርጥር የሌለባት እምነት ስላገኘባቸው ነው:: «የልብሱን ዘርፍ ብቻ ብዳስስ እንኳ እድናለሁ ብላ በልቧ ታስብ ነበር» /ማር. 5÷28/ ከዚህ የበለጠ ፍጹም እምነት ለማን አለው? ወንጌል ስለ እርሷ እንዲህ ነው ያለው? «የኢየሱስንም ወሬ ሰምታ በስተኋላው በሰዎች መካከል መጥታ ልብሱን ዳሰሰች»





/ማቴ. 5÷20/ ከብዙ ባለ መድኃኒት ብትደርስም ለመዳን ምክንያት አልሆኑላትም ስቃይም ጠንቶባት ነበር:: ገንዘቧንም ሁሉ ለባለ መድኃኒት ሰጥታ መዳን አልቻለችም:: ይህቺ ሴት ናት ስለ ኢየሱስ በሰማችው ብቻ አምና የለበሰው ጨርቅ ብቻ ቢነካኝ እድናለሁ ያለችው:: በውስጧ ብዙ ነገር የያዘች ፍጽምት የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት እንዴት የሚገርም ነው! ገንዘቧ ሊያድናት ሳይችል ቀርቶ ባለቀ ጊዜ ይረዳት ዘንድ ወዳለው በእምነት ዐይኖቿን እነሳችው መዝሙረኛው «ዐይኖቼን ወደ ተራሮች ዐይኖቿን አነሳችው መዝሙረኛው «ዐይኖቼን ወደ ተራሮች አነሣሁ ረዳቴ ሰማይንና ምድርን ከሠራ ከእግዚአብሔር ነው» አለ እንዲኖረን /መዝ. 120÷1-3/ እንደነዚህ ያለ ፍጹም እምነት እንዲኖረን ያለፉት ቅዱሳን ለእምነታችን መጽናት ወሳኞች ናቸውና ልናስባቸው ይገባል:: በዚህም ሳያበቃ እነርሱ የያዙትን ፍጹም እምነት ገንዘብ እናደርግ ዘንድ ቅዱስ ጳውሎስ «በእምነት ምሰሏቸው» ሲል አሳስቦናል:: /ዕብ. 13÷2-10/ እንደ እምነታችሁ ይደረግላችሁ እንባል ዘንድ ወደ ሕይወት ማዕድ ቅዱስ ቁርባን ስንቀርብ በፍጹም እምነት ሊሆን ይገባል::





# ምዕራፍ ስምንት

## ከሥራ የተለየ እምነት የሞተ ነው

«አንተ ከንቱ ሰው እምነት ከሥራ ተለይቶ የሞተ መሆኑን ልታውቅ ትወዳለህ» /ያዕ. 2÷2/

የእምነት ሕይወት ስንል በእምነት ሕይወት የሚኖር ክርስቲያን ማለታችን ብቻ ሳይሆን ሕይወት ያለው ሕያውነት ያለው እምነት ማለታችን ነው:: ሐዋርያው በመልእክቱ «እንደ ዚሁም ሥራ የሌለው እምነት ቢኖር በራሱ የሞተ ነው» /ያዕ 2÷17/ ለዚህ በሥራ ለማይገለጥ ሙት እምነት ማደሪያ የሆነ እርሱን ከማመን የተነሣ ከሚንቀሳቀሰው አጋንት እምነት ሊለይ እንዴት ይችላል?

እምነት በሥራ ተገልጦ ሕያው ሊሆን ይገባዋል ሥራንም ደግሞ ከእምነት በመነጨ ኃይል እንሠራዋለን::

ለዚህም በጣም ጥሩና ግልጽ የሆነው ማስረጃ የአብርሃም ታሪክ ነው:: /በሮሜ. 4÷16/ የምእመናን ሁሉ አባት ተብሎ መጠ ራቱ የሚታወስ ነው:: የአብርሃም እምነት ለሚያምን ሁሉ የእውነተኛ እምነት ምሳሌ ሊሆን ይችላል ማለት ነው::

በሰብዓዊ ግምት አቋሙ ለጊዜው ፈጽሞ ተስፋ የሚያስቆርጥ መስሎ ታየ እግዚአብሔር ለታላቅ ሕዝብ አባት ትሆናለህ ብሎ ተስፋ ሰጥቶት ነበር:: ሚስቱ ሳራ ግን በእድሜዋ ያረጀችና ልጅም ያልወለደች ሴት ነበረች:: /ዘፍ. 15÷6/ አብርሃም ግን ለሰው የማይመች ነገር ለእግዚአብሔር ይቻለዋል ብሎ ተማመነ እግዚአብሔርም እምነቱን ተመልክቶ ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት /ዘፍ. 15÷6/ «አብርሃም አመነ ጽድቅም ሆኖ ተቆጠ ረለት»:: እግዚአብሔርን ያስደሰተው ይህንን የመሰለ እምነት ነው:: በእርሱም ፊት የታመነው አቋም ትክክለኛ ያደርገዋል::

ይሄ ለአብርሃም ጽድቅ ሆኖ የተቆጠረለት እምነት ነበር /ያዕ. 2÷21/ በእምነት ሕይወት የሚኖር ክርስቲያን ለእኔ ክርስቶስ ሠርቶልኛልና «ከእኔ የሚጠበቅብኝ ነገር በእርሱ ማመን ብቻ ነው» በሚል የተሳሳተ አመለካከት መታመኑን እርሱን በማምለክና በማመስገን ሥራ መግለጥ አቅቶት የወደቀውና የጎስቋላው መልእክ የሰይጣን ሰለባ የሆኑ ጥቂቶች አይደሉም:: በእርግጥ እርሱ ሥራችንን ሠርቶልናል ክርስቶስ የሠራው ለእኛ መስራት ያልተ ቻለንን እርሱ ሠርቶ እርሱንም ከማመናችንም የተነሣ እምነታችንን የምንገልጽበት በእምነት ሥራ የምንሠራበትን ኃይል እንደሰጠን እንዳይረዱ የጨለማው ዓለም ገዢ የወንጌልን ብርሃን የሰወረባቸው እምነታቸው የሥራ ሕይወት ያጣ ሰዎች የተያያዙት የጭፍን ጉዞ መሆኑን ተረድተው ከእንቅልፋቸው ሊነቁ ይገባቸዋል «አንተ የምትተኛ ንቃ ክርስቶስ ያበራልሃል»:: /ኤፌ. 5÷14/

በእርግጥም የምንገልጠው ጌታችን የሠራው ለሰው ያልተ ቻለውን ነው:: በፍርድ ሥር የነበረው ሰው፣ ሕይወቱ ጎስቋላ ሥልጣኑ ደካማ የነበረውን ሰው፣ ሕይወቱ እንደ ጥላ አልፎ እንደ አበባም ረግፎ ይቀር የነበረው ሰው፣ እራሱን ከፍርድ ነጻ ማድረግ አልተቻለውም:: ስለዚህ ከሕግ በታች የነበረው ሰው ከሕግም በላይ ሊያደርገው ሕግንም የሚፈጽምበትን የእምነት ኃይል ሊሰጠውም የእግዚአብሔር ልጅ የሰው ልጅ ሆነ ነቢያትም እንደጠሩት መጣ «ዮሴፍን እንደ መንጋ የምትመራው ሆይ ና» ብለውታል:: እርሱም በዘመኑ መጨረሻ ከድንግል ማርያም ተወልዶ መጣ ለእኛ ራሳችንን ማዳን አልተቻለንም ነበርና ጌታችን እኛን የማዳኑን ሥራ ሠራ ከሕግም በላይ አደረገን በፊቱ የተወደደ ሥራ የምንሠራበትንና ሰውነታችን ለእርሱ በመሥዋዕትነት የምና ርብበት የእምነት ኃይል አገኘን:: ከእንግዲህ «ወንድሞች ሆይ ሰውነታችሁን እግዚአ ብሔርን ደስ የሚያሰኝና ሕያው ቅዱስም መሥዋዕት አድርጋችሁ ታቀርቡ ዘንድ በእግዚአብሔር ርኅራ





እለምናችኋለሁ እርሱም ለአእምሮአችሁ የሚመች አገልግሎታችሁ ነው" /ሮሜ. 12÷1/ ይላል::

ያለ ጥርጥር ሐዋርያው እንዳለው ሰውነታችንን መሥዋዕት የምናደርግበት ሥራ ለእምነታችን ሕይወት የሚሰጥ አገልግሎታችን ነው:: በእምነት ሕግን መጠበቃችን ወይም መፈጸማችን በፊቱ በእምነት በሆነ ሥራ መገለጣችን ነው:: በእግዚአብሔር ፊት መገለጥ ደግሞ እንዴት ያስደስታል? ለዚህም ጥሩ ምሳሌያችን ኢዮብ ነው:: ኢዮብ በፊቱ በተወደደ ሥራ የተገለጠ ስለነበረ አምላኩ መሰከረለት:: እንዲህ ብሎ "ፍጹምና ቅን እግዚአብሔርን የሚፈራ ሰው በምድር ላይ እንደርሱ የለም::"/ኢዮ 2/

በእውነት እንዲህ አይነቶቹን ከላይ የሆነ ምስክርነት ማን ሊያገኘው ይችላል? በፊቱ በመልካም ሥራ ከሚገለጡ ሰዎች በቀር ልብ በል መስካሪው ደግሞ ራሱ ፈጣሪ ነው:: ስለዚህም በኢዮብ እንደማያፍርበት ለሰይጣን አስረግጦ ነገረው:: ከተፈቀደለትም ስልጣን በቀር በኢዮብ ላይ በራሱ ምንም እንዳይሠራ ገደበው::

ስለዚህም በዚያች በተገደበችው ሥልጣኑም ኢዮብን ድል መንሳት አልተቻለውም:: ስለዚህም መልሶና ደጋግሞ በእግዚአብሔር ፊት ከሰሰው:: "የወንድሞች ከሳሽ ተጣለ" በማለት ዮሐንስ በራእዩ እንደተናገረው ከኢዮብ ፍጹምነትና ትዕግስት የተነሣ ከሳሹ ሰይጣን ድል በመነሳቱ ሀፍረትን ተከናነበ:: ኢዮብ ግን ወደ በለጠ ጸጋ አደገ:: ከመንፈስ ፍሬዎች አንዱ የሆነው ትዕግስት በሚገባ በማፍራቱ ዛሬ የኢዮብ መለያው ትዕግስት ሆነ::

ሰው በሕግ አይጸድቅም የሚል አመለካከት ያላቸው ሰዎች ከግንዛቤ ማነስ በስህተት ላይ ተጥለዋል:: ቅዱስ ጳውሎስ ለሮማውያን ክርስቲያኖች ሲጽፍላቸው "በእግዚአብሔር ፊት ሕግን የሚያደርጉት ይጸድቃሉ እንጂ ሕግን የሚሰሙ ጻድቃን አይደሉምና" /ሮሜ 2፡15/ በማለት ያስተማራቸው ቃል በእምነት የሕግን ተፈጻሚነት ያረጋገጠ ነው::





ዛሬ ብዙዎች የሳቱት በዚህ ነው:: ስለ ቅዱስ ቁርባን አማናዊነት ማመን ብቻ ቤተ ክርስቲያን ለማኞች የምታቀብለው ክርስቶስ ለዓለም ድህነት የሰጠው ሥጋውና ደሙ መሆኑን ማመኑ ብቻ ሕይወትየሚሰጣቸው እየመሰላቸው ይዘናጋሉ ይህ እምነት ግን ወደ ቅዱስ ቁርባን በመቅረባችን በሥራ ሊገለጥ ይገባዋል::

## ሀ. በእምነት መዛል

" ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ ራሳቸውን ወጉ" /1ጢሞ. 6፡10/

ብዙዎች የዚህችን ዓለም ክብርሥልጣን ውሸትና በውስጧ ያሉትን የሥጋ ሥራዎች በመውደድ ወደ ኋላ አፈገፈጉ:: የግብር ይሁዳ ጌታችንን ሸጦ ከሐዋርያት ተለይቶ ሄደ:: የጳውሎስ ወንድሙም ዴማስ የዚህች ዓለም ውበት ማርኮት የታላቁን ሐዋርያ የቅዱስ ጳውሎስ ረዳትነት አስጣላው:: ጥቂት የማይባሉት ከእናታቸው ከቤተ ክርስቲያን እቅፍ እየወጡ ሄዱ:: በጠላትነት የተነሱባትና ስለ እርሷ ለመስማት ጆሮአቸውን ያልሰጡ ለቁጥር ያዳግታሉ:: እነዚህ ሁሉ ግን በአንድ ወቀት የክርስትናን ትምህርት የተማሩ የብርሃንን ወንጌል ቃል ያዳመጡ መድኃኒተ ዓለም ክርስቶስ ያደረገውን የመስቀል ሥራ ያወቁ ናቸው:: ነገር ግን ከዚህ የመዳን ትምህርትና የመንፈሳዊ ክብር ፈቀቅ አሉ:: እነዚህ ወገኖች ከቤተ ክርስቲያንአንድነት ተቆጥረው የነበሩ ዛሬ ግን የክርስትናን ሕይወት ጉዳይ መስማት የማይሹ ቢገጥማቸውም ሰምተው እንዳልሰማ የሚያልፉ ናቸው::

ሌሊት በኪዳኑ፣ ማለዳ በቅዳሴው የሚተጉ ደጋግመው በዓላት በፊቱ ለጸሎት የሚቆሙ በአበይት በሌሎችም በዓላት ተገኝተው ቤተ ክርስቲያንን የሚሰሙ ለአገልግሎት እጅግ የሚፋጠኑ በራሳቸው ጊዜ ወደ ቅዱስ ቁርባን የቀረቡ ዛሬግን





መዝሙራቸውን በዘፈን ምጽዋታቸውን በስርቆትና በስስት ፍቅራቸውን በጥላቻ ጸሎታቸውንና ትጋታቸውን በስንፍና ለውጠውታል በነበርንበትና እናውቀዋልን የሕይወታቸው ዓቢይ ብሂል ሆኗል::

የክፋት ሁሉ ምንጭና የሐሰት አባት የተባለው ዲያብሎስ መንፈሳዊ ሐብታቸውን እያስጣለ በሐሰት ትምህርት ንፋስ እየገፋ አፍገምግሞ ከሃይማኖታቸው በማስወጣት ትላንት ፈጣሪና መድኃኒት የሚሉትን ጌታ የፍጡርን ጸጋና ማዕረግ የሰጡ ለድህነት ዓለም ምክንያት ያደረጋትን እናቱን ድንግል ማርያምን የሚቃወሙ የተሳለሙትን መስቀል የካዱ የወንጌሉን ቃል ሲቃወሙ ቅዱስ ቁርባንን መታሰቢያ እንጂ እውነተኛ አይደለም የሚሉ! ሐዋርያው እንደጻፈው የአጋንንትን ትምህርት እያዳመጡ በእምነታቸው ከመዛላቸው የተነሣ የወደቁበት ጥልቅ የጥፋት ጉድጋድ ነው:: /ማቴ 24÷24/ "በኋለኛው ዘመን አንዳንዶች የአጋንንትን ትምህርት እያዳመጡ ሃይማኖትን ይክዳሉ::" /1ጢ.ሞ. 4÷1-2/

በመግቢያችን ላይ እንደጠቀስነው የዚህ ሁሉ ምክንያትና በእምነታቸው ዝለው የጠፉ ሰዎች መውደቅ ምሥጢሩ በዚህች ዓለም ያለውን ክብር ሥልጣን ማዕረግና ከንቱ ልፍለፋዋን መፈለግ ነው:: ቤተ ክርስቲያንን መቆያ አድርገው ከነዚህ ከተጠቀሱት አንዱን ሲያገኙ ወጥተው የሚሄዱ የእምነት ሕይወትን ጉዳይ ሁለተኛና አልያም በመጨረሻ የሸምግልናቸው ወራት መጦሪያ አድርገው የሚገምቱ ከዚህም የተነሣ ወደ ቅዱስ ቁርባን መቅረብ የሚገባው በስተርጅና እንደሆነ የሚያምኑ የሚያስተምሩ አሉ::

ለብዙ ሰዎች በእምነት መዛል ምክንያቶች አድርገን የጠቀስናቸው ልዩ ልዩ የመንፈሳዊ ሕይወት ማነቆዎች ናቸው:: እዚህ ላይ በዓቢይነት የሚጠቀሰው ለእምነታችን መዛል ሰፊ አስተዋጽኦ የሚያደርገው እጉል ምኞታችንንና ገደብ የሌለው ፈላጎታችን ነው:: ክብር! ሥልጣን! ገንዘብ! ውዳሴን የመፈለጉ ሃሳባችን እነዚህን ለማግኘት የምናደርገው ጥረት በእምነታችን ያዝለናል:: ይህ

ገፅ 19



ዓይነቱ ችግር በሕይወታችን ሲፈጠር የቻለውና በዚህ ማነቆዎች በእምነት እንዳንጠነክር ታንቀን የምንያዝበት ምሥጢሩ ራሳችንን አለመካዳችን ነው፡፡ "እኔን መከተል የሚወድ ቢኖር እራሱን ይካድ" /ማቴ 16÷24/ በማለት ጌታችንም ያስተማረው በፍላጎቶቻችን ታንቀን በእምነት እንዳንዝል ፈልጎ ነው፡፡ ራሱን ያልካደ ሰው ገንዘብን ከመውደድ የተነሣ አምላኩን ይክዳል፡፡ ይሁዳም ያደረገው ይህንኑ ነው "ገንዘብን መውደድ የክፋት ሁሉ ሥር ነውና ይህንን ሲመኙ ከሃይማኖት ተሳስተው በብዙ ስቃይ ራሳቸውን ወጉ" /1ጢሞ 6÷10/ በማለት ቅዱስ ጳውሎስ በእምነታቸው የሚዝሉ ሰዎች ከሃይማኖት መንገድ እንደሚወጡና ራሳቸውን በመከራ ጦር እንደሚወጉ አስገንዝቦናል፡፡

ስለ ገንዘብ የሰውን ደም በማፍሰስ ወንጀለኞች የሆኑ ሰዎች ከእምነት ሕግ ውጪ የመሮጥ ችግር ባለቤቶች ናቸው፡፡ ንጉሡ አክዓብ ደሃውን ገበሬ ኢይዝራኤላዊውን ናቡቴንን ያስገደለው ያለአግባብ ለመክበርና አምሮቱን ለመፈጸም የናቡቴንን የወይን ቦታ ለመንጠቅ ሲል ነው፡፡

ነገር ግን ሃሳቡ አልተፈጸመም የእግዚአብሔር ነብይ ኤልያስ ስለ ናቡቴን ገሰፀው የገበሬውን ደም ውሾች እንደላሱት የእራሱንም ደም ውሾች እንደሚልሱት ነገረው ቃሉም ተፈጸመ አክዓብም በብዙ ስቃይ ደሙ ፈሰሰ፡፡ ዛሬ የምናያቸው የምንሰማቸውና የምናስባቸው በእምነታችን እንድንዝል ግድ የሚሉ መሆናቸውን መዘንጋት የለብንም፡፡ ስለዚህ ራሳችንን ከኃጢአት እውቀት ነጻ ማድረግ እንዳለብን ልብ እንበል፡፡ ጌታ ያለውን አንርሳ "የሰው ልጅ በመጣ ጊዜ በምድር ላይ እምነትን ያገኝ ይሆንን?" /ሉቃ 18፥8/ መዝሙረኛው የወደፊት ተስፋውን በእግዚአብሔር ላይ ጥሎ በእምነት የሚኖርን ሰው ምስጉን ብሎታል፡፡

ለዚህ ነው ብዙቅዱሳት ምስጉናን የተባሉት ዛሬም በሚገባቸው ክብር በስማቸው ጽላት ተቀርጾ የመታሰቢያ ቤተ





ክርስቲያን ተተክሎ በእውነተኞች ክርስቲያኖች የሚመሰገኑት የዘላላም ስምና መታሰቢያ በቤቱና በቅጥሩ እንዲይዙ የተደረጉት /ኢሳ 56÷1/ ከሞት በኋላ ያለው ዘላለማዊ ተስፋ መረሳትና መካድ በዚህም ዓለም የፈተና ማዕበል እየተገፋ በመፍገምገም ተስፋ መቁረጥ የእምነት ጸር ነው፡፡

"ለሁሉም እንዲህ አላቸው በኋላዬ ሊመጣ የሚወድ ራሱን ይካድ መስቀሉንም ዕለት ዕለት ተሸክሞ ይከተለኝ" /ሉቃ 9÷23/ እንዲህ ዓይነቱ ተአማኒ ሕይወቱን ለእግዚአብሔር ሰጥቶ በፍቃድ እየተመራ በዚህ ዓለም የሚደርስበትን መከራ አይቆጥረውም፡፡ ምክያቱንም ራሱንም ከሞት በኋላ ስላለው ተስፋ ክዶታልና ነው፡፡ ስለዚህ ሁሉን ለእግዚአብሐር ይሰጣል እንጂ በራሴ ይህን አደርግ ዘንድ ይቻለኛል ብሎ አይናገርም፡፡ በመፈተኑም ጊዜ እንኳ እንዲህ ባደረግ ብሎ የራሱን መላ ምት ከፊቱ አያቆምም ግን ዝምብሎ ወደ አምላኩ ይጸልያል እርሱን ብቻ ተስፋ አድርጎ ይጠባበቃል፡፡ "ሰው ዝም ብሎ የእግዚአብሔረን ማዳን ተስፋ ቢያደርግ መልካም ነው" /ሰቆ.ኤር. 3÷3/ ስለሚናፍቀውና ተስፋ ስለሚያደርገው የዘላለም ሕይወት ትጋቱን መታዘዝ ያደረጋል፡፡ ከፊቱ እግዚአብሔር ለሚሠራው ሥራ ራሱን እየቀደሰ ያዘጋጃል እንጂ በራሱ ሊሠራና በውስጡ ለሚፈጥረው ፈቃድ ጊዜ ሊሰጠው አይሞክርም፡፡ ይልቁንም ራሱን ለእግዚአበሔር ይቀድሳል፡፡ "እግዚአብሔር ነገ በመካከላችን ድንቅ ይሠራልና ተቀደሱ" /ኢያ3÷5/ የእግዚአብሔርን ሥራ በሕይወቱ ለማየት የሚቀድስ ክርስቲያን እራሱን ለሰማያዊውና ለዘላለማዊው ተስፋ ያዘጋጀ ነው፡፡

ከምስር ምድር ወጥቶ ወደ ምድረ ርስት ከነዓን በተስፋ ይጓዝ የነበረውን የእስራኤልን ሕዝብ ይመራ የነበረው ኢያሱ ዮርዳኖስን ለመሻገር ሕዝቡን ካዘጋጀ በኋላ እግዚአብሔር በፊታቸው ለሚሠራው ሥራ እንዲቀደሱ ጠየቃቸው፡፡ በሐሳባቸው ከንቱነት በዚህች ዓለም የሚባክኑ ብዙ ሰዎች የእግዚአብሔርን





መኖር ለማረጋገጥ በፊታችን እንዳች ለምንአያደርግም ብለው ይጠይቃሉ፡፡ የሚገርመው ግን እንደነዚህ ላሉ ሰዎች የበለጠ የእግዚአብሔር ሥራየተሰወረ ነው፡፡ ባልተቀደሰ ሕይወት የቅዱሱን አምላክ ሥራ ለማየት የሚቀርብ ጥያቄ ምንዓይነት ጥያቄ ነው?

እግዚአብሔር በፊቱ ያለ እምነት የሚቆሙትንና ከከንቱው ምኞታቸው ካለማመን ሕይወታቸው የሚመነጨውን ጥያቄ ይዘው የሚገዳደሩትን ይጥላቸዋል፡፡

## ሰ. እምነትን ማሳደግ

"ማደግህ በነገር ሁሉ እንዲገለጥ ይህን አስብ ይህንም አዘውትር" /1ጢሞ 4÷15/

ይህን ቃል ለመንፈስ ልጅ ለጢሞቴዎስ የጻፈለት ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ነው፡፡ በእምነት ሕይወቱ እንዲያድግ ምን ማድረግ እንዳለበት ሲያስገነዝበው ይህን ማስጠንቀቂያ ነግሮታል፡፡ በተጨማሪ ለተሰሎንቄ ክርስቲያኖች እንዲህ ብሎ ጽፎላቸዋል፡፡

ወንድሞች ሆይ እምነታችሁ እጅግ ስለሚያድግ የሁላችሁም የእያንዳንዳችሁ ፍቅር እርስ በርሳችሁ ስለሚበዛ ሁል ጊዜ ስለ እናንተ እግዚአብሔርን እንደሚገባ ልናመሰግን ግድ አለብን፡፡ /2ተሰ.1÷3/

የተሰሎንቄ ምእመናን ዕለት ተዕለት በእምነታቸው እያደጉ እየጎለመሱና እየጠነከሩ መሄዳቸውን ተመልክቶ ይህንን ያደረገው ደግሞ እግዚአብሔር ነውና ልናመሰግነው ግዴታችን ነው አለ፡፡ የእምነት ሕይወት ያለው ሰው በሕይወቱ ስላለው ለውጥ ራሱን አያወድስም ከሥጋዊ ደማዊ እውቀቱና ጥበብ እንደመነጨ አድርጎም አይቆጥርም፡፡ ሁሉን ማድረግ ከሚችል እግዚአብሔር እንደሆነ ያውቃልና አምላኩን ያመሰግናል፡፡

በእምነት ማደግ ማለት በሃይማኖትና በምግባር ደንቶ መኖር በመንፈሳዊ ሕይወትም ከዓመት ዓመት እየጠነከሩ





እየጎለመሱ መሄድ ማለት ነው፡፡ በተጨማሪ በውስጡ ያለውን ፍቅር ዓላማ ይቅር ባይነት ሲያበዛ የሌሉትንም ወደ ሕይወቱ ሲያመጣ የመንፈስ ፍሬዎችን ሲያፈራ ነው በእምነት አደገ የምንለው፡፡ በቅዱስ መጽሐፍ ከአርሻ ሥራ፣ ከእረኝነት፣ ከንግድ፣ ከተጠሩ በኋላ እርሱን በመከተል የእምነት ሕይወታቸውን ያሳደጉ ብዙ ናቸው፡፡

ዳዊት ትንሽ ልጅ ደግሞም እረኛ የነበረ ሰው ነው፡፡ እግዚአብሔር እርሱን በፈለገ ጊዜ ወደ አባቱ ቤት ነብዩ ሳሙኤልን ላከው፡፡ ነቢዩም ወደ ዳዊት አባት ቤት በገባ ጊዜ ዳዊት አልነበረም፡፡ እርሱ በዱር እረኝነት ላይ ነበር፡፡ የዳዊት ወንድሞች ቅብዐ መንግሥቱን ለመቀባት ወደ ነቢዮ በተራ ቀርበዋል፡፡ ነቢዩም ተክለ ቁመናቸውንና የሰውነት ብስለታቸውን እያየ እንዱንሊያነግስ በልቡ ይሻ ነበር፡፡ እግዚአብሔር ግን "ሰው መልክን ያያል እግዚአብሔር ልብን ያያል" አለው፡፡ በመጨረሻ ተረስቶ የነበረው ትንሹ ዳዊት ታወሰና ተጠርቶ መጣ፡፡ እግዚአብሔር በሳኦል ቦታ አነግሠው ዘንድ የመረጥኩት ይህ ነውና ቅባው አለው፡፡ ሳሙኤልም ቅብዐ መንግሥቱን በራሱ ላይ አፈሰሰበት፡፡

ዳዊት ከዚህ ጊዜ ጀምሮ በእስራኤል ነገሠ የእግዚብሔር ጊዜ ደረሰ በዙፋኑ እስኪቀመጥ ድረስ የነበረው ጊዜ ዳዊት በእግዚአብሔር ላይ ያለውን እምነትና መመካት የሚያሳድግበት ጊዜ ነበር፡፡ የደረሰበት ፈተና እምነቱን አጠነከረ ከሳኦል ብዙ ታገሰ ከሳኦልም ግድያ እግዚአብሔር ደጋግሞ አተረፈው፡፡ ስለዚህ ዳዊት በእምነቱ እያደገና ለተቀባበትም አገልግሎቱ ብቁ እያሆነ መጣ አሳዳጅንና ጠላቱን ሳኦልንም ለብቻው ተኝቶ ባገኘው ጊዜ አልገደለውም እንዲገለውም ከጓደኛው የቀረበለትን ጥያቄ አልተቀበለም፡፡ ይህም በእምነት ከማደግ የሚገኝ እንጂ ደመኛውን አግኝቶ የሚተው ማን ነው? እርሱ ግን እግዚአብሔር በቀባው ላይ እጄን

ገፅ 20



አላነሳም አለ:: ይልቁንም ሳኦል ሳይወድ በግድ የዳዊትን ንግሥና እንዲቀበል አደረገው::

ከመጎናጸፊያው ቆርጦ የወሰደውን ጨርቅ በሩቁ በአቀበት ላይ ቆሞ ለሳኦል ባሳየው ጊዜ ሳኦል አዘነ:: ስለ ዳዊት ትልቅነት መሰከረ:: እግዚአብሔር ከእኔ በኋላ በእስራኤል ላይ እንደሾመህ አውቄአለሁ አለ::

ሌላው በሕይወት እያለ ሙት እስከማንሳት የደረሰውን በኋላም ሞቶ እንኳ ሳለ በአጽሙ በሬሳ ላይ ነፍስ የዘራው ታላቁ የእስራኤል ነብይ ኤልሳዕ ነው:: እርሱ ከነቢዩ ኤልያስ በኋላ የሚከተል ደቀመዝሙሩ ነው:: ኤልያስ በተነጠቀበት ዕለት በጽናት እስከ መጨረሻዋ ሰዓት አልለይህም በማለት ተከተለው:: በጽናት እስከ መጨረሻዋ ሰዓት አልለይህም በማለት ተከተለው:: /2ነገ. 2÷1-6/ በዚህም ጽናቱ በኤልያስ ላይ የነበረው መንፈስ በእርሱ እጥፍ ሆኖ አደረበት ብዙ ድንቆችንም አደረገ በእስራኤልም በነቢይነቱ የተወደደና የተፈራ ነበር::

ባጠቃላይ በእምነት ማደግ ማለት ታአማኒው በመንፈሳዊ ሕይወቱ የሚያደርገው እድገት ማለት ነው:: አንድ ሰው እውነተኛ ተአማኒ ከሚያሰኘው ነጥቦች ዋንኛው የሃይማኖቱን ሕግና ሥርዓት ጠብቆ ክርስቶስን ለመምሰልና ይህችን ዓለም ለማሸነፍ የሚያደርገው ግስጋሴ ነው:: በፍጹም አምላኩን ለመምሰል በፍቅርና በትህትና ይሮጣል ሁል ጊዜ የሚታየው "እርሱ ኃጢአት የኢየሱስ ክርስቶስ የደግነት ውበት ነው:: "እርሱ ኃጢአት የሌለበት ጻድቅ፣ እድፍ የሌለበት ንጹህ፣ጠማማነት የሌለበት ቅን፣ ያለ መከልከል ሰጪ፣ መንፈግ የሌለበት ለጋስ፣ ያለ ቂምና ቅናት ይቅር ባይ" መሆኑን ያውቃልና:: /ቅዱስ ኤጲፋንዮስ/

ይህን በመረዳት እራሱን ከኃጢአት አርቆ በቅዱስ ቃሉ እየተመራ በቅዱስ ቁርባን ተወስኖ መኖሩ ወይም በቅዱስ ቁርባን ለመወሰን በምክረ ካህን መመራቱ የእምነቱን ማደግ የሚያመለክት ሐቅ ነው::





## ሐ. መናፍስትን የሚገዛ የእምነት ኃይል

"ወዳጆች ሆይ መንፈስን ሁሉ አትመኑ ነገር ግን መናፍስት ከእግዚአብሔር ሆነው እንደሆነ መርምሩ" /1ዮሐ. 4÷1/

እምነት የጽድቅ ተቀራኒ የሆነውን ጠላት ዲያብሎስን የምንቃወምበት ኃይል ነው:: ቅዱስ ጴጥሮስ "በእምነት ጸንታችሁ ተቃወሙት" /1ጴጥ 5÷9/ ብሉናል:: ዲያብሎስን በእምነት ድል እናደርገዋለን:: በዚህም ኃይል እንገዛዋለን ግንጌታችን እንደ ተናገረው መናፍስት ስለተገዙልን ደስ ሊለን አይገባም:: ምክንያቱም አጋንንትን ድል የምናደርግበትና የምንገዛበት ኃይል የተገኘው ካመነው አምላክ የተነሣ እንጂ በእኛ ኃይል አይደለምና ነው:: እዚህ ላይ ዲያብሎስን ስለምንቃወምበትና እርሱንም ስለሚገዛው የእምነት ኃይል ልንረዳ ይገባል:: ዲያብሎስን የምንቃወመው በምን እምነት ነው? የእግዚአብሔር ኃይል ከእኛ ጋር ሆኖ በሚሠራበትና በእኛ ላይ የተጠመዱትን ወጥመዶች ሰብሮ የዲያብሎስን ኃይል ሁሉ ሊያጠፋልን በሚችል እምነት ነው::

ደቀመዛሙርቱ አጋንንትን ማውጣት ባልተቻላቸው ጊዜ ጌታችንን እንዲህ ብለው ጠይቀውት ነበር:: እኛ እናወጣው ዘንድ ያልቻልነው ለምንድን ነው? እርሱም እንዲህ ብሎ መለሰላቸው ስለ እምነታችሁ ማነስ በተጨማሪ አምላካችን እግዚአብሔር ከጠላታችን ከዲያብሎስ በላይ ኃይል እንዳለው ማወቅ ብቻ ሳይሆን ማመንና ስልፉ የእኛ ሳይሆን የእግዚአብሔር መሆኑን መረዳት ያስፈልጋል:: /1ሳሙ. 17÷47/

ይህም ብቻ ሳይሆን "እግዚአብሔር ስለ እናንተ ይዋጋል እናንተም ዝም ትላላችሁ" /ዘጸ 14÷14/ ተብሎ መጻፉን መዘንጋት የለብንም:: ዘማሪው ዳዊት እግዚአብሔር የመናፍስትን ኃይል ድል የሚነሳበትና ዲያብሎስን የሚያሸንፍበትን የውጊያውን ልምምድ የሚሰጠው እግዚአብሔር እንደሆነ ሲናገር እንዲህ ብሏል:-





"እግዚአብሔር አምላክ ይባረክ ለእጆቼ ሰልፍን ለጣቶቼም ዘመቻን የሚያስተምር" /መዝ 143÷1/ ሁል ጊዜና በማናቸውም የሕይወት እንቅስቃሴያችን የዲያብሎስ ተቃውሞ በማናቸውም ጊዜ እንዳለ መዘንጋት የለብንም:: ስለዚህ በማናቸውም ጊዜ እግዚአብሔርን ከጎናችን ልናደርገውና ከኃይል ሁሉ በላይ መሆኑን መጠራጠር የለብንም:: ስለዚህ ራሳችንን እግዚአብሔርን ደስ በሚያሰኝና ዲያብሎስን በሚቃወም መልካም ሥራ ልናስጠምድ ይገባናል::

የመናፍስትን ኃይል በሚያጋልጥና በሚገዛቸው ጸሎት ጾምና ስግደትራሳችንን ያስገዛንና የነዚህ መንፈሳዊ ኃይሎች ባለኃብት ልንሆን ይገባል:: እግዚአብሔር ኃይሉን በሚያምኑት ዙሪያ ጸንቶ እንዲያቆሙ የሚፈቅድላቸው የጠላት ወገን እንደማይኖሩና በእኛምላይ አንዳች ያደርጉ ዘንድ እንደማይፈቅድላቸው ልናምን ይገባል:: እኛ ግን አበክረን ልናውቀው የሚገባን መጋደላችን ከደምና የሥጋ ጋር አለመሆኑን ነው ከዲያብሎስ ጋር ስላለው ውጊያ ሐዋርያው ሲናገር እንዲህ ይላል " በቀረውስ በጌታና በኃይሉ ችሎት የበረታችሁ ሆኑ የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙ ዘንድ እንዲቻላችሁ የእግዚአብሔርን ዕቃ ጦር ሁሉ ልበሱ" /ኤፌ 6÷10 -11/ እዚህ ላይ ይህን መልዕክት ስንመለከት የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙት የምናስምርበት ዓቢይ ጉዳይ የዲያብሎስን ሽንገላ ትቃወሙት የምናስምርበት ዓቢይ ጉዳይ የዚህም ርእስ መጀመሪያ ሆኖ ዘንድ የተባለውን ነው:: የዚህም ርእስ መጀመሪያ ሆኖ የተጠቀሰው ጥቅስ መንፈስን ሁሉ አትመኑ ነው የሚለው:: ምክያቱም ግልጽና ዲያብሎስ ሽንገላ ስለሆነ ነው::

## የዲያብሎስ ሽንገላ

የዲያብሎስ አንዱ የውጊያ ባሕሪው ሽንገላ ነው:: ሐሰቱን እውነት ጨለማውን ብርሃን ሞትን ሕይወት አስመስሎ የሚሸነግል ክፉ ጠላት ነው:: በእርሱ ያልተሸነገለ የለም:: ብዙዎቹም በሽንገላ ተጠልፈው ወድቀዋል:: እርሱ ለማንም የማይመለስ ሽንጋይ ነው::





ደናግልን፣ መነኮሳትን ይሸነግላል:: ከድንግልና ሕይወት እንዲወጡ ምንኩስናቸውንም እንዲያፈርሱ ብዙ መንፈሳውያን ወደ ዓለም ተመልሰዋል:: እያሌ የሰንበት ት/ቤቶች ወጣቶች የተሰለፉለትን ቤተ ክርስቲያን የማገለገል ምርጫ የሚመሩትን መንፈሳዊ ሕይወትን ትተው ሄደዋል:: የቤተ ክርስቲያንን ጡት እየጠቡ ያደጉ ክብረ ቅዱሳንን ያውቁ የነበሩ ዓይኔን ግንምባር ያርገው ዓይነት ክህደት ክደዋል የጌታችን እናት ከእንደበታቸው ሳትጠራ ውለውና አድረው የማያውቁ እርሷን ለምነው በአማላጅነቷ ብዙ ነገር ያገኙ ዛሬ ግን አፋቸውን ሞልተው "አታማልደንም" ብለዋል::

እነዚህ ሁሉ በዲያብሎስ ተሸንግለው ስብከቱ እውነት መስሏቸው የሰጣቸው ዘላቂ መስሏቸው የወደቁ ናቸው:: መንፈስን ሁሉ ከማመን የተነሣ የሳቱም ጥቂት አይደሉም:: በሐሰተኛ ህልም ምሪት ሕይወታቸውን ለጥፋት የዳረጉ ለሐሰተኞች ነቢያት ቃል የተገዙ ራእይ በእኛ ዘንድ አለ በሚሉ ሰዎች የተጠለፉ ልክ የላቸውም ምክንያቱም የዲያብሎስ ሽንገላ ዛሬ የጀመረና ቀላል አይደለም:: የመጀመሪያ ሰው አዳም በገነት በነበረ ጊዜ የዚህ ጠላት ሽንገላ ደርሶበታል ልጅነትን ያህል ጸጋ ገነትንም ያህል ቦታ እግዚአብሔርን ያህል ጌታ ያጣው በሽንገላ ነው:: "ከዚህ በበላችሁ ቀን ሞትን አትሞቱም እንደርሱ እንዳትሆኑ ክፋውንም ደጉንለይታችሁ እንድታውቀ ስለሚያውቅ ከለከላችሁ እንጂ" /ዘፍ 3÷4/ ከዚህ የሚበልጥ የሽንገላ ቃል ለማን አለው?

ይህን የተናገረው ጠላታችን ዲያብሎስ ነው:: ሴቲቱም የዚህን ሽንጋይ ቃል ተቀበለችው እርሷ በልታ ለባሏ ለአዳምም አበላችው:: እግዚአብሔር አስቀድሞ ከዚህ በበላችሁ ቀን "ሞትን ትሞታላችሁ" ይህን ቃል ለማስለቀቅና ትእዛዙን ለማፍረስ ነው ያ ሁሉ ሽንገላ ለጠላት ያስፈለገው:: ሽንገላው በሐሰት የተሞላ ነው እንዲህ የሆነው የሽንገላ ጠባይ እንዲህ ስለሆነ ብቻ አይደለም:: ዲያብሎስ የሐሰት አባት ስለሆነም ጭምር እንጂ የዲያብሎስ

ሽንገላ በአንድ ወቅት የሚፈጸም አይደለም:: ሁል ጊዜ ቀጣይነት ያለው እና እንደ ዘመኑ ሁኔታ የተራቀቀ ነው:: በዚህ እኛ በያዝነው ዘመን የዲያብሎስ ሽንገላ እጅግ የረቀቀና ብዙዎችን ወደ ማመን ያደረሰ ነው::

ብዙዎች የክርስቶስን ወንጌል አንግበው በሐዋርያነት መልክ ሲሯሯጡና መዳን ትፈልጋለህን?ሲሉ እንደየሀሳባቸው የወንጌሉን ቃል ሲያጣምሙ ይህዓለም በነዚህ ሽንጋዩች ቁጥጥር ሥር መውደቁ ችግሩ ሰዎች መንፈስን ሁሉ ማመናቸው ነው:: ያውም ሐሰተኛ የሐሰት አባት የተባለውን የጣላት መንፈስ /ዩሐ 8÷44/ ጌታችን እንዲህ ያለው ዲያብሎስ የሚነግረንን ነገር በማመን ከመታለል እንድንጠበቅ ነው:: ዲያብሎስ ውሸትን በመንፈስ ብቻ ሳይሆን በሌላም መልኩ ያስተላልፋልና ነው:: ይህም በሚልካቸው ሐሰተኛ ነቢያትና ሐሰተኛ ክርስቶሳውያኖች መናገር መቻሉ ነው:: ጌታችንም እንደነዚህ ካሉት የሐሰተኛ መንፈስ ደቀመዛውርት እንድንጠበቅ በመዋዕለ ስብከቱ "በዚያን ጊዜ ማንም እነሆ ክርስቶስ ከዚህ አለ፤ ወይም ከዚያ አለ ቢሏችሁ አትመኑሐሰተኞች ክርስቶሶችና ሐሰተኞች ነቢያት ይነሳሉና ቢቻላቸውስ የተመረጡትንእንኳ እስኪያስቱ ድረስ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ":: /ማቴ 24÷23-24/ በማለት የተናገረው::

እዚህ ላይ ልብ ይሉት ዘንድ የሚገባው የተመረጡትን እስኪያስት ድረስ ድንቅን የሚያደርግ መባሉን ነው:: ስለዚህ አንዳንድ ሰዎች ስለ ሕይወታችን ሲተነብዩና ወይም ስለአሳለፍነው ነገር ሲነግሩን በእኛም ዙሪያ የገመቱትን እየተናገሩ ጥገኞቻቸው ሊያደርጉንና ሕይወታችንን ሊመሩት ሲፈልጉ ከዚህም በላይ በፊታችን ሙትን እስከማስነሳት ድረስ ድንቅን ሲያደርጉ እውነተኛነታቸውን ለማረጋገጥ ሚዛናችን ያሉንን ማመንና እነርሱን መቀበል መሆኑ እንደሌለበት መረዳት ይኖርብናል::

እንግዲህ አለማመንና ፍርሃትን ከእኛ እናርቅ በፍርሃት ተውጠን ካዩን የሐሰት ሥራቸውንም በተላላነት የምንቀበል ከሆነ





ጠባቂ የሌለውን ግቢ እንዳገኙ ዘራፊዎች ይሰለጥኑብናል:: ሕይወታችንንም ለጉመው ወደፈለጉበት የክህደት ጎራ ይመሩናል:: ስለዚህ ሽንጋዩን ጠላትና ሐሰተኛውን መንፈስ እንዲህ ልንለው ይገባናል::

"ሂድ አንተ ሰይጣን ለእግዚአብሔር ለአምላክህ ስገድ እርሱንም ብቻ አምልክ ተብሎ ተጽፏልና":: /ማቴ 4÷10/ ወደ ሕይወታችን መዳኛ ወደ ቅዱስ ቁርባን እንዳንቀርብና የአባታችንን የሕይወት ግብዣ እንዳንቀበል በከንቱ መለፍለፍ መንገዳችንን ለመዝጋት የሚሽነግለንን ጠላት ከእኔ ዞር በል ልንለው ይገባል::





# ምዕራፍ ዘጠኝ

## ባርነት ወይስ ነጻነት

"ኢየሱስ መለሰ እንዲህ ሲል እውነት እውነት እላችኋለሁ ኃጢአት የሚያደርግ ሁሉ የኃጢአት ባሪያ ነው" ዩሐ 8÷34

በቅድሚያ ባርነት ምንድን ነው? ትክክለኛ የቃሉ ፍቺ ተገዢነት ማለት ነው:: መብትን የሚያሳጣ ነጻነት የሚገፍ ስለሆነ ስያሜው ነጻነት መብት የሌለውንበራሱ ፈቃድ የፈለገውንማድረግ የማይችለውን ተገዢ ያመለክታል:: በመጀመሪያ እግዚአብሔር አንድን ሰው ለሌላው ባሪያ እንዲሆን አልፈጠረውም:: ይህ ቃል ለመጀመሪያ ጊዜ በወይን ጠጅ ስካር ወድቆ ከነበረው ከኖኅ እንደበት ተገኘ እርቃኑን በማየት በሳቀበት ልጅ ከነዓን ላይ የእርግማንቃል ሲናገር እንዲህም አለ "ከነዓን ርጉም ይሁን ለወንድሞቹም የባሪያዎች ባሪያ ይሁን" /ዘፍ 9÷25/ ሰው መብቱን ነፃነቱን በማጣት የሚኖረው ሕይወት የባርነት ሕይወት ነው የእስራኤል ሕዝብ በግብጽ ሀገር የኖሩት ለ430 ዘመናት ነው ይህም የባርነት ኑሮና ተገዢነት ነው /ዘጸ20÷2/

በብሉይ ኪዳን ዘመን ሰው ወደ ባርነት በልዩ ልዩ መንገድ ይገባ ነበር:: ድህውም በገንዘብ ሲገዛ /ዘሌ 25፤44/ በጦርነት ጊዜ ሲማረክ /ዘኁ 31÷7/ ዕዳ ሲኖርበት /ዘሌ 25÷39/ በሌብነት /ዘፃ 22÷2/ በገዛ ራሱ ፈቃድ /ዘፃ 21፤5/ የመሳሰሉትን ያጠቃልላል:: የሙሴ ሕግ ግንከባርነት እርነት የሚወጡበትን መንገድ አመልክቷል/ዘፃ20÷10 -21፤ ዘዳ 2÷27/

ቅዱስ ጳሎውስ ሰው ለእግዚአብሔር የመገዛት መብቱን ለመክልከል በቅድስና ሕይወት በመመላለስ ለዘላለም ደህነትና ከእግዚአብሔር ዘንድ ለሚጠብቀው ወራሽነት እንዳይበቃ የሚያደርገውን የኃጢአት ተገዢነትና የጠባይ የአመል ለውጥ ባርነት ብሎታል:: ይህን በገለጠበት በገላትያ መልእክቱ ለገላትያ





ክርስቲያኖች "በነጻነት ልንኖር ክርስቶስ ነጻ አወጣን እንግዲህ ጸንታችሁቁሙ እንደገናም በባርነት ቀንበር አትያዙ" /ገላ 5÷1/ በማለት ባገኙት ነጻነት ጸንተው በገዛ ራስ ወይም ፈቃድ በሚሠራ ኃጢአት በሚከተለው ዕዳ ወደ ባርነት እንዳይገቡ አስጠንቅቋቸዋል::

በዓለማችን ውስጥ የአያሌ ሰዎች ችግራቸው ነጻነት ማጣታቸው ነው በልዩ ልዩ መልክ ለእግዚአብሔር እንዳይሆኑና የነፍሳቸውን ፈቃድ በመከተል ነፃነት እንዳይኖራቸው ነጻነታቸውን ለሚያረጋግጠው ለሕገ እግዚአብሔር መገዛት የተነሳናቸው ብዙዎችም ከቅዱስ ቁርባን ርቀው የሚኖሩት ከኃጢአት ባርነት የተነሣ ነው::

ማንም መኅዳትን በፈቃድ የሚቀበልና ነፃነቱን የሚጠላ የለም::ብተሻለ መንገድ የባርነትን ዕዳ ለመመልከት የነፃነትን የቃል ፍቺና የሕይወቱን ጠባይ እንመልከት ከባርነት የመላቀቁ በሕጋዊነት የመኖሩና መብትን የማስከበሩ የውስጥ ሰላምና ደስታ ማግኘቱ ነፃነት ይባላል ያለ አንዳች አስገዳጅና ተጽዕኖ ለሚጠቅምና ትርፍ ላለበት ሕይወት መኖር ነው ነጻነት::

ሰው ባዋቂ ሕሊና እንደመፈጠሩ በማመዛዘን የሚጎዳውንና የሚጠቅመውን የመለየት ችሎታ ብቃት አለው::ይህም ብቻ ሳይሆን ራሱን ከጉዳት የሚጠብቅበት ተገቢ ፍርሃት በስሜቱ ውስጥ አለው::

ይሁንና እንደሚጎዳው ወይም እንደማይጠቅመው ውጤቱ የሕይወት ኪሳራ ሲሆን እንደሚችል እያወቀ ፍላጎቱን እንዳይፈጽምና እንዲያደርግ የሚያስገድደው ሁኔታና የማይጠቅመውን ሕግ የሚከለክለውን ከመተው ከማቆም ለመከላከል የማይችልበት ሁኔታ የሚፈጠረው ከመንፈስ ባርነት ነው:: ለምሳሌነት ኃጢአት እንዲሰራ ከትክክለኛ መንገድ የወጣ የክፉ ጠባይ ልምድ ግፊትን እንዲያመነዝር፣ እንዲሰርቅ፣ እንዲገድል፣ እንዲዘፍን፣ እንዲያጨስ፣ እንዲቅም፣ እንዲያማ ፣ በመንፈሱ ያለ ተጽዕኖ ወይም ከፈቃድ

በመንጩ ነጻነቱን የሚያስከብሩለትን ነገሮችን የሚቃረኑ የእነዚህ ነገሮች ፈላጊ መሆኑ የዚህን ርዕስ ትክክለኛ ትርጉም ይሰጠናል። /ሮሜ. 6÷16/

ስለ ሰው ልጅ የዘላለም ድህነት ብሎ ወደዚህች ዓለም የመጣው መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ በሰንበት ቀን ወደ ምኩራብ ገብቶ ሳለ እርሱ በትንቢት የተጻፈውን የኢሳያስን የትንቢት መጽሐፍ በማንበብ የነጻነት አመላክና ነጻ አውጪ መሆኑን ለተሰበሰቡት ገልጦላቸዋል እንደዚህ ሲል «የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው /ለድሆች ወንጌል እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና ለታሰሩትም መፈታትን/ ። ለእውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ» /ሉቃ. 4÷17-19፤ ኢሳ. 64÷12/ የጠባይ ለውጥ ማምጣት እንዳለባቸው እያመኑና ከኃጢአት መፈታት መላቀቅ እርነት መውጣት እነዳለባቸው እያመኑ እንዴት ይቻላል? ለሚለው የራሳቸውን ጥያቄ መልስ መስጠት ሳይቻላቸው ቀርቶ ነጻነታቸውን ማስከበር ያልቻሉ ብዙዎቹ ናቸው። ልብ በል አንተ አንተነትህን ማንነትህን ካወቅህ ከኃጢአት በላይ ነህ የነጻነትህም አምላክ እግዚአብሔር ነው ሕጉና ሥርዓቱንም የነጻነትህ ዋስትናህ ነው።

አሁን ተይዘህ የምትንገላታበት ባርነት ለኃጢአት ከመሸጥህ የተነሣ የመጣብህ ነው አሁን ተይዘህ የምትሰቃይበት ባርነት ከእግዚአብሔር ተለይተህ ካተረፍከው ዕዳ የመነጨ ነው አሁን ተይዘህ ሰላም እርካታ ያመጣህበት ለበዙ ኪሳራ ከተዳረግክበት ነገሮች የተነሳ ነውና ለነጻነትህ የዘላለም ሕይወት ወደምታገኝበት ቅዱስ ቁርባን የሚጠራህን አምላክህን ስማ።





## ጥሪውን መስማት

«ስለዚህ ከሰማያዊው ጥሪ ተካፍዮች የሆናችሁ ቅዱሳን ወንድሞች ሆይ የሃይማኖታችንን ሐዋርያና ሊቀ ካህናት ኢየሱስ ክርስቶስን ተመለከቱ» /ዕብ. 3÷1/

ቅዱስ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት እንዲህ ብሎታል። «በቅዱስም አጠራር የጠራን እግዚአብሔር» /2ኛጢሞ. 1÷9/ የእግዚአብሔር ጥሪ ቅዱስ ነው። የሚጠራቸውን ወይም ጥሪው እንዲደርሳቸው የሚያደርጋቸው ለዘላለም ድህነት ነው እግዚአብሔር ለአርነት ስለሆነ ሰዎችን የሚጠራው ሥራቸውን አይመለከትም ቅዱስ ጳውሎስ በመቀጠል «ይህም እንደ ራሱ ሐሳብና ጸጋ መጠን ነው እንጂ እንደ ሥራችን መጠን አይደለም» በማለት ይህን ያረጋግጥልናል። እግዚአብሔር ከጥልቅ ፍቅሩ የተነሣ የሰው ልጆችን አብዝቶ ይጣራል። የመጣራቱም ዓላማ ለድህነት ነው። ሐዋረያው ቅዱስ ጳውሎስ «ሰዎች ሁሉ ሊድኑ እውነቱን ወደ ማወቅ ሊደርሱ በሚወድ በእግዚአብሔር በመድኃኒታችን ፊት መልካምና ደስ የሚያሰኝ ይህ ነው» ይላል። /1ኛጢሞ. 2÷4/ የእግዚአብሔር ጥሪ የሚያተኩረው ወደ እርሱ እንድንመለስ ነው ነብዩ ወደ «እኔ ተመለሱ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ ይላል የሠራዊት ጌታ እግዚአብሔር» /ሚል. 3÷7 ይላል። ስለዚህ ሰው የእግዚአብሔርን ጥሪ መስማት ሊመርጥ ይገባዋል። ከቀረብልን ጥያቄዎችም አንዱና ዋናው የዘላለምና ሕይወት በማግኘት በልጁ የተገኘውን መንግሥት ወራሾች የሚያደርገን የጌታችንን የመድኃኒታችንን የኢየሱስ ክርስተስን ቅደስ ሥጋውና ክቡር ደሙን ተቀብለን እንድንድን ስለሆነ ጥሪውን መስማት ይገባል። ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋና ክብር ደም ተቀብለን እንድንድን ስለሆነ ጥሪውን መስማት ይገባናል።





## ወደ እርሱ መመለስ

ጥሪውን ከመስማት በኃላ ቀጥሎ ያለው እርምጃ መመለስ ነው። አዎ ወደ እርሱ መመለስ ትክክለኛ መመለስ እውነተኛ ንስሐና ኃጢአትን መናዘዝ ነው «አሁንም ንስሐ ግቡ ተመለሱም ኃጢአታችሁ እንዲጠፋላችሁ» /ሐዋ. 3÷14/ በማለት ተጽፏል። ወደ እርሱ የተመለሰ ሁል ጊዜ በመንፈስ የሚመራ ነው። ሐዋርያው «የሕግ ጽድቅ በኛ ይፈጽም ዘንድ በሥጋ የማንመላለስ በመንፈስ እንጂ እርሳቸው በሥጋ የሚሔዱ የሥጋን ነገር ያስባሉ። ያስባሉና። በመንፈስ ግን የሚሔዱ የመንፈስን ነገር ያስባሉ። በመንፈስ ግን የሚሔዱ የመንፈስን ነገር ያስባሉ። በእግዚአብሔር መንፈስ ተመርተው የሚሔዱ ሰዎች እርሳቸው የእግዚአብሔር ልጆች ናቸውና።» /ሮሜ. 8÷4-5/ ሁል ጊዜ በመንፈስ የሚመላለሱ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ በመንፈስ የሚመላለሱ ክርስቲያኖች ከእግዚአብሔር ዘንድ የሆነ ውን የሚሹ ናቸው። በመንፈስ የመኖራቸውም ውጤት ሐሳባቸው መንፈሳዊና ሰማያዊ እንዲሆን ያደርገዋል። «ከክርስቶስ ጋር የተነሣችሁ እንደሆናችሁ በላይ ያለውን እሹ ክርስቶስ በእግዚአ ብሔር ቀኝ ተቀምጦ ወዳለበት በላይ ያለችውን አስቡ በምድርም ያለችውን አይደለም» /ቆላ. 3÷1-2/ በማለት ሐዋርያው የገለጸውን ይህን የሚያረጋግጥ ነው።

ኃጢአት ከእግዚአብሔር ከስጦታው መለየት እንደሆነ የሚያምን ክርስቲያን ከኃጢአት በቁርጥ ውሳኔ ይመለሳል። የበደለውን አምላክ ይቅርታ ለመጠየቅ በውስጡ ከተሞላ ጸጸት የተነሣ አይኖቹ ኃጢአቱን የሚያጥብ እንባ ያነባል። የእርሱ ወደ ፈጣሪው መመለስ የፈጣሪ ወደ እርሱ መመለስ እንደሆነ ያምናል። «ከአባቶቻችሁ ዘመን ጀምሮ ከሥርዓቴ ፈቀቅ ብላችኋል። እርሷንም አልጠበቃችሁም ወደ እኔ ተመለሱ እኔም ወደ እናንተ እመለሳለሁ» /ሚል. 3÷7/ ተብሎ በነብዩ ተነግሯል። ወደ እግዚአብሔር የሚደረግ መመለስ ወደ ገዛ ልብ የሚደረግ መመለስ ነው።





ኃጢአት ከንቱ ምልልስ እንዝላልነት የአቅጣጫ መጥፋት ያባከኑትን ያጠፉትን ልብ ማግኘት ማንነትን ማግኘት በንዋይ ፍቅር ልቡ የጠፋበት አባቱን ተለይቶ ያባቱንም ቤት ትቶ የጠፋው ልጅ ወደ ልቡ በተመለሰ ጊዜ ነው ወደ አባቱ ቤት ለመመለስ ቁርጥ ውሳኔ የወሰነው /ሉቃ. 15÷18/ እውነተኛ መመለስ በቁርጥ ውሳኔ የሚከናወን ንስሐ ነው። ይህ ደግሞ ሰው የሕይወት ንጽሕና እንዲኖረው ቅዱስ ቁርባን እንዲቀበል ያበቃዋል። ሕይወት ስለሆነ ወደ እርሱ ልንመለስ ይገባል።

## የሕይወት ጎዳና

ጌታችን መድኃኒታች ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔርን ክብር ስለሚያዩ ሰዎች በተራራ ስብከቱ እንዲህ አለ። «ልበ ንጹሐን ብፁዓን ናቸው። እግዚአብሔር ያዩታል» /ማቴ. 5÷8/ ከእግዚአብሔር ጋር የሚኖሩ በንጽሕና የሚመላለሱ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ደግሞ ኃጢአት ኃጢአት መሆኑን ያወቁ ብቻ ሳይሆኑ ኃጢአትን የሚጸየፉትም ናቸው። ብርሃነዓለም ቅዱስ ጳውሎስ ጢሞቴዎስን ሲመክረው «ራስህን በንጽሕና ጠብቅ» /1ኛጢሞ. 5÷22/ ኃጢአትን ከመጥላታቸው የተነሣ ራሳቸውን በንጽሕና በመጠበቅ ከመመላለስ ሲደርሱ ከማንም ጋር በኃጢአት እንዳይተባበሩ የተጠነቀቁ ናቸው። እንዲህ ተብሎ ተጽፏልና «በማንም ላይ ፈጥነህ እጆችህን አትጫን በሌሎችም ኃጢአት አትተባበር» /1ጢሞ. 5÷22/ የሰውን የሕይወት ንጽሕና የሚያበላሽ ክፉ ምኞት ነው። ይህም ነፍስን የሚዋጋት የሥጋ ምኞት ነው «ወዳጆች ሆይ ነፍስን ከሚዋጋ ሥጋዊ ምኞት ትርቁ ዘንድ እንግዶችና መጻተኞች እንደመሆናችሁ እለምናችኋለሁ /1ኛ ጴጥ. 2÷11/ በማለት ሐዋርያው ጴጥሮስ ይመክራል።

ስለዚህ ሁል ጊዜ የሥጋን ሳይሆን የመንፈስን ሥራ እያሰብን ልንመላለስ ይገባናል። የሚገለጠውና የታላቁን ክብር

ባለቤት እንድንሆን «በቀረውስ ወንድሞች ሆይ እውነተኛ የሆነውን ነገር ሁሉ ጭምትነት ያለበትን ነገር ሁሉ ጽድቅ የሆነውን ነገር ሁሉ ንጹህ የሆነውን ነገር ሁሉ... እነዚህን አስቡ» /ፊል. 4፥8/ መባላችንን መዘንጋት የለብንም::

ሌላው የሕይወት ንጽሕና ስንል በኃጢአት ያልተበላሸ ልቦና አዕምሮ ማለታችን ነው:: ኃጢአት የበረዘው ያበላሸው ህሊና የሕይወት ንጽህና እንዳይኖረን ያደርጋል:: የእግዚአብሔርን ኃይል ያዘናጋል:: ሳኦል የሆነበት እንደዚህ ነው ጠላቶቹ ባስጨነቁት ጊዜ የተበላሸው አዕምሮው ሟርተኞችን አሳሰበው የልቡም መሻት ስለበረታ በመልእክተኛ አስፈልጎ ወደገኛት የሙታን መንፈስ ሳቢ ገሰገሰ:: ከዚህም በደሉ የተነሣ ጠንካራ ቅጣት ከእግዚአብሔር ዘንድ ታዘዘበት «የእግዚአብሔር መንፈስ ከሳኦል እራቀ:: ክፉም መንፈስ ከእግዚአብሔር ዘንድ አስቃየው» /1ኛሳሙ. 16፥14/ ሳኦል ከእግዚአብሔር በተለየበት ቅጽበት በአጋንንት ሥልጣን ሥር ወደቀ ያልተቀጠረ ከተማና ጠባቂ የሌለው ቤት ለጠላት ግልጽ እንደመሆኑ ሳኦልም የሰይጣን መጫወቻ ሆነ:: ሕይወቱ ሁሉ የጭንቀት ማደሪያ ሆነበት እጅግም ተቅበዘበዘ:: በሥራው ሁሉ ደስተኛ አልነበረም:: የሚረዳው የእስራኤል አምላክ ተለይቶታልና:: እግዚአብሔር ደስ ወደሚያሰኝ ህሊና መመለስ አልቻለም:: የቀደመውን ልብ ገንዘብ ማድረግ ተሳነው:: ሐዋርያው እንዲህ ይላል «በልባችሁ መታደስ ተለወጡ እንጂ ይህን ዓለም አትም ስሉ» /ሮሜ. 12፥2/

«ለጊዜው በኃጢአት ከሚገኘው ደስታ ይልቅ ከእግዚአ ብሔር ሕዝብ ጋር መከራ መቀበልን መረጠ» /ዕብ. 11፥26/ ድንቅና የተወደደ አባባል ነው:: ብዙ ሰዎችም የሕይወት ምንጭ ቅዱስ ቁርባንን እንዳይለዩ ያደረጋቸው ይኸው ለጊዜው በኃጢ አት የሚገኘው ደስታ ነው::

«ኃጢአት ደሞዙ ሕይወት ሳይሆን ሞት ነው» ለዚህ ነው ሰውን በእግዚአብሔር ፊት ጥፋተኛ የምታደርገውና የሕሊና





መታወክ የሚፈጥርበት ኃጢአት የእግዚአብሔር ቅዱስ ፈቃድ የሚቃረን በመሆኑ ሰው ከኃጢአቱ የተነሣ በፊቱ ጥፉተኛ ይሆናል::

በኃጢአቱም የእግዚአብሔርን ፈቃድ ስለተቃወመ የሕይወትና ደስታ ምንጭ የሆነው አምላክ እርሱን ስለተቃወመ የዘለዓለም ሕይወትና ደስታን ያጣል ዳዊት በኑዛዜው «ከቁጣህ የተነሣ ለሥጋዬ ጤና የለውም ከኃጢአቴም የተነሣ ለአጥንቶቼ ሰላም የላቸውም» /መዝ. 37፥3/ ያለው ለዚህም ነው /ይህ ሰው/ ሰላማዊ ሕይወት በማጣቱና ደስታ ስለተለየው በበደል ሕይወት ውስጥ መሆኑን በመናገር የእስራኤል አምላክ ጭንቀቱን እንዲያስወግድለት «አቤቱ ፈቃድ ሁሉ በፊትህ ነው ጭንቀቴም ከአንተ አልሰውርም ብሎታል » /መዝ.37፥9/

## ስውጣ

«ወደዚህ አትቅረብ አንተ የቆምክባት ሰፍራ የተቀደሰች መሬት ናትና ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው» /ኦ ዘፀ. 3፥5/

እስራኤልን ከግብጽ እንዲያወጣ የተጠራው ሙሴ የዮቶርን የአማቱን የምድያምን ካህን በጎች ይጠብቅ በነበረበት ጊዜ በእግዚአብሔር ተራራ በኮሬብ ታላቅ ምስጢር ተገለጠ:: እነሆም ቁጥቋጦው በእሳት ሲነድድ ቁጥቋጦው ሳይቃጠል ታየ:: ያን ጊዜ ዕብራዊው ሙሴ ልሂድና ቁጥቋጦው ስለ ምን አልተቃጠለም ይህን ታላቅ ራእይ ልይ አለ እግዚአብሔር እርሱ ይመለከት ዘንድ እንደ መጣ ባየ ጊዜ ጫማህን ከእግርህ አውጣ አለው:: ይህ ትዕዛዝ ለሙሴ የቀረበለት በእግዚአብሔር ተራራ በመገኘቱና የተገለጠውን ምስጢር ያይ ዘንድ በመምጣቱ ነበር::

ይህ ይሆንለት ዘንድ ደግሞ ሙሴ መታዘዙና የእግሩን ጫማ ማውጣት ምርጫው መሆን ነበረበት በእጁ እግዚአብሔር እስራኤልን ከግብፅ ባርነት አውጥቶ እስራኤልን እንዲመራ





የሚያደርገው ከዚህም የተነሣ ሰፊ አገልግሎት የነበረው በሕዝብ ሁሉ ላይ መሪና ፈራጅ የነበረው ሙሴ ገና መጀመሪያ ሲጠራ የተፈለገበትና እርሱም ሳያቅማማ ያደረገው የእግሩን ጫማ ማውጣት ነበር:: በተቀደሰው የእግዚአብሔር ተራራ ላይ እንዲቆምና የተገለጠውን ምስጢር አይቶ እንዲረዳ ሙሴ የእግሩን ጫማ አወጣ::

ሙሴ ከዚህ ጥሪ በኋላ ላለው አገልግሎት እግዚአብሔር ፊት ለፊት አፍ ለአፍ በግልጥ ያናገረው ዘንድ እግዚአብሔር ፊት ለፊት ያየው ዘንድ ለሚጠብቀው ክብር /ዘኁ. 12፥6/ ከጥሪው በፊት በግብጽ እያለና በአማቱ በዮቶር ቤት የተማረውን ለአገልግሎት እንቅፋት የሚሆነውን ጠባይና ማንኛውንም ልምምድ ከልብ አውጥቶ መጣል ስለነበረበት እግዚአብሔር የተቀደሰ ሥራ የሚሠራበት ሕይወት ነውና:: የሚቃረን ሐሳብ ከልቡ

ከዚህ በኋላ ለእግዚአብሔር

እንዲወጣ አውጣ የሚለው ቃል ቀረበለት:: ከቅዱስ ቁርባን የሚያርቃ

ለብዙ ሰዎች የዛሬ ችግራቸው ማውጣት አለ

ቸው ምክንያት የኃጢአት ፍቅር ከልባቸው ከመመላለስ በቀር ኃጢ አትን መቻላቸው ነው:: በአምልኮ መልክ ከመመላለስ በቀር ኃጢ አትን ከልብ የማውጣቱ ሥራ ከባድ መስሎ ስለሚታየን እናደርግ ዘንድ አይደለም:: ማሰብን የማንፈልግ አለን ይህ ደግሞ ራስን ካለማወቅ የተነሳ መጎዳት ነው:: መጀመሪያ እራስህን በትክክል እወቅ ራስን ማወቅ ማለት የቆዳ ቀለም የትውልድን ቦታ ጾታ ሐብትና የስልጣንን መጠን አለመሆኑን ልብ በል! የሕይወት ንጽሕና የምታመጣበትና ከእግዚአብሔር ጋር እንዳትኖር ከቅዱስ ቁርባን እንድትርቅና ቤተ መቅደሱን ያቆሸሸከበትን ምኞት ከልብህ ታወጣ ዘንድ እግዚአብሔርና ቃሉ አንተን ማን እንደሚሉህ ተረዳ:: ይህንን ነው ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ለቆሮንቶስ ክርስቲያኖች መልዕክቱን የጻፈላቸው እንዲህ ሲል «ወይስ ሥጋችሁን ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁትን በእናንተ የሚኖረው





የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን በዋጋ ተገዝታችኋልና ለራሳችሁ አይደላችሁም ስለዚህ በሥጋችሁ እግዚአብሔርን አክብሩ::» /1ኛቆሮ. 6፥19-20/

ለዚህ ነው እግዚአብሔር በዋጋ ከገዛችሁት መቅደሴ ለራሳችሁ ካልሆነው ሥጋችሁ እርኩሰትን የኃጢአትን ጫማ አውጣ የሚለው በሌላ በኩል ሕይወታችንን በሙሉ በኃጢአት አጥር ያጠርን የሕይወታችንን ምህዋር በምኞት መሪነት የሚንቀሳቀስ ስለሆነ ክፉውን ምኞት ሁሉ ከእኛ እንድናርቅ «ከልብህ አውጣ በማለት» ለቅዱስ ቁርባን የተዘጋው ልብ ለእርሱ ይከፈትለት ዘንድ ይጠይቃል:: «እነሆ በደጅ ቆሜ አንኳኳለሁ ማንም ድምፄን ቢሰማ ደጁንም ቢከፍትልኝ ወደ እርሱ እገባለሁ ከእርሱም ጋር እራት እበላለሁ እርሱም ከእኔ ጋር ይበላል» /ዮሐ ራዕ. 3፥20/

ስለዚህ እውነተኛ ክርስቲያን ለእርሱ ሲል ያለምንም ቅሬታ ሁሉን ነገር መተውና ከልብ አልያም ቢያንስ ይህን ለማድረግ የልቡና ዝግጅት መኖር እንዳለበት ያስተውላል:: አምላክህ ከልብህ ታወጣው ዘንድ የሚጠይቅህ የሚጠቅምህን ሳይሆን የሚጎዳህን እርሱ ለመረጠልህ ክብር የማያበቃህን እንደሆነ ተረዳ:: ስለዚህ አንዱንና ትልቁን የጉዳትህን ምንጭና የሕይወትህን እንቅፋት በልብህ የነገሠውን ኃጢአት ከልብህ አውጣ::

## ተከተለኝ

«ኢየሱስም... ማቴዎስ የሚባል አንድ ሰው አየና ተከተለኝ አለው ተነሥቶም ተከተለው» /ማቴ. 9፥9/::

ይህ በእውነት ልዩ የሆነ የክብርና የዘለዓለም ሕይወት ጥሪ ነው:: እንከፍልበት ዘንድ የምንጠየቀው ዋጋ ቀላል አይደለም:: ይኸውም ራስን መካድ ነው:: ራስን በመካድ እርሱን መከተል የደቀ መዝሙርነት ሕይወት መኖር እስከመጨረሻው በሃይማኖት ጸንቶ ለበጎ ሥራዎች ሁሉ መገዛት ማለት ነው::

በጠቀስነው ጥቅስ ላይ እንዲህ የሚል ቃል እናንሣ «ተነስቶም ተከተለው» እውነተኛን የሕይወት መሪ የሚከተሉ ሰዎች በጥሪው ላይ የሚያቅማሙ አይደሉም:: በመቅረጫው ተቀምጦ ይቀርጥ የነበረው ማቴዎስ ያለማንገራገር ሁሉን ትቶ እንደተከተለው ይከተሉታል:: /ሉቃ.5÷20/ በአጠቃላይ ስለነበረው ማናቸውም ነገር አሳሰበም ጴጥሮስ እንድሪያስም ሆኑ ሌሎች ሐዋርያት ሲጠሩ እንዲህ ነው ያደረጉት ቅዱስ ጴጥሮስ ለጌታችን በሰጠው መልስ ይህንን ያረጋግጣል:: «እንግዲህ እኛ ሁሉን ትተን ተከተልንህ» /ሉቃ. 18÷28/ በማለት እርሱ የሕይወት መንገድ የእረፍትም ወደብ የሰላም ከተማችን ነውና ወዴትም ቢሆን ተነሥቶ እርሱን መከተል ለምን ሳንል ስለወደፊቱ ሳንጨነቅ ሳንሰጋ በደስታ እርሱን የተከተልን እንደሆነ ሕይወታችንን በጥበቡ ወደ ክብር ይመራዋል::

እዚህ ላይ የመከተልን ትክክለኛ ትርጉም ልንረዳ ይገባል:: ይህም ከእግዚአብሔር ጋራ አንድ መሆን ራሳችንን ለእግዚአብሔር በማቅረብ በክርስትና ውስጥ ባለው መንፈሳዊ ሕይወት አድገን ከፈጣሪ ጋር መገናኘት ማለት ነው:: ከእግዚአብሔር ጋር አንድ ለመሆን ከእርሱ ጋር ለመኖር በንጹህ ሰውነት በቅዱስ ሕይወት የሚያረክሰንን ሁሉ ወደ ኋላ በመጣል ልንከተለው ይገባል:: እውነተኛ ክርስቲያን እግዚአብሔርን እከተላለሁ ሲል በዘፈቀደ በሚመስለው ሀሳብና መንገድ የሚጓዝ ሳይሆን በሃይማኖቱ ሕግና ሥርዓት በመመላለስ ከአምላኩ ጋር አንድ ወደ መሆን ደረጃ ላይ የደረሰ ሲሆን ነው::አንድነቱም ቅዱስ ቁርባን በመቀበል የጸና ነው::

ትክክለኛ አማኝ የሆነ ሰው ይህ እውነተኛ እምነቱ የሚታወቀው ከእርሱ በፊት እንደነበሩት ቅዱሳን አባቶች ከእግዚአብሔር ጋር መገናኘትና አንድ ሆኖ መኖር ሲችል ነው:: ለዚህ ደግሞ የራሱ የሆኑትን ነገሮች እየጣለ በተፈቀደለት ሁሉ እንደ አብርሃም እንዲከብርና እንዲበለጽግ እራሱን ከዶ የአምላኩን





ፍቃድ ይከተላል:: እግዚአብሔርን ከማሰብ የራቀ ሀሊና እግዚአብሔርን መከተል እንዳንመርጥ የሚያደርግ እንቅፋት ነው:: እግዚአብሔርን በፍጹም መከተል አለመምረጥ መጥፋት ነው ምክንያቱም ይህ የምንኖርበት የገሀዱ ዓለም ምንነትና የሕይወት ትርጉም ማወቅ አይቻልም::

የሰው ልጅ ሀልውና የዚህን ዓለም አስገኚ መጋቢና ጠባቂ የሆነ የሕይወት ባለቤት እግዚአብሔርን በማያወላውል ውሳኔ መከተል ነውና::ደግሞም እግዚአብሔርን መከተል ስንል የክርስትና ኑሮ መኖር ማለታችን እንደሆነ መዘንጋት የለበትም::

የክርስትና ኑሮ ማለት ደግሞ የራስን ፈቃድ ጥሎ በእግዚአብሔር ፍቃድ የመኖር ሕይወት ማለት ነው:: በእርግጥ የዚህ ዓለም ሕይወት ፈታኝ ጉዞ የሆነ ተስፋ አስቆራጭ እልህ አስጨራሽ ነው:: የዚህችን ዓለም ሕይወት አቋርጦ ወደ ሚያረካ ነፃነት ለመግባት በምኞት እየተፍገመገሙ ጨው ወደሌለው አልጫ በማይጣፍጥ ሕይወት ከመኖር ነፃ ለመውጣት እግዚአብሔርን መከተል እንዴት እንደሚቻል የቅዱሳንን ሕይወት መከተልና የክርስቶስ የሆኑትን መምሰል ልንመርጥ ይገባል:: ሐዋርያው «እኔ ክርስቶስን እንደምመስል እናንተም እኔን ምሰሉ» ያለው ይህን ሊያረጋግጥልን ነው:: /2ኛ ቆሮ 11÷1-2/

## ስለሰቅህም

«እንዲህም አለው.... ሊነጋ አቅላልቷልና ልቀቀኝ እርሱም ካልባረከኝ አልለቅህም አለው» ዘፍ. 32÷26

ይህንን ቃል የተናገረው የአስራሁለቱ የእስራኤል ነገድ አባት የሆነው የአብርሃም ልጅ ይስሐቅ ከወለዳቸው መንታዎች ታናሹ ያዕቆብ ነው ::የወንድሙን ብኩርና በወጥ ከመግዛት ባሻገር በናቱ ግፊት አባቱን አታሎ የወንድሙን ምርቃት (በረከት) ስለወሰደ ኤሳው ተቆጥቶ ሊገድለው በፈለገ ጊዜ ወደ እናቱ





ወንድም ላባ ዘንድ ሔዶ ከኖረ በኋላ እግዚአብሔር ወደ ከነዓን እንዲመለስ ባዘዘው ጊዜ በጉዞው ላይ በጵንኤል ተኙቶ ሳለ እግዚአብሔር ተገለጸለት:: አንድ ሰውም ሌሊቱን ሁሉ ሲታገለው አደረ በመጨረሻ ግን ያ የሚታገለው ሰው ሊነጋ አቅላለቷልና ልቀቀኝ አለው::ያዕቆብ ምንም ቢደክምና የጭኑ ሽሉዳ ቢደነዝዝም አልለቅህም ካልባረከኝ አልለቅህም ሆነ:: ስንት ሰዎች መርጫው አልለቅህም ካልባረከኝ አልለቅህም ሆነ:: ስንት ሰዎች ናቸው መንፈሳዊ ሕይወታቸው የሃይማኖት ሰውነታቸው ጅምር ሆኖ የቀረው ሲሮጡ የታጠቁት እንዲሉ የቋጠሩት እየተፈታባቸው የያዙት መንፈሳዊ ሕይወት «ፍሬ አልባዋን በለስ» የሆነባቸው::

ለያዕቆብ ምርጫ ግን የዚያ የተገለጠው ሰው መልስ ስምህ ማን ነው? የሚል ነበር:: እርሱም ያዕቆብ ነኝ አለው:: «ከእንግዲህ ወዲህ ስምህ እስራኤል ይባል እንጂ ያዕቆብ አይባል ከእግዚአብሔርም ከሰውም ጋር ታግለህ አሸንፈሃልና» ሲል በዚህ /ዘፍ. 32÷27/ ያዕቆብ በረከት ለማግኘት ያደረገው ስፍራ ባረከው ነው:: መባረክን መርጧልና ትግል ከትክክልኛ ምርጫ የመነጨ ነው:: መባረክን መርጧልና የጭኑ ሽሉዳ ቢደነዝዝም ያን በጽናት ታገለ መቆም እንዳይችል የጭኑ ሽሉዳ ቢደነዝዝም ያን በጽናት ታገለ አሸነፈ:: ምርጫውም ዘሮቹ ሁሉ የተገለጠ ሰው በእምነት ታግሎ አሸነፈ:: ምርጫውም ዘሮቹ ሁሉ የሚጠሩበት በእግዚአብሔር ፊት የተወደደና የተባረከ ስም ሆነ:: ብዙዎች መንፈሳዊ ሕይወታችን ስኬታማዎች እንዳንሆን እንቅፋት የሆነብን ትልቁ ችግራችን እስከ መጨረሻው አለመጽናታችን የያዝነውን መለቀቃችን ነው:: ከብርሃን ወደ ጨለማ የተመለሱ እግዚአበሔር የሰጣቸውን ጸጋ የጣሉ ለነፍሳቸው እረፍት ያገኙበትንና የማይጠፋ ክብርና ስም የሚያስገኝላቸውን እግዚአብሔርን የሚያስደስቱበትን ክርስቲያናዊ ሕይወታቸውን መልቀቃቸው ነው::

የኤልያስ ደቀ መዝሙር ኤልሳዕ ለረጅም ጊዜ በእስራኤል እግዚአበሔርን ያገለገለውና ተአመራትን በማድረግ ያታወቀና የተፈራነቢይ የሆነው መምህሩ ኤልያስ የሚነጠቅበት ጊዜ በደረሰ





ሰዓት አልለቅህም ብሎ በጽናት ስለተከተለው ነው:: ምንም እንኳን ኤልያስ ትቶት እንዲቀር «እግዚአብሔር ወደ ቤቴል...ወደ ኢያሪኮ...ወደ ዮርዳኖስ ልኮኛልና በዚህ ቆየኝ እያለ ደጋግሞ ቢታገለውም ኤልሳዕ ግን ሕያው እግዚአብሔርን በህያው ነፍስም እምላለሁ አልለይህም» (አለቅህም) አለው:: /2ኛነገ. 21÷5/ ከዚህም የተነሣ ኤልያስ ሲነጠቅ ጸንቶ ከማየቱ የተነሣ በመምህሩ የነበረው መንፈስ እጥፍ ሆኖ በእርሱ አደረ ለታላቅ ነቢይነትም አበቃው::

ብዙ ጊዜ ሰዎች እግዚአብሔርን የሚከተሉት በሚመቻቸው በድሎታቸው በስኬታቸው ወቅት ይሆንና የተለያዩ ችግሮች ሲደርሱባቸው አልያም በፈታኝ ሁኔታ ላይ ሲሆኑ እንደ ሳኦል እግዚአበሔርን ለቀው ሟርተኛ ቃልቻ ፍለጋ እንደ ይሁዳ ጌታቸውን ተለይተው ገንዘብ ፍለጋ ይሄዳሉው:: ይሁንና እውነተኛ ክርስቲያን እንደ ዳንኤል በአናብስ ጉድጓድ እንደ ሰለስቱ ደቂቅ ከእሳት ውስጥ ቢሆን እንኳ አምላኩን አልለቅህም ይለዋል:: በደስታም ቢሆን ደስታውን እንዲባርክለት በአደጋ ውስጥ ቢሆንም እንዲያድነው አልለቅህም ይለዋል::

ይህ ምርጫ ደግሞ ይህንኑ ዓይነት ቃል ከአምላኩ ዘንድ እንዲሰማ እንዲያገኝ ያደርገዋል:: ስለዚህ ነገር ቅዱስ ጳውሎስ ሲመሰክር «እርሱ ራሱ አልለቅህም ከቶም አልተውህም» ይላል ብሎአልና:: ስለዚህ በድፍረት «ጌታ ይረዳኛልና አልፈራም ሰው ምን ያደርገኛል እንላለን::» /ዕብ.13÷5/ ብሏል ይህ ቃል እስራኤልን እንዲያገለግል ከሙሴ በኋላ ለመረጠው ለኢያሱ የተነገረው ነው:: በረጅሙ የአገልግሎት ዘመን በሚመጣበት ማናቸውም ፈተና አገለግሎቱን እንዳይለቅ የእስራኤል አምላክ እንዲህ አለው « በሕይወትህ እድሜ ሁሉ ማንም አይቋቋምህም ከሙሴ ጋር እንደነበርኩ ከአንተ ጋር እሆናለሁ አልጥልህም አልተውህም::» /ኢያሱ. 1÷5/

ልብ በል በማናቸውም መከራ አንተንም እንደማይተውህ በኃጢአት መካከል ተጥለህ እንድትቀር አይተውህም እርሱ ባጣህ

በታመምህ በሰዎች ዘንድ በተገፋህና በተረሳህ ጊዜ እንኳ አይለቅህም። ስለዚህ አንተ በማናቸውም አስቸጋሪ ሁኔታ እንኳ አልለቅህም ብለህ በእርሱ ላይ ያለህን የእምነት ጽናት በንጽሕና እየተመላለስክ ቅዱስ ቁርባን በመቀበል ግለጽ።

## ሸሽተህ ስምልጥ

«ወደ ሚዳም ካወጡአቸው በኋላ እንዲህ አለው ራስህን አድን ወደ ኋላህ አትይ በዚህም ዙሪያ ሁሉ አትቁም እንዳትጠፋ ወደ ተራራው ሸሽተህ አመልጥ» /ዘፍ.19÷17/

አንዳንድ ሰዎች ባለማወቅ ብቻ ሳይሆን ውጤቱ ምን ሊሆን እንደሚችል እያወቁ እንኳ ጉዳት ከሚያስከትልባቸው ነገር ሸሽቶ ማምለጥ ያቅታቸዋል። ሸሽት ራስን የማዳኛ መንገድ ነው። አንድ ክርስቲያን በሕይወቱ ኃጢአትን በሁለት መንገድ ሊያሸንፍ ይችላል።ይህም ሊከናወን የሚችለው ከኃጢአቱ ባሕርይ አኳያ ተነሥተን እንጂ እንዲያው በደፈናው አይደለም። ምክንያቱም በሽሽትም የምና በትግል የምናሸነፈው ኃጢአት እንዳለ ሁሉ በሽሽት ማመለጥ ያለብን ኃጢአት ራሴን ሸንፈው ኃጢአት አለ። በሽሽት ማመለጥ ያለብን ኃጢአት ራሴን መሞከር አውቃለሁ አልሸነፍም በሚል ትምክህት ለምታገል መሞከር ያለብን ኃጢአት ራሴን አውቃለሁ ውጤቱ አደገኛ ሊሆን ይችላል እየበሉና ።ለምሳሌ በአንድ ትልቅ ፓርቲ ላይ ተገኝቶ ብዙዎች እየበሉና እየጠጡ ተነሥተውም እየጨፈሩና እየደነሱ ባሉበት ሁኔታ ይህን ከመሸሽ ይልቅ በመካከላቸው በታዛቢነት ተቀምለጬ እያቸዋለሁ እንጂ ምንም አልሆንም በዐይኔ የማየው ዳንሳቸው በጆሮዬ የምሰማው ዘፈናቸው በዙሪያዬ የሚከናወነው ትርምሳቸው ሁሉ ለእኔ የሚታየኝ እንደ ምንም ነው ማለቱ ከከንቱ ትምክህት የሚመነጭ ነው ከዚህ ይልቅ ውጤታማ የሚያደርግ በዚያ ዙሪያ ሁሉ አለመቆሙ የሕሊናና የመንፈስ መሰረቅ እንዳያጋጥመን ሸሽቶ ማምለጡ አማራጭ የሌለው መፍትሔ ነው።





እግዚአብሔር ለሎጥ መላእክቱን ሰደደለት መላእክቱም ከሰዶምና ገሞራ እንዲወጣ ራሱንም እንዲያድን ራሱንም የሚያድን በት ብቸኛ መንገድ ከምትነደዋ ከተማ በመሸሽ ከታዘዘውም እሳት ማመለጥ እንደሆነ ነገሩት ሎጥም ወደ ተራራው ሸሽቶ ራሱን አድኗል /ዘፍ.19÷16/ ልብ በል በዘመናችን የሰዎች ችግር ሕሊናቸ ንን ከሚያነደው ኃጢአት እሳት ለማምለጥ ወደ እግዚአብሔር ተራራ የእውነት መሠረት አምድ ወደ ህያው እግዚአብሔር ቤተክርስቲያን መሸሽ አለመቻላቸው ነው። /1ጢሞ. 3÷15/

ከላይ እንደጠቀስነው ውጤት ጭንቀት ኃጢአትና ሞት ሊሆን እንደሚችል እንኳ እያወቅን ለግዜው ባገኘነው የኃጢአት ደስታ ይሁን አልያም ከውሳኔ ላይ የመድረስ አቅም አጥተን በመሸሽ ልናመልጠው የሚገባን ኃጢአት አለመሸሽ በሕይወታችን የሚያስከትለው ክስረት ቶሎ የማይመለስ ሊሆን ይችላል። የሚመለስ ቢሆን እንኳ የምናተርፈው ጠባሳ በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ሊከተለን ይችላል።

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ በሽሽት ልናመልጠው ስለሚገባ ኃጢአት ሲጽፍልን«ከዝሙት ሽሹ» /1ኛቆሮ. 6÷18/ ይላል። «ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋው ውጪ ነው ዝሙትን የሚሰራ ግን በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል በማለት ያስገነዝበናል።ዝሙትን ታግሎ ለማሸነፍ ከመሞከር ሸሽቶ ማምለጠ ነው። ሙሉ በሙሉ ውጤታማ የሚያደርገን ይህ ደግሞ በመንፈሳዊ ሕይወታቸው የበሰሉና እግዚአብሔርን የሚፈሩት ሰዎች የሚፈጽሙት ተጋድሎ ነው።እግዚአብሔር ለዮሴፍ ከወንድሞቹ ለይቶ አለቃ እደሚያደርገውና እነርሱም ከፊቱ ተደፍተው እንደሚሰግዱለት አሳየው። /ዘፍ. 37÷10/ ግን እግዚአብሔር ቃል የገባለት ነገር ሳይፈፀም ወንድሞቹ ሊገድሉት ወደ ጉድጓድ ጣሉት እንደ ባርያም ሸጡት ጥቂት ነጋዴዎች ከተቀበሉት በኃላ ለእስማኤላውን ተሸጠ በጴጥፍራ ቤት የተወደደ አገልጋይ ነበረ ከዚህ በኋላ ግን የጌታውን ሚስት ዮሴፍ አብሯት





እንዲተኛ ጠየቀችው እርሱ ግን ይህን ክፉ ኃጢአት በእግዚአብሔር ፊት አላደርገውም አላት። /ዘፍ. 39÷9/ በዝሙት ፍቅር ህሊናዋ ተበርዞ ስለነበር የለበሰውን ልብስ ይዛ ታገለችው እንዲገደድም አስጨነቀችው ዮሴፍ ግን የለበሰውን ልብስ ትቶላት ሸሸ በእግዚአብሔር ፊት ፍጹም የተወደደና የተከበረ ሰው ሆነ። እርግጥ ሲሸሽ ልብሱን ትቶ በመውጣቱ ሌላ ችግር ብትፈጥርበትም በሐሰት እሷ ወደ ወህኒ ብታስጥለውም ዮሴፍ እግዚአብሔር ላዘጋጀው ታላቅነት ለአምላክ መለኮታዊ የጥበብ አሠራር መንገድ ሆነ እንጂ አሰጨናቂ አልነበረም። ዮሴፍ ይህንን ባይመርጥና በቀረበለት የኃጢአት ግብዣ ቢስማማና ቢሸነፍ ኖሮ ይህ የተዘጋጀለት ታላቅ ሥልጣንና ክብር በቀረበለትም ነበር። ግን ሸሽቱ አዋጣው።

አንተም አታመንታ በሽሽትህ ምክንያት ልታጣቸው የምትችላቸው ሥጋዊ ጥቅምና የኃጢአት ደስታ አይታይህ ሸሽ እራስህን ወደምታድንበት ተራራ ቤተክርስቲያን በመሸሽ ከዚህ ዓለም የኃጢአትና የተንኮል ሥራ አምልጥ ዓለም በምትፈጥረው ችግር የኃጢአት እሳት እንዳያቃጥልህ ወደ አምላክህ ሸሽተህ አምልጥ። ይህን ብታደርግ በቤቱ የዘላለም ክብርና ሕይወት ከሚገኝበት ማዕድ ከክቡር ሥጋዉና ከቅዱስ ደሙ ትገናኛለህ።

# ምዕራፍ አሥር

## ንጹህ ያልሆነ ግን አይቅረብ

ይህ ቃል በታላቁ ጸሎተ ቅዳሴ ዋናው ካህን ወደ ፍሬ ቅዳሴው ከመግባቱ በፊት እጆቹን በውሀ እያነጻ በሚያውጀው አዋጅ ላይ የሚገኝ ቃል ነው። የአዋጁም ሙሉ ቃል «ንጹሕ የሆነ ከቁርባኑ ይቀበ ንጹሕ ያልሆነ ግን አይቀበል ለሰይጣንና ለመላክተኞቹ በተዘጋጀ በመለኮት እሳት እንዳይቃጠል በልቡናው ቂምን የያዘ ልዩ አሳብና ዝሙትም ያለበት ቢኖር አይቅረብ እጆን





ከአፍአዊ እድፍ ንጹሕ እንዳደረግሁ እንደዚሁም ከዙላችሁ ደም ንጹሕ ነኝ ደፍራችሁ ወደ ክርስቶስ ሥጋና ደም ብትቀርቡ ከርሱ ለመቀበላችሁ መተላለፍ የለብኝም ኃጢአታችሁ በራሳችሁ ይመለሳል እንጂ በንጽሕና ሁናችሁ ባትቀርቡ እኔ ከበደላችሁ ንጹሕ ነኝ» የሚል ሲሆን ብዙ ምእመናን ወደ ቅዱስ ቁርባን ለመቅረብ የማያሰብበትና የማይደፍሩበት ተዘጋጅተው የመጡት እንኳ ለመቀበል የማይደፍሩበት ምክንያት የሚያደርጉት የዚህን አዋጅ መልእክት አለመረዳታቸውን ነው።

የዚህ ነገር ምክንያቱ ደግሞ አማኙ ለዚህ አዋጅ የራሱን ትርጓሜ ስለሚሰጠው ነው።

ብዙዎች ንጹህ መሆን እንዴት ለሰው ይቻለዋል? ምናልባት ልነጻ የምችልበት እድሜ አግኝቼ ሩጫዬን ስጨርስና ሳረጅ ነው ብለው ሲናገሩ ይደመጣሉ።

ይሁንና የአዋጁ አላማና መሠረታዊ ትርጉም ምንድር ነው? እንዴትስ ንጹህ መሆን ይቻላል? ለሚሉትና መሰል ጥያቄዎች መልስ የሚሆነን ትንታኔ ከዚህ በታች ቀርቧል።

በጸሎተ ቅዳሴው ብዙና ልዩ ልዩ ሰዎች ሊሰበሰብ ይችላሉ። ታዲያ ግብታዊ የሆነ ሰው ስለመሥዋዕቱ ሳይገባውና በቂ ጥናት ሳያደርግ ንስሐ ሳይገባና እራሱን ከሠራው ኃጢአት በኑዛዜ ሳያነፃ በደለኛው ከነበደሉ ቂመኛው ከነቂሙ ያላመነው ከነጥርጣሬው እንዳይቀርብ ለማስጠንቀቅና በንስሐ ሳይነጹ መቀበል ተገቢ አለመሆኑን ለማስገንዘብ ነው።

በሌላ መልኩ ኢ አማንያን እንዳይቀበሉ በግዴለሽነት ከመጣሁ ሳይቀር ብለው የሚቀርቡ እንዳይኖሩ አስቀድሞ ለማሳወቅ ሲሆን ንጹህ ያልሆነ ማለት ከኃጢአቱ ያልተመለሰ በካህኑ ፊት ያልተናዘዘ ስለ ቅዱስ ቁርባን ያልጠነቀቀ የቀማውን ያልመለሰ የበደለውን ያልካሰ በንስሐ ተለይቶ ቀኖናውን ያልጨረሰ በድፍረት አይቅረብ ማለት ነው።

## ሳይገባው ማለቱ ምን ማለቱ ነው?

«ስለዚህ ሳይገባው ይህን እንጀራ የበላ ወይም የጌታን ጽዋ የጠጣ ሁሉ የጌታ ሥጋና ደም ዕዳ አለበት።» /1ቆሮ 11÷27/

ሐዋርያው በዚህ መልዕክት ሕይወቱን ለሥጋ ወደሙ እንደሚገባው አድርጎ ሳይዘጋጅና ሳይበቃ የሚቀበለው ባለ ዕዳ ነው አለ ዕዳውም በነፍስና በሥጋ የሚያስፈረድ ነው:: ስለዚህ እንድንበታለን፣ እፈወስበታለሁ፣ ድህነተ ሥጋ ወነፍስ አገኝበታለሁ ሳይል ቢቀበል ይፈረድበታል ሲል መልዕክቱን ጽፎላቸዋል።

## ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት

«ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመስግኖ ቈርሶም እንካችሁ ብሉ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ... ይህ ጽዋ በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው በጠጣችሁት ጊዜ ሁሉን ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት አለ። ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና።» /1ቆሮ. 11÷27-32/

አማናዊውን የሐዲስ ኪዳን መሥዋዕት «መታሰቢያ ነው» የሚሉ ወገኖች የሚጠቅሱት ከዚህ ከላይ ከተጠቀሰው የሐዋርያው መልእክት «ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት» የሚለውን ሐረግ በመምዘዝ እየጠቀሱ ነው።

ጌታችን ግን በጸሎተ ሐሙስ ማታ ከራት በኋላ ምሥጢረ ቁርባንን ለሐዋርያት ሲያሳያቸው ኅብስቱን አንስቶ ባርኮና ቀድሶ «ይህ ሥጋዬ ነው» ብሎ ቆርሶ ሰጣቸው እንጂ ይህ ኅብስት የኔ መታሰቢያ ነው። ወይም የሥጋዬ መታሰቢያ ነው ብሎ አልሰጣቸውም ጽዋውንም አንሥቶ አመስግኖ ባርኮና ቀድሶ «ስለ እናንተ ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው





ከእርሱ ጠጡ» ብሎ ሰጣቸው እንጂ «የደሜ መታሰቢያ ነው» ብሎ አልሰጣቸውም። /ማቴ. 26፡26/

ቀጥተኛውን የዚህን ሐረግ ትርጉም ስንመለከት ትክክለኛውን መልስ የሚሰጠን ከላይ የተጠቀሰውን የሐዋርያውን መልእክት ሙሉ በሙሉ በመቀበልና በማስተዋል መመልከቱ ነው።

ለመታሰቢያዬ አድርጉት ሲል ቀጥተኛ ትርጉሙ ስለ እናንተ የተቀበልኩትን መከራ የመስቀሉን መከራ ሞቴንና መቃብሬን እያሰባችሁ ተቀበሉት ባጠቃላይ ሰውን ሁሉ ስለማዳን ታስሮ ተገርፎ ምርር ብሎ አልቅሶ ተጠምቶና ተገፎ ተሰቅሎ የቆረሰውና ያፈሰሰው ስለሆነ ይህን ሥጋና ደም በተቀበላችሁ ጊዜ መከራዬን አዘክሩ የሚል ነው። ለዚህም ማስረጃችን በዚሁ መልዕክት መደምደሚያ ላይ «ይህን እንጀራ በበላችሁ ጊዜ ሁሉ ይህንም ጽዋ በጠጣችሁ ጊዜ ሁሉ ጌታ እስኪመጣ ድረስ ሞቱን ትናገራላችሁና» /1ቆሮ. 11÷26/ የሚለው ኃይለ ቃል እና ይህን ለመታሰቢያዬ አድርጉት ለሚለው ሐረግ ማብራሪያ አድርጎ ያቀረበው ቃል ነው።

# ምዕራፍ አሥራአንድ

## የተሳሳቱ አባባሎችና የመንደር ወሬ

«ነገር ግን ለዚህ ዓለም ከሚመችና የአሮጊቶችን ጌቶች ጨዋታ ከሚመስል ተረት ራቅ» /1ጢሞ. 4፡7/

ቅዱስ ጳውሎስ ይህን ታላቅ ማስጠንቀቂያ ለመንፈስ ልጁ ለጢሞቴዎስ የጻፈለት ተራ አባባሎችና የመንደር ወሬዎች ለክርስቶስ ወንጌል መጋረጃ እንዳይሆኑና ክርስቲያኖችን ከእውነት እንዳያርቃቸው ለማስተማር ጭምር ነው።





ሰዎች ወደ ሕይወት ምንጭ ወደ ቅዱስ ቃሉ እንዳይቀርቡ የየመንደሩ ወሬዎችና የባልቴቶች ተረት የወንጌሉ ቃልና የቤተ ክርስቲያናችን ትምህርት እየመሰሉ ሕዝብን ሲያሳስቱና በመንደር ወለድ የተሳሳቱ አባባሎች እዲመራ ሲያስገድዱት ይታያሉ።

ሕዝቡም ልክ ከቤተክርስቲያኒቱ አንደበት የሰማ በአውደ ምሕረቱም የተሰበከለት ይመስል ያንኑ መልሶ ሲያስተጋባና ከዚህ ከንቱ ከሆነ ለዓለምም ከሚመች ወሬ ሊርቅ ሲገባው የሃይማኖቱ ቀኖና አስመስሎ የሙጥኝ ማለቱ ሕይወቱ ካለበት አንድ እርምጃ እንዳይዘል አድርጎታል።

ታላቁ ሐዋርያ ቅዱስ ጳውሎስ በድጋሚ ጢሞቴዎስን ሲመክረው «ጢሞቴዎስ ሆይ በውሸት እውቀት ከተባለ ለዓለም ከሚመች ከከንቱ መለፍለፍና መከራከር እየራቅህ የተሰጠህን አደራ ጠብቅ ይህ እውቀት አለን ብለው አንዳንዶች ስለ እምነት ስተዋልና» /2ጢሞ. 6÷20/ ይለዋል።

ዛሬም ብዙዎች ከቤተ ክርስቲያኗ ቀኖናና ትውፊት ውጭ በተሳሳቱ የመንደር ወሬዎችና ባሕል ወለድ ትምህርቶች እየተወሰደ ለወንጌሉ ቃልና ለቤተ ክርስቲያኒቷ መመሪያ ተቃራኒና ተከራካሪዎች ሆነዋል። እኔም በዚህ ምዕራፍ በሕዝበ ክርስቲያኑ መካከል እንደ ሕግና ሥርዓት ተጠቃሽነት ባላቸው አንዳንድ ነጥቦች ላይ መልስ ሰጥቼባቸዋለሁ።

## የታመመን ሰው ቢያቆርቡት ቶሎ ይሞታል

«ሰው ከርሱ በልቶ እንዳይሞት

ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው» /ዮሐ. 6÷50/

መቼስ የዲያብሎስ የውጊያው ጥበብ የቱንም ያህል ቢረቅ በመንፈሳዊ ሕይወት ለሚመላለስ ሰው ግን ሊሰወርበት አይገባም «ጦር ከፈታው ወሬ የፈታው» እንዲሉ የተሳሳተ ትምህርትን እና





የማስፈራሪያ ወሬዎችን ከምሥራች ወንጌል ጋር እንዲደባለቅ በማድረጉ ሰይጣን ውጤታማ ሆኗል ብንል ማጋነን አይሆንብንም።

ቀድሞ ሞት የሚያመጣውንና ውድቀት ያስከተለውን የዕፀ በለስ ፍሬ አዳምና ሔዋን እንዳይበሉ በተከለከሉ ጊዜ በተቃራኒ ሃሳብ መጥቶ ብሉ «ሞትን አትሞቱም» /ዘፍ. 3÷4/ ያላቸው እርሱ ሲሆን ዛሬ ደግሞ እንበላው ዘንድ አምላካችን የሰጠንን የሕይወት እንጀራ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን እንዳንቀበል «የታመመን ሰው ቢያቆርቡት ይገላግለዋል» እያሰኘ ቆራቢን አስቆራቢን በፍርሃት ሸብቦ መዳኛውን እንደመጥፊያ እንዲቆጥረው አድርጓል።

ከሞት ወደ ሕይወት የሚያሸጋግረውን በቀደመ ኃጢአት ይቅር የሚያሰኛቸውን ከሚመጣ ኃጢአት የሚጠብቃቸውን ከደዌ ሥጋ ከደዌ ነፍስ የሚፈውሰውን ቅዱስ ሥጋውን «የሕይወት እንጀራ እኔ ነኝ አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱም ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል። እኔም ስለ ዓለም የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው» /ዮሐ. 6÷48-51/ በማለት የሰጠውን ጸጋ ሰው እንዳያገኝ እና በሥጋው ፈውስ በነፍሱ ድህነት እንዳይቀበል «የታመመን ሰው ቢያቆርቡት ይሞታል» እያሰኘ ሲያስፈራራና ጣር ላይ ያለ በሽተኛ ቢያቆርቡት ይገላግለዋል በሚል ወሬ ክርስቲያኑ በቅዱስ ቁርባን ላይ ያለው እምነት እንዲዛባ እያደረገ ከመጨረሻው የድህነት መንገድ ሲያስወጣው ይታያል።

ስለዚህ ይህን የጠላት ውጊያና የወንጌል እንቅፋት ለማሸነፍ ክርስቲያኖች ሰይጣንን ልንዋጋውና እንዲህ ካለ የተዛባ ትምህርትና ከንቱ ተረት ልንርቅ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ከደዌ ሥጋ ከደዌ ነፍስ የሚፈውስ ክርስቶስ በእኛ እንዲኖር በመስቀል ላይ የተሰዋልን እውነተኛ የሕይወት መብልና መጠጥ መሆኑን እንረዳ።

«ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜም እውነተኛ መጠጥ ነው» /ዮሐ. 6፡55/

## የቆረበ ሰው ብቻውን ቢሆን ሰይጣን ያገኘዋል

«ሰብዓውም በደስታ ተመልሰው ጌታ ሆይ አጋንንት ስንኳ በስምህ ተገዝተውልናል አሉት እንዲህም አላቸው ሰይጣንን እንደ መብረቅ ከሰማይ ሲወድቅ አየሁ እነሆ እባቡንና ጊንጡን ትረግጡ ዘንድ በጠላትም ኃይል ሁሉ ላይ ሥልጣን ሰጥቻችኋለሁ የሚጐዳችሁ ምንም የለም» /ሉቃ. 10÷17/

እንዲህ አይነቱ አስተሳሰብ ያላቸውና ይህንን የመንደር ወሬ ስማ በለው የሚሉ ሰዎች ትልቁ ችግራቸው የእውቀት ማነስና በእምነት ዝለው በሰይጣን ላይ የተሰጣቸውን ሥልጣን አለማወቅ ነው::

በቅድሚያ አንድ ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን የተቀበለ ሰው ከጐኑ ሰው የሚያስፈልገው ለምንድር ነው? ለሚለው ጥያቄ ለአንባብያን መልስ ልሰጥበት እወዳለሁ::

እንደ ሕግና ሥርዓት ቆራቢን ሰው ከአጠገብ እንዳይለይው የሚል በቤተ ክርስቲያን ተጽፎ አናገኝም:: ይሁንና ቆራቢዎቹ ልጆች ከሆኑ ሊጠበቁ ስለሚገባቸውና በሌላ መልኩ መለኮታዊውን ሥጋና ደም የተቀበለው ሰው በዕለቱ የማያከናውናቸው ሥራዎች ይኖራሉ ቆራቢው ደግሞ አምላኩ የጸጋ ተዋሕዶ የተዋሐደው የክርስቶስ ሙሽራ ነውና ላብ እንዲፈሰው ድካም እንዲሰማው የሚያደርጉ ሥራዎችን ስለማይሠራ ረዳት ስለሚያስፈልገው ነው::

ይህም ክርስቲያኖች ለአምላካቸው ካላቸው ፍቅርና ለአማናዊው ቁርባን ከሚሰጡት ክብር የተነሣ የሚወስዱት ጥንቃቄ ሆኖ ሳለ በመግቢያው ላይ እንደተጠቀሰው ከእውቀት ማነስና በጠላት ኃይል ላይ ሁሉ የተሰጣቸውን ሥልጣን ካለመረዳታቸው የተነሣ ይህን ማብራሪያ የሰጠንበትን አባባል





የተቀበሉ ወይም የቆረበ ሰው ብቻውን ከሆነ ሰይጣን ይጸረረዋል የሚባለውን እንደወንጌል ቃል የወሰዱ ጥቂቶች አይደሉም::

ለክርስቲያኖች ሁሉ የሚሆን ጥያቄ ማቅረብ እወዳለሁ:: ለሁላችን ሕይወት ለኃጢአታችን ይቅርታና ከአምላካችን ጋር ለተመሠረተው እርቅ መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እራሱን በስቀል ላይ ሰውቶ ቅዱስ ሥጋውን ሲቆርስልን ክቡር ደሙን ሲያፈስልን ሰይጣን ምን ብሎ እንደ ጮኸ ታስታውሳላችሁ? ለዓለሙ ሁሉ ድህነት በቅዱስ መስቀሉ ላይ የሕይወት እንጀራ በሰጠ ጊዜ ሳጥናኤል ወደቀ በብርቱም ተጨነቀ በምሬትም እንዲህ ሲል ጮኸ «ሥጋን ከብልየቱ አድሶ ከመለወጥ አድኖ የተዋሐደው ይህ ማነው? በኔ ሥልጣን ሥር ያለ ሥጋን ለብሶ በባሕርዩ ባለ የብርሃን ነፀብራቅ እኔን ድል የነሣ ይህ ማነው? ወደ ጥፋት ነጥቆ ይወስደኝ ዘንድ በእኔ ሥልጣን ሥር ካለ ሥጋ ሥልጣን የተሰጠው ይህ ማነው? ምድራዊ ሥጋን የተዋሐደ ይህ ማነው? እርሱ ግን ሰማያዊ ነው:: በሚለወጥ ባሕርይ የተወለደ ይህ ማነው? እርሱ ግን የማይለወጥ ነው?::

ከሕግ ልዩ የሆነ ይህ ማነው? ከእኔ ዘንድ የነበሩ አሕዛብን ከወገኖቼ ለይቶ የሚማርካቸው ይህ ማነው? ከሞት ጋር የሚሰላለፍ ይህ ማነው? በነደ እሳት ኃይል ማነው? ጨለማን የተመሉ መቃብርና ሲኦል ይዘው ሊያስቀሩት ያልተቻላቸው ይህ ማነው?... ያለ ኃጢአት የሞተ ይህ ማነው? በብርሃኑ የነጸብራቅ ኃይል የጨለማውን አቢጋዝ ዕውር ያደረገው ይህ ማነው? ወገኖቼን እገዛ ዘንድ ያልተወኝ ይህ ማነው? ነገር ግን ተሰጥተውኝ የነበሩት ነፍሳትን ሁሉ ወደ ሰማይ ያወጣል እንጂ... ሕፀፅ የሌለበት ይህ ብርሃን የሚከበው ማነው? ወገኖቼን እንዳላጠፉ የሻረኝ በርሱ ላይ ሰልጥኜ የምኀዳው ሥልጣን የሌለኝ ይህ ማነው? ይህስ የተሰቀለው ኢየሱስ ክርስቶስ ነው በግራ የነበረው ወደ ቀኝ የተዛወረበት...» /ትምህርተ ኅቡአት ም. 123/





ደግሞስ ከእኛ ጋር ያለው ከእርሱ ጋር ካለው እንዲበረታ ታውቃላችሁ? ዲያብሎስን ድል የነሱ ብርሃናውያን መላእክት አይደሉምን? ይህን ባለ ራእዩ ዮሐንስ ሲናገር እንዲህ አለ «በሰማይ ሰልፍ ሆነ ሚካኤልና መላእክቱ ዘንዶውን ተዋጉ ዘንዶውም ከመላእክቱ ጋር ተዋጋ አልቻላቸውም... ወደ ምድርም ተጣለ» /ራእ. ዮሐ. 12÷7/ ይህን ቃል አስተውላችሁታል? የክርስቶስን ሥጋና ደም በመቀበል በከበረው ሰውና በሚካኤልና በሠራዊቱ በሚጠበቅ ክርስቲያን ፊት ዘንዶው ያ የቀደመው እባብ መቆም እንደማይችል?

## ያላገባ ሰው መቁረብ ስይገባውም

በመሠረቱ ጋብቻ ቅዱስና በእግዚአብሔርም ሆነ በሰው ፊት ሕጋዊነት ነው:: ሆኖም ግን ማግባት ብቻውን ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ለመቀበል ብቸኛ መስፈርትና የብቃት ደረጃ ነው ብለው የሚገምቱ አማኞች የተሳሳቱ ናቸው:: ምክንያቱም በጋብቻ ውስጥ ሆነው ንስሐ የሚያስፈልገው ብዙ ኃጢአት ያለባቸው ሰዎች ስላሉ በጋብቻ ተወስነናልና እኛ ለሥጋ ወደሙ ብቁ ነን ማለት አይችሉም::

ብዙ ጊዜ ያላገባ ሰው መቁረብ እንደሌለበት የሚስማሙ ሰዎች ምክንያታቸው ያላገባ ሰው በሕግ ስላልተወሰነ በዝሙት ይወድቃል:: በኃጢአት ሰውነቱን ያረክሳል የሚለውን ነው::

በእርግጥ ይህ አባባል ትክክል የሚሆንበት ጐን ቢኖርም በሌላ መልኩ አንድ ሰው ቅዱስ ሥጋውንና ክቡር ደሙን ሳይቀበል ሕግ ቢያፈርስ ዝሙት ቢፈጽም አምላኩን የመበደሉ ሁኔታ ምንም ማለት አይደለም እንደማለት እንደሆነ አያስተውሉትም::

ቅዱስ ቁርባን ተቀበለም አልተቀበለም ይህን ኃጢአት ቢፈጽም ለንስሐ እስካልበቃ ድረስ ቅጣቱ ደረጃ እንደሌለው ሊያውቁት ይገባል:: ስለዚህም የእግዚአብሔር ቃል እንዲህይላል





«ከዝሙት ሽሹ ሰው የሚያደርገው ኃጢአት ሁሉ ከሥጋ ውጭ ነው ዝሙትን የሚሠራ በገዛ ሥጋው ላይ ኃጢአትን ይሠራል:: ወይስ ሥጋችሁ ከእግዚአብሔር የተቀበላችሁት በእናንተ የሚኖረው የመንፈስ ቅዱስ ቤተ መቅደስ እንደሆነ አታውቁምን?» /1ቆሮ. 5÷18-20/ በዚህ መሠረት በማናቸውም ሁኔታ ሆነ ጊዜ ቤተ መቅደሱን በዝሙት ማርከስ የተከለከለ ነው::

አንድ ሰው ባያገባም ከዝሙት እርቆ ከሌሎችም ኃጢአቶች ተጠብቆ በሠራውም ኃጢአት ንስሐ ገብቶ በምክረ ካህን ሆኖ ሥጋውንና ደሙን ሊቀበል ይገባዋል:: ማንኛውም ምእመን ለቅዱስ ቁርባን ከኃጢአት የራቀ ሕይወት ሊኖረው ይገባል:: ይህ ማለት ግን ያገባና ያላገባ በማለት መለየት አይደለም:: አለማግባትን ለሥጋ ወደሙ አለመብቃት ማግባትን ደግሞ ለሥጋ ወደሙ እንደ መብቃት መውሰዱ በራሱ የሳሳተ ግምታዊ አባባል እንጂ የወንጌሉ ቃል የቤተ ክርስቲያኗም ትምህርት አይደለም:: ማንኛውም ሰው ለአቅመ አዳምና ሔዋን ሲደርስ በውስጡ ከሚፈጠረው ፈቃዱ የተነሣ በዝሙት እየወደቀ አምላካዊ ሕጉን ከማፍረሱም የተቀበለውን የክርስቶስን ሥጋና ደም እንዳይበድል በሕግ ተወስኖ በዚህ ኃጢአት በኩል ከርኩሰት እርቆ ለሥጋ ወደሙ ዝግጁ ሕይወት እንዲኖረው ያደርገዋል::

በዚህ ደግሞ የክርስቶስን አካል ወስዶ የጋለሞታ አካል ከማድረግ መጠበቅ ይሆናል:: ቅዱስ ጳውሎስ «ሥጋችሁ የክርስቶስ ብልቶች እንደሆኑ አታውቁምን? እንግዲህ የክርስቶስን ብልቶች ወስጄ የጋለሞታ ብልቶች ላደርጋቸው አይገባም» /1ቆሮ. 6÷15/ ይላል::

እንግዲህ ከዝሙት እርቆ ንጽሕ ጠብቆ ለመቀበል የማይችል ቢኖር ከሕግ ወጥቶ እየበደለ ያለ ስለሆነ ከበደሉ ሊመለስ ከዝሙት ሊሸሽ በዚህ ኃጢአት የሚጠቃ ከሆነ በፈቃዱ ከመቃጠል ሊያገባ ይገባዋል:: በጭፍን ግን ያላገባ ሊቆርብ አይገባውም ማለት አማኙን ማደናገርና የሳሳተና ሰው ወለድ

ትምህርት ስለሆነ ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን ከሰጠ በት አምላካዊ ምሕረትና ከወንጌሉ ቃል ጋር ይቃረናል «እንካችሁ ብሉ ይህ ሥጋዬ ነው አለ ጽዋውንም አንስቶ አመስግኖ ሰጣቸው እንዲህም አለ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢ አት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው::» /ማቴ. 26÷26-27/

## ነፍሰ ጡር ሴት መቁረብ ስይገባትም

«እግዚአብሔር ባረካቸው እንዲህ ብሎ ብዙ ተባዙ ምድርን ሙሉአት» /ዘፍ. 1÷28/

ይህን አባባል የሚጠቀሙት ሰዎች ኃጢአት ሊያደርጉት የፈለጉት ጉዳይ የትኛው እንደሆነ ግልጽ አይደለም ወይም ያስከትላል ብለው የሚፈሩት ነገረ ብዙም ባይታወቅም ይሁንና ከአጉል ባህል በመነጨ አስተሳሰብ እንዲህ ሊሉ እንደሚችሉ መገመቱ አያዳግትም::

እስኪ ልብ በሉ በማህፀን ጽንስን የሚያከናውን ማን ነው? በማህፀን ያለው የጽንሱ ሕልውናስ በማን ላይ ነው? በረጋው ደም አጥንት ሰክቶ ወደ ህያውነት የሚያመጣውስ ማን ይመስላችኋል? ታዲያ ፈጣሪ አምላክ ልዑል እግዚአብሔር አይደለምን? ወይስ ነፍሰ ጠ እግዚአብሔር ከጽንሱ ጋር ምን መቃረን አለው? ወይስ ነፍሰ ጡሯ ሴት በመጽነሷ በእግዚአብሔር ፊት እንድትጠላ የሚያደርጋት ምንድን ነው? ነፍሰ ጡር ሴት ለሥጋ ወደሙ ብቁ የሆነ ሕይወትና ዝግጅት ካላት ለመቁረብ የምትከለከልበት ምክንያት አይኖርም::

ገና በጥንተ ተፈጥሮ እግዚአብሔር የሰውን ልጅ ሲፈጥር የባረከበት መንገድ «ብዙ ተባዙ ምድርንም ሙሉአት» ብሎ ነው ይህ ቃል ደግሞ እስከ ዓለም ማለፍ የሰው ልጆችን ሲበዙ ሊዋለዱ እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል የክርስቶስም ደም የፈሰሰው ከእርሱ መስቀል በኋላ ወደዚች ዓለም ለሚመጡት ሁሉ ነው::





እርሱ ሰውን ከእናቱ ማህፀን ጀምሮ ይጠብቃል ይመርጠውማል ወደ ኤርሚያስ የመጣው የእግዚአብሔር ቃል ይህን ያረጋግጥልናል "በሆድ ሳልሰራህ አውቄሀለሁ ከማህፀንም ሳትወጣ ቀድሼሀለሁ ለአሕዛብም ነብይ አድርጌአለሁ" /ኤር 1÷4/ በተጨማሪም ፈጣሪ ፍጥረታት እግዚአብሔር አምላክ በማህፀን ባለ ጽንስ እንኳ የታወቀና የተገለጠ ነው:: በካህኑ በዘካርያስ ሚስት በቅድስት ኤልሳቤጥ ማህፀን የነበረውን የስድስት ወር ጽንስ እናቱ የክርስቶስን እናት ሰላምታ በሰማች ጊዜ በደስታ መዝለሉ /መስገዱ/ በእናቱ አማካኝነት ተመስክሯል:: /ሉቃ 1፥44/ "እነሆ የሰላምታሽ ድምጽ በጆሮዬ በመጣ ጊዜ ፅንሱ በማህፀኔ በደስታ ዘሎአልና" እንግዲህ ነፍሰ ጡር ሴት ብትቆርብ እርሷ እንዲያ ትሆናለች ጽንሱ እንዲህ ይሆናል የሚለውን ባህል ያመነጨውን አባባል የወንጌል ቃል አለመሆኑን ለማረዳት አያዳግትም በመሠረቱ ሴትም ሆነች ወንድ ሥጋ ወደሙ ሊቀበሉ የሚያስችላቸውን ሁኔታና ጊዜ በምዕራፍ አምስት ዝግጅት በሚለው ክፍል ተብራርቶ ቀርቧል ይመልከቱት::

## "በሥርዓተ ተክሊል ጋብቻቸው ያልተፈፀመ ሰዎች መቁረብ አይችሉም"

"መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር መኝታውም ንጹህ ይሁን" /ዕብ 13፥4/ የክርስቲያኖች ጋብቻ ሲፈጸም የሚገባው በጸሎተ ተክሊል ክብሮ በቅዱስ ሥጋውና ደሙ ተቀድሶ ነው:: ይሁንና በአንድም በሌላ ሁኔታ ከሥርዓተ ተክሊል ውጪ ጋብቻቸውን የፈጸሙ ሁሉ በደፈናው ጋብቻቸውን ያልሰመረ ማድረግ ሕብ ጋብቻነቱን ማፍረስ፣ ሥጋውንና ደሙን የመቀበል እድል እንደሌላቸው የሚነገረው ወሬ ተራ አባባልና የዚሁ የጥንተ ጠላታችን የሽንገላ ውጊያ ነው::





ጋብቻቸውን በስርዓተ ተክሊል በቅዱስ ቁርባን ያልፈጸሙ ባለ ትዳሮች ጋብቻቸውን ወደ ቅድስና እንዳያመጡና በቅዱስ ቁርባን እንዳይከብሩ በዚህም ላይ ለነፍሳቸው መዳን የመጨረሻው ዋስትና ከሆነው ቅዱስ ቁርባን በሩቅ ለማጠር ለጠላት ውጊ ልዩ ኃይል ፈጥሮሲታል::

«መጋባት በሁሉ ዘንድ ክቡር ይሁን መኝታውም ንጹህ ነው» እንዳለ አንድ ለአንድ በሕግ ከተወሰኑና ከማመንዝር ተጠ ብቀው በመምህረ ንስሐቸው ምክር እየተመሩ በንስሐ እየታነጹ ቅዱስ ቁርባን የማይቀበሉበት ምንም ምክንያት አይኖርም::

እንዲያውም ጋብቻቸውን በሥርዓተ ተክሊል ባለመፈጸማ ቸው የዚህ ጸጋ ባለቤቶች አልሆንም እያሉ ከህሊና የተነሣ ከሚሰቃዩ ጋብቻቸውን በቅዱስ ቁርባን ሊቀድሱ ሊጠብቁ በቤተ ክርስቲያኒቱ አውደ ምሕረት በምእመናኑ ጉባኤ ፊት ሊከብሩ ይችላሉ::

በጋብቻ የሚኖሩ ሰዎች አንድ ሥጋ ስለሆኑ በምናገባኝ ያለ ስምምነት ያለ ምክረ ካህን ባለመግባባትም ተለያይተው ሊቆርቡ አይገባቸውም:: «ሁለቱ አንድ ሥጋ ይሆናሉ» /ማቴ. 19÷5፣ ዘፍ. 2÷24/

በተጨማሪ እንደማስረጃ የምጠቅሰው በቤተ ክርስቲያን ሥርዓት እንኳ ለሥርዓተ ተክሊል የሚያበቃ ሕይወት የሌላቸው በድንግልና ያልኖሩ /በማስባን ጋብቻ/ በጸሎተ ንስሐና በቅዱስ ቁርባን ሥርዓተ ጋብቻቸው ተፈጽሞ ሥጋ ወደሙ በቀረቡ ጊዜ ሁሉ ስታቀብላቸው ትኖራለች::

## ፍቅረኛሽ እንዳይከዳሽ ተያይዛችሁ ቁረቡ

እንዲህ ዓይነቱ ምክር የሚሰማው ከቤተ ክርስቲያን ወይም ከመንፈሳውያን አገልጋዮች ሳይሆን ከአማኙ ወይም በአዲሱ ትውልድ ዙሪያ የሚሰማ ስህተት ነው::





ዛሬ ዛሬ ብዙ ወጣቶች በመተጫጨት ዙሪያ ወይም በፍቅር ሕይወታቸው ጉዳይ ቅዱስ ቁርባንን እንደ ቃል ኪዳን ወይንም በራሳቸው ውስጥ እንዳለው ግምት ማሠሪያ ነው ብለው ስለሚያምኑ ሕጋዊነቱ ባልተጠበቀ መንገድና አካሄድ ባሰኛቸው ጊዜ ተነስተው ሲቆርብና «ቆርባልኝ ቃል ኪዳን ገብታልኝ ከዳችኝ» ሲሉና ከገቡበት ውስብስብ ችግር መውጣት አቅቷቸው «ሳይገባቸው» ተቀብለው በራሳቸው ላይ ሲያስፈርዱ ይገኛሉ:: /1ቆሮ. 11÷27/

በዚህ ነጥብ ልገልጽ የምፈልገውን ቁም ነገርና ሳቀርብ የምፈልገውን ማብራሪያ በሁለት ከፍዬዋለሁ፤

ሀ. ቃል ኪዳን ያለ ሕጋዊነት አካሄድ ተፈጽሞ የሚኖረው ሕልውና

ለ. ቅዱስ ቁርባን ያፈቀሩትን ሰው እንደማሠሪያ አድርጎ ማሰብ ከቤተ ክርስቲያን ሕግና ሥርዓት አኳያ ሲታይ፤

ቤተ ክርስቲያንን የጐዳት ከውጪ ጠላት ይልቅ በውስጥ ያሉ ያልገባቸውን ጠይቀው የማይረዱ፣ በግምት የሚጓዙ፣ ለራሳቸው ሕግና ሥርዓት አውጥተው የቤተ ክርስቲያኗን ሕግና ሥርዓት የሚቃረኑና ወደጐን የጣሉ፣ አውቆ አጥፊዎችና ለሌሎች እንቅፋት የሆኑ ሰዎች መሆናቸው አያጠራጥርም ይህም ከላይ ጠ ቅሼ ማብራሪያ ያቀረብኩበት አባባል በቤተ ክርስቲያኗ ውስጥ በግምት ከሚጓዙ ጠይቀው ከማይረዱ ለራሳቸው ሕግና ሥርዓት ከሚያወጡ ሰዎች ዙሪያ መሆኑን አስቀድሜ መግለጤ ከዚህ በታች ለማቀርበው ማብራሪያ እንደ ማስረጃ ይጠቅመኛል::

ሀ. ቃል ኪዳን ያለ ሕጋዊነት አካሄድ ተፈጽሞ የሚኖረው ሕልውና

በሁለቱ ተቃራኒ ጾታዎች መካከል ባልጠበቁበት ሁኔታም ሆነ በቅድመ ዝግጅት መተሳሰብ አልፎም መፈቃቀር ሊከሰት

ይችላል:: ይህም ሁኔታ በራሱ ሕይወት ዘርቶ በመካከላቸው የጠበቀ ግንኙነት እንዲኖር ያደርጋል::

ይሁንና ይህን ሁኔታ ወደ ሕጋዊነት መተጫጨት ለማምጣት የሚፈልጉ ከሆነ የቤተ ክርስቲያኗም ሥርዓት የአገሬቷም ባሕል እንደሚያውቀው ሁለቱም ቤተሰቦቻቸው እንዲያውቁት ሽማግሌዎች ሊልክ ከሚገባው ክፍል ሽማግሌዎችን በመላክ ለወላጆች አሳውቀው የፈቃድ ስምምነት ከተፈጸመ በኋላ ወደ ካህን ቀርበው ፈቃዳቸውን በማሳወቅ በቀለበት ሥነ ሥርዓት ቃል ኪዳናቸውን ተለዋውጠው በመቁረብ ከዚህም በኋላ በምክረ ካህን እየተመሩ እስከ ጋብቻቸው ዕለት ከፍካቤ /ከግንኙነት/ ርቀው በየራሳቸው ሲቀበሉ መኖር ቃለ ኪዳናቸውን ሕጋዊነት ሰጥቶት ሲጠበቅ እንዲኖርና በኋላም እንዲጸና ያደርገዋል::

ነገር ግን ሁለቱ ብቻ ያለ እማኝ /ታዛቢ/ በሜዳ ቃል ኪዳን ለጊዜው በሥጋ ስሜት ታውረውና በግምታዊ እውቀት እየተነዱ በመጓተት «እንዳትከዳኝ እንቁረብ» «እንዳትከጂኝ እንቁረብ» በመባባል ወደ ቅዱስ ቁርባን መቅረብ ለተወሳሰበ ችግር ራስን ማጋለጥና ለከፋ በደል ራስን መዳረግ ነው::

ሌላው እነርሱ ገብተናል ወይም ተለዋውጠናል ብለው የሚገምቱት ቃል ኪዳን የተፈጸመው ያለ ሕጋዊነት ስለሆነ በመካከላቸው ሊቆም ወይም አንዱን ክፍል ከቃል ኪዳኑ ውጭ እንዳይሆን የሚያግደው ነገር ስለሌለ ቃል ኪዳኑ ሕልውና ስለሌለው እንዳፈጻጸሙ ሁሉ በየሜዳው ይቀራል::

የሚያሳዝነው ግን ቅዱስ ቁርባን መግባትና መጠቀስ በሌለበት ቦታና ሁኔታ እንዲፈጸም መደረጉ ያለ ዓላማው ስለሆነ በነፍስ በሥጋ ያስፈርዳል «ሰው ግን ራሱን ይፈትን... ሳይገባው የሚበላና የሚጠጣ የጌታን ሥጋ ስለማይለይ ለራሱ ፍርድ ይበላልና ይጠጣልምና ስለዚህ በእናንተ ዘንድ የደከሙና የታመሙ ብዙዎች አሉ አያሌዎችም አንቀላፍተዋል ራሳችንን ብንመረምር ግን ባልተፈረደብንም ነበር፤» /2ቆሮ. 11፥28-31/





ስለዚህ በዚህ አስተሳሰብና ግምታዊ ዕውቀት ተገዝተን የተሳሳትን ብንኖር በንስሐ ልንመለስ ከቁጣው ልንድን ይገባል:: ይሁንና ግን ከዚህ ከተሳሳተ አካሄድ በተለየ በመተጫጨትም ይሁን በፍቅር እንኖራለን የምንል በምክረ ካህን እየተመራን በንስሐ እየነጻን በቅዱስ ቁርባን ተወስነን መኖር ተገቢ ነው::

### ለ. ቅዱስ ቁርባንን ያፈቀሩት ሰው እንደማሠሪያ አድረጎ ማሰብ ከቤተክርስቲያን ሕግና ሥርዓት አኳያ ሲታይ

ክርስትና በታማኝነት ውስጥ የሚገለጥ ሕይወት ነው ታማኝነት ደግሞ በፈሪያ እግዚአብሔር የሚጠበቅ አቋም ነው አንድን ሰው ስላቆረቡት ብቻ ታማኝ ይሆናል ብሎ መጠበቁ ትልቅ ስህተት ነው:: ይሁዳ ለምን ለክርስቶስ ታምኖ አልተገኘም? /ሉቃ. 22፥2/

ቅዱስ ቁርባን እንደማሰሪያ ወይም አንድን ሰው አስፈራርቶ እንደመያዣ መቁጠር ቅዱስ ቁረባን ከተሰጠበት ክርስቶስ ቅዱስ ሥጋውን ከቆረሰበት ክቡር ደሙን ካፈሰሰበት ዓላማ ጋር የሚቃረን ከስህተት ጉድጓድ የሚጨምር አስተሳሰብ ነው::

በመጀመሪያ የመተጫጨት ወቅት እንደጋብቻ ወቅት የሚወሰድ አይደለም የመተጫጨት ዓላማ ወይም ትርጉም የመጠናናት የመጠባበቅ ጊዜ ነው ምን አልባት እርስ በእርስ በሚያደርጉት መጠናናት ባለመስማማት ግንኙነታቸው የሚቋረጥበት ሁኔታ ሊኖር ይችላል::

በሌላ መልኩ ለራሱና ለቃሉ ታማኝ ያልሆነን ሰው በየትኛውም መልኩ በምንም ዓይነት ሁኔታ አስፈራርቶ ወደ ታማኝነት ማምጣት አይቻልም በራሱ የታማኝነትን ጥቅም አውቆትና ለዘላቂነቱ ወስኖ ሊገባበት የሚኖረው ውጤት ጥሩ ሊሆን ይችላል:: ስለዚህ ይህ ዓይነቱ አስተሳሰብ ከቤተ ክርስቲያን ሥርዓትና ሕግ አንጻርም ቢታይ ስህተታችንን የጐላ ያደርገዋልና ልንታረም ይገባል::





# ምዕራፍ አሥራሁለት

## ቅዱስ ቁርባንን እንደ ጉጂ መቁጠርና ሸሽቶ መኖር

ስለ ግብፅ ኦርቶዶክሳውያን ክርስቲያኖች ካነበብኩት ጥቂቱን ልጥቀስ «በእነርሱ ዘንድ ንስሐን ማሳደር፣ ቤተ ክርስቲያን አስቀድሶ ሳይቆርቡ መውጣት አልተለመደም::» የሚል ነው::

ደግሞ ቅዳሴ ለመግባት ከቤተልሔም ተነስተን ወደ ቤተ መቅደስ ስንገባ እንዲህ እናዜማለን «ሃሌ ሉያ እመቦ ብእሲ እም ምእመናን ዘቦአ ቤተ ክርስቲያን በጊዜ ቅዳሴ ወኢሰምዐ መጻሕፍተ ቅዱሳተ ወኢተዐገሠ እስከ ይፌጽሙ ጸሎተ ቅዳሴ ወኢተመጠወ እምቁርባን ይሰደድ እም ቤተ ክርስቲያን»

የግዕዙ ትርጉም «ሃሌ ሉያ በቅዳሴ ጊዜ ከምእመናን ወገን ወደ ቤተ ክርስቲያን የገባ ሰው ቢኖር ቅዱሳት መጻሕፍትን ሰምቶ የቅዳሴውን ጸሎት እስኪጨርሱ ባይታገሥ ከቁርባንም ባይቀበል ከቤተ ክርስቲያን ይለይ» ማለት ነው::

በተጨማሪ ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ያስተማረው ወንጌላዊው ቅዱስ ዮሐንስ የመዘገበው የወንጌሉ ቃል እንዲህ ይላል «አባቶቻችሁ በምድረ በዳ መና በሉ ሞቱም ሰው ከእርሱ በልቶ እንዳይሞት ከሰማይ አሁን የወረደ እንጀራ ይህ ነው:: ከሰማይ የወረደ ሕያው እንጀራ እኔ ነኝ ሰው ከዚህ እንጀራ ቢበላ ለዘላለም ይኖራል እኔም ስለ ዓለም ሕይወት የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው::» /ዮሐ. 6፥49-51/

ክርስቲያኑን ሕዝብ ከቅዱስ ቁርባን ያርቀዋል ሊያውቀው ይገባል በምለው አስፈላጊ ነጥብ ወደ ኋላ ባሉት ምዕራፎች አስፈላጊውን ማብራሪያና ማስረጃ ለማቅረብ ሞክሬአለሁ::

ይሁንና አብዛኛው ሕዝበ ክርስቲያን ቅዱስ ቁርባንን ከጥቅሙ ይልቅ በራሱ ግምት የሚያስበውን ጉዳት መቁጠርና





ሸሽቶ መኖር በውስጡ የጸና ትክክል ድንጋይ ሆኖ ሕይወቱን ሲጐዳውና መጻኛውን ሲያሳጣው ማየቱ ቤተ ክርስቲያንን በጥልቀ እንድታዝን ያደርጋታል::

ቅዱስ ቁርባንን እንደ ጉጂ ቆጥሮ ሸሽቶ መኖር የድህነትን መንገድ መሸሽና የእግዚአብሔርን ጸጋ መጋፋት ብቻ ሳይሆን ከዚህ በታች ያቀረብኳቸው ነጥቦች በውስጡ ይካተቱበታል::

### ትዕግሥቱን መናቅ ነው

«... የእግዚአብሔር ቸርነቱንና የመቻሉን የትዕግሥቱንም ባለ ጠግነት ትንቃለህን?» /ሮሜ. 2፥4/

በሰው ልጆች የወደፊት ድህነት ውስጥ ትልቁን ሥፍራ የሚይዘው የእግዚአብሔር ትዕግሥት ነው:: እግዚአብሔር በባሕሪው ታጋሽ ነው:: ትዕግሥቱ ደግሞ እግዚአብሔር ሰዎች እንዲያገኙት ለሰጣቸው ጸጋ ያበቃቸዋል::

እግዚአብሔር በሕይወትህ ውስጥ ምን ያህል ጊዜ እንደ ታገሠህ አስበኸው ታውቃለህ? አንተ ማን እንደሆንክ ያውቃል? ፈጽሞ ከሠራሀቸው ኃጢአቶች አንዷም ከፊቱ ተሰውራ አታውቅም ትዕግሥቱ ግን አንተን ለንስሐ ለማብቃት ከባሕሪው ከሆነ ፍቅር የተነሣ የሆነ ርህራሔ ነው::

በዚህ ትዕግሥት ተስፋ ልታደርግ አንተ ወደ ንስሐ እንድትደርስ የመቻሉንና የትዕግሥቱን ባለ ጠግነት እያመሰገንህ እራስህን ለቅዱስ ሥጋውና ለክቡር ደሙ ለማዘጋጀት ከመነሳሳትና ቀርበህ ከመቀበል ይልቅ በቅዱስ ቁርባን ላይ የተሳሳተ አመለካከት መያዙና ሸሽቶ መኖሩ «ትዕግሥቱን መናቅ» ነው::

### ቸርነቱን ስለመታመን ነው

«እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና ተመልከት ጭከናው በወደቁት ላይ ነው:: በቸርነቱ ግን ጸንተህ ብትኖር

የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው፡፡ ያለዚያ አንተ ደግሞ ትቆረጣለህ» /ሮሜ. 11፥22/

ድህነታቸው በሥራቸው ብቻ እንዲሆን የሚመኩ ሰዎች ትምክህታቸው ከንቱ ነው፡፡ ከዚህም የተነሣ በቸርነቱ ጸንቶ መኖር ይሳናቸዋል፡፡ ስለ እግዚአብሔር ቸርነት ስናስብ ትዝ ሊለን የሚገባ ትልቁ ቁም ነገር መዳናችን ፈቃዱና የሚያስደስተውም መሆኑ ነው፡፡ በዚህ ላይ የኃጢአተኛውን ሞት አለመሻቱ እግዚአብሔር ቸርና ለቁጣ የዘገየ መሆኑን እንድናረጋግጥ ያደርገናል፡፡ ስለዚህ ነጥብ በኢዩኤል የትንቢት መጽሐፍ የተጻፈውን እንጥቀስ «ልባችሁን እንጂ ልብሳችሁን አትቅደዱ አምላካችሁም እግዚአብ ሔር ቸርና መሐሪ፣ ቁጣው የዘገየ ምሕረቱም የበዛ ለክፋትም የተጸጸተ ነውና ወደ ርሱ ተመለሱ» /ኢዩ. 2፥13/ ይላል፡፡

የእግዚአብሔር ቸርነት ከፍጹም ፍቅሩ የመነጨና የተገኘ ነው፡፡ የወደቀውን ሰው ለማንሳትና የቀደመውን ክብሩን ለመመለስ እግዚአብሔር ለዓለሙ ያደረገው ጸጋ አንድያ ልጁን መስጠቱ ከሰው በተገኘ በእግዚአብሔር ፊት በታየ ትጋት ሳይሆን እግዚአብሔር ሰውን በቸርነቱ ተመልክቶ በፍቅር ያደረገው መሆኑን ዮሐንስ አረጋግጦልናል «በርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» /ዮሐ. 3፥16/

እምነትህ ያለሥራ ሊገለጥና ሕይወት ሊኖረው እንደ ማይችል የታመነ ቢሆንም ሥራህ ግን በፊቱ ተቀባይነት የሚ ኖረው ቸርነቱ ታክሎበት ነው፡፡ እዚህ ላይ የተወሰኑ ጥያቄዎችን ላንሳ ቸርነት ምንድር ነው? የቃሉስ ትርጉም? ቸርነት፣ ደግነት፣ ታጋሽነት፣ ለጋስነት ማለት ነው የቃሉም ትርጉም ይኸው ነው፡፡ በደግነት በለጋስነት ብድራትንና ዋጋን ያለመፈለግ የመስጠትን ሁኔታ ቸርነት እንለዋለን፡፡ እግዚአብሔር ይህን ቸርነት ለሰው እንዳሳየ ተጽፎልናል፡፡ መዝሙረኛው እንዲህ ብሏል፡፡ «ጽድቅንና





ፍርድን ይወድዳል የእግዚአብሔር ቸርነት ምድርን ሞላች፡፡» /መዝ.33፥5/

ስለዚህ እግዚአብሔር ከዚህ ቸርነቱ የተነሳ ለሰው ልጅ መልካም አደረገ /መዝ. 145፥8-9፣ ማቴ. 5፥44/ ከደግነቱና ከለጋስነቱ የተነሣ «ሥጋዬን የበላ ደሜን የጠጣ የዘላለም ሕይወት ያገኛል» ብሎ ቅዱስ ቁርባንን ሰጠ ይህን መሸሽና ቃሉን መቃወም በራስ ላይ ማስፈረድና «ቸርነቱን አለመተማመን» ራስን ለእግዚአብሔር ፍርድ አሳልፎ መስጠት ነው፡፡

## ፍቅሩን ስለመረዳት ነው

«ስለ ወዳጆቹ ራሱን ለሞት አሳልፎ ከመስጠት ከዚህ የሚበልጥ ፍቅር ለማንም የለውም» /ዮሐ. 15፥13/

ታላቁ ሰው ሊቁ ዮሐንስ አፈወርቅ እግዚአብሔር ለሰው ልጆች ስለ ገለጣት ፍቅር እንዲህ አለ፡፡ «ፍቅር ሰአቦ ለወልድ ኃያል እመንበሩ ወአብፅኦ እስከለሞት» ማለት ፍቅር ኃያል ወልድን ከሰማያት ዙፋኑ አወረደው ነው፡፡ ይህ ፍቅር ደግሞ እግዚአብሔር በደለኛውን ሰው /ዓለሙን/ የወደደበት ፍቅር ነው «... እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና፡፡» /ዮሐ. 3፥16/

ይህ ክርስቶስ እኛን ከመውደዱ የተነሣ በፍቅር ካደረገልን መካከል አንዱና የመጀመሪያውን ደረጃ የሚይዘው ስለ ሁላችን ራሱን በመስቀል ላይ መሥዋዕት አድርጎ ማቅረብ ነው፡፡ ሐዋርያው ጳውሎስ ይህን ሲያረጋግጥ «ፋሲካችን ክርስቶስ ታርዷልና» /1ቆሮ. 5፥7/ ብሎ ጽፎልናል፡፡ ክርስቶስ ደግሞ የታረደው ለመዳናችን ነው፡፡ ለዚህም ነው ወደዚህ የሕይወት ገበታ የጠራን «እኔ ስለዓለም የምሰጠው እንጀራ ሥጋዬ ነው» ብሎ /ዮሐ. 6፥ 51/ ይህን የሕይወት እንጀራ ቅዱስ ቁርባን በነፍስ በሥጋ መዳኛዬ ብሎ ምርጫውን ያላስተካከለ ክርስቲያን ምን





ያህል የተጐዳና እግዚአብሔር ለርሱ ያለውን ፍቅር ያልተረዳ ነው፡፡

## መድኃኒትነቱን ስለማወቅ ነው

«በጸጋው ጸድቀን በዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንድንሆን በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ በእኛ ላይ አትርፎ አፈሰሰው፡፡ ቃሉ የታመነ ነው» /ቲቶ. 3፥6-7/

ከዘላለም ፍርድና ከባርነት ሕይወት ያድነን ዘንድ ክርስቶስ ወደ ዓለም በመጣ ጊዜ በሰማያውያን መላእክት በታወጀው አዋጅ መድኃኒቲነቱ ተመስክሯል «ዛሬ በዳዊት ከተማ መድኃኒት የሆነ እርሱም ክርስቶስ ተወልዶላችኋል» /ሉቃስ. 2፥11/

እርሱም ሁላችንን ከኃጢአትና ከዘላለም ሞት አዳነን ስለ እርሱም ሐዋርያት በስፋት መድኃኒታችን እያሉ ፅፈዋል/ ቲቶ 1፥4.፣ 2ጢሞ. 1፥1/ ስለክርስቶስ አዳኝነት ስንናገር የምናስምርበት ቁም ነገር መድኃኒትነቱ ለሰው ሁሉ ስለሆነ የዓለም መድኃኒት /አዳኝ/ መባሉን ነው፡፡ /ዮሐ.4፥42፣ 1ዮሐ. 4፥14/

እንግዲህ በዚህ ነጥብ ማስገንዘብ የፈለግሁት ክርስቶስ ስለ ሁላችን በደል በመስቀል በመሞቱ፡ ደህንነታችን ሆነ ሥጋውንም ቆርሶ ደሙንም አፍሶ ከሞት ወደ ሕይወት ከጨለማም ወደ ሚያስደንቅ ብርሃን መለሰን ይህ ከፍቅሩ የተነሳ ለሰው ልጆች የታደለ ጸጋ ሲሆን በእያንዳንዳችን ሕይወት ቦታ አለማግኘቱ መድኃኒትነቱን ካለማወቅ የተነሳ ነው፡፡ እግዚአብሔር ለደህንነታ ቸው አምነው ቅዱስ ቁርባንን ለሚመርጡ የዘላለም ሕይወት ተስፋ ወራሾች እንደሆኑ በታመነው ቃሉ አረጋግጦልናል፡፡





# ምዕራፍ አሥራሦስት

## የቅዱስ ቁርባን ጥቅም

❖ ዘላለማዊ ድህነት እንቀበልበታለን

«ኢየሱስ እንዲህ አላቸው እውነት እውነት እላችኋለሁ የወልድ እጓለ እመሕያው ክርስቶስን ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም» /ዮሐ. 6፥53/

ይህ ቃል ሊለወጥ ሊሻሻል የማይችል የራሱ የሰው ልጆች የመዳን ራስ የሆነው የክርስቶስ ቃል ነው፡፡ «ካልበላችሁ ካልጠጣችሁ» ሕይወት የላችሁም የሚለው ኃይለ ቃል ያለ ሥጋ ወደሙ ድህነት እንደሌለ የሚያረጋግጥ ቃል ነው ለዚህ ደግሞ የዘላለም ሕይወት እንድናገኝ ወደዚህ ዓለም በመጣውና በሥጋ ማርያም በተገለጠው በእግዚአብሔር የባሕርይ ልጅ ማመን አምኖም እንዲህ ያለውን ክብርና ሕይወት የሚያስገኝ ትዕዛዙን መፈጸም ይገባል «ብትወዱኝስ ትዕዛዜን ጠብቁ» /ዮሐ. 14፥15/

ይህንን ቃል በመሠረታዊነት ከድህነታችን ጋር የተያያዘ መሆኑን ለማስገንዘብ እሞክራለሁ ይህ ቃል /ትዕዛዙ/ ልክ በዮሐንስ. 3፥5 ላይ «ሰው ከውኃና ከመንፈስ ካልተወለደ በቀር ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊገባ አይችልም» እንደሚለው ድህነትን የሚመለከት ነው፡፡

ስለሥጋ ወደሙ ክርስቶስ በሰጠው ትምህርቱ ላይ የምናገኘው ኃይል ቃል ከላይ እንደጠቀስኩት «ካልበላችሁ ካልጠ ጣችሁ ሕይወት የላችሁም» የሚል ነው፡፡ ይሔውም ስለ ዓለም ድህነት በመስቀል ለይ የቆረሰውን ሥጋውንና ደሙን ነው፡፡

በተጨማሪ አንባብያን ልብ እንዲሉት የምገልጸው ስለ ቅዱስ ሥጋውና ክቡር ደሙ ያስተማረውን ትምህርት ወንጌላዊው ዮሐንስ በስፋት ጽፎት እናገኘዋለን፡፡ /ዮሐ. 6፥35-71/ ጌታችን በዚህ ትምህርቱ አስረግጦ የገለጠው በመጨረሻው የትንሣኤ ጊዜ

ለድህነት እንደሚያበቃ ነው ሥጋውን ስለ በላ ደሙን ስለጠጣ ሰው ሲናገር በተደጋጋሚ «በመጨረሻም ቀን አስነሳዋለሁ» ብሏል /ዮሐ. 6፥39-40-47/

## ኃጢአታችን ይሰረይበታል

«ጽዋንም አንሥቶ አመስግኖም ሰጣቸው እንዲህም አለ ሁላችሁ ከእርሱ ጠጡ ስለ ብዙዎች ለኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ይህ ነው» /ማቴ. 26፥27/ «በእውነት አምነው ከርሱ ለሚቀበሉ ሕይወትና መድኃኒት የኃጢአት ማስተስሪያም ሊሆን የሚሰጥ የጌታችንና የአምላካችን የኢየሱስ ክርስቶስ ክቡር ደም ይህ «እማሬ» ነው /ቅዳሴ ሐዋርያት/ በመሠረታዊነት ደም ይህ «እማሬ» ነው /ቅዳሴ ሐዋርያት/ በመሠረታዊነት

ስለዚህ ለበደለኛው ሰው ይቅርታና በኃጢአቱ ምክንያት ከእግዚአብሔር ለተለየው ሰው እርቅ ሲባልና ለካሣ የክርስቶስ ደሙ ፈሠሠ ሥጋው ተቆርሶ ይህ ደግሞ አንድ ጊዜ የሆነና የሰው ልጆችን በደል ያስወገደ ነው:: የቅዱስ ጳውሎስ መልዕክት እንዲህ ይላል «ሊቀ ካህናት በየዓመቱ የሌለውን ደም ይዞ ወደ ቅድስት እንደሚገባ ራሱን ብዙ ጊዜ ሊያቀርብ አልገባም እንዲህ ቢሆንስ ዓለም ከተፈጠረ ጀምሮ ብዙ ጊዜ መከራ ሊቀበል ባስፈለገ ነበር አሁን ግን በዓለም ፍጻሜ ራሱን በመሠዋት ኃጢአትን ሊሽር አንድ ጊዜ ተገልጦአል::» /ዕብ. 9፥25-26/

ይሁንና አንዳንድ ሰዎች በመስቀል ላይ አንድ ጊዜ በፈሰሰው የክርስቶስ ደም ድኛለሁ በዚህም ደም ታጥቤአለሁ የሚያስፈልገው ማመን ብቻ ነው:: እያሉ የቅዱስ ቁርባንን ሥርዓት ሰው ሠራሽና እንዳላስፈላጊ በመቁጠርና በማስተማር





የክርስቶስ ወንጌል ጠላቶች ሆነዋል እርሱ ራሱ ባለቤቱ ኢየሱስ ክርስቶስ የቅዱስ ቁርባንን ሥርዓት ለሐዋርያት አሳይቶ ሲሰጣቸው እንዲህ ብሏቸዋል «እንዲሁ ከእራት በኋላ ጽዋውን አንስቶ እንዲህ አለ ይህ ጽዋ ስለ እናንተ በሚፈሰው በደሜ የሚሆን አዲስ ኪዳን ነው» /ሉቃ. 22፥20/

ታደያ የዚህ ዓለም ገዢ የተባለው ዲያቢሎስ የወንጌልን ቃል የሠወረባቸውንና ክርስቶስ ለተከታዮቹ የሰጣቸውን የአዲስ ኪዳን ደሙን ሳጡና ለተቃወሙ እግዚአብሔር ይህን የድህነት መንገድ እንዲያሳያቸሙ ጸሎታችን ነው እኛ ግን ካለፈ ኃጢአት እንደምንነጻበት ከሚመጣ ኃጢአት እንደምንጠበቅበት አምነን የአዲስ ኪዳን /ማቴ. 26፥28/ ደም ባለ ጸጋዎች በመሆናችን የቤተክርስቲያንን አምላክ እያመሰገንን በዚህ እምነት ልንቀበለው ይገባል::

## ከእግዚአብሔር ጋር አንድነት ይኖረናል

«ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ» /ዮሐ. 6፥56/

ብዙ ሰዎች ከእግዚአብሔር ጋር ለመኖር ማመን ብቻ በቂ ነው ይላሉ:: ነገር ግን ይህን አባባላቸውን የሚደግፍ አንድ ቃል እንኳ በመጽሐፍ ቅዱስ አልተጻፈም::

ክርስቶስን የሚያምን ይሰማዋል እርሱ ደግሞ ከእርሱ ጋር ስላለው አንድነት ማመን ብቻ በቂ ነው አላለም «ሥጋዬን የሚበላ ደሜንም የሚጠጣ በእኔ ይኖራል እኔም በእርሱ እኖራለሁ» እርሱ ከኛ ጋር ከሆነ ደግሞ ማን ያሸንፈናል በዚህ ካሸናፊዎች ሁሉ እንበልጣለን::

## ኃይል መንፈሳዊ እንቀበልበታለን

የክርስቶስን ሥጋ በመብላታችን ደሙንም በመጠጣታችን ኃጢአትን የምንቃወምበት ኃይል እናገኛለን ሞትንም በማሸነፍ





በመጨረሻው ቀን ለክብር ትንሳኤ እንበቃለን:: /ዮሐ. 6፥39፣ 40፣ 44/

ነቢዩ እግዚአብሔር ኤልያስ አንድ ጊዜ በበላው እንጀራ በጠጣው ውሃ ኃይል መንፈሳዊ ተቀብሏል:: ከፉዋን ኤልዛቤልን ሸሽቶ በምድረ በዳ በክትክታ ዛፍ በታች ተኝቶ ሳለ የእግዚአብሔር መልአክ ዳሰሰውና ተነስተህ ብላ አለው ሲመለከትም እነሆ በራሱ አጠገብ የተጋገረ እንጐቻና በማሰሮ ውኃ አገኘ በልቶና ጠጥቶ ተመልሶም ተኛ ደግሞ የእግዚአብሔር መልአክ ቀስቅሶ የምትሄድበት መንገድ ሩቅ ነውና ተነስተህ ብላ አለው:: ተነሥቶም በላ ጠጣም:: አንዴ በበላውም ሳይርበው ሳይጠማው ሳይደክም 40 ቀንና 40 ሌሊት ተጉዟል:: ይህን ነገር ቃሉ እንዲህ ይመሰክራል:: «በዚህም ምግብ ኃይል እስከ እግዚአብሔር ተራራ እስከ ኮሬብ ድረስ አርባ ቀንና አርባ ሌሊት ሄደ::» /1ነገ.19፥1-8/

ይህ ሁሉ በኋላ ሊመጣ ላለው ምሳሌ ነው:: ስለዚህ በክርስቶስ አምነን በኃጢአታችን ንስሐ ገብተን ሥጋውን የምንበላ ደሙን የምንጠጣ ዓለምን የምናሸንፍበትና ከእርሱ ጋር የምንኖርበትን የመንፈስቅዱስ ኃይል እንቀበልበታለን:: /ዮሐ. 15/

## ክርስቲያኖችን ሁሉ እንደ አንድ አካል ያደርገናል

«አካልም አንድ እንደ ሆነ ብዙም ብልቶች እንዳሉበት ነገር ግን የአካል ብልቶች ሁሉ ብዙዎች ሳሉ አንድ አካል እንደ ሆኑ ክርስቶስ ደግሞ እንዲሁ ነው... እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና:: ሁላችንም አንዱን መንፈስ ጠጥተናል:: ...እናንተም የክርስቶስ አካል ናችሁ እያንዳንዳችሁም ብልቶች ናችሁ::» /1ቆሮ. 12፥12 ና 27/

ሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ ክርስቲያኖች በክርስቶስ ከማመናቸው የተነሣ ስላላቸው አንድነት ሲገልጽ ለቆሮንቶስ ቤተ ክርስቲያን በጻፈው መልእክቱ «እኛ ሁላችን በአንድ መንፈስ





አንድ አካል እንድንሆን ተጠምቀናልና»:: በማለት ይህን ኃይለ ቃል ተናግሯል:: እግዚአብሔር ስለ ሰው ልጆች ፍቅር በሰጠው በአንድያ ልጁ በሥጋ ማርያም በተገለጠው በኢየሱስ ክርስቶስ አምነው የተጠመቁ ክርስቲያኖች ሁሉ ከዚህ የተነሣ እንደ አንድ አካል ሆነዋል::

ቤዛ ዓለም ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ ወንጌል በምዕራፍ 17 በተጻፈው ቃሉ ደጋግሞ የሚገልጠውና በአባቱ ፊት ባቀረበው ልመና የሚገልጸው ይህንኑ የክርስቲያኖችን አንድ አካልነት ነው:: ቃሉንም ከዚህ በታች እዘረዝረዋለሁ::

«ቅዱስ አባት ሆይ እነዚህን የሰጠኸኝን እንደ እኛ አንድ እንዲሆኑ በስምህ ጠብቃቸው» /ዮሐ. 17፥11/

«ሁሉም አንድ ይሆኑ ዘንድ ከቃላቸው የተነሣ በእኔ ስለሚያምኑ ደግሞ እንጂ ስለ እነዚህ ብቻ አልለምንም» /ዮሐ. 17፥20/

«አንተ አባት ሆይ በእኔ እንዳለህ እኔም በአንተ እነርሱ ደግሞ በእኛ አንድ ይሆኑ ዘንድ እለምናለሁ እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ» /ዮሐ. 17፥22/

እነዚህ ኃይለ ቃላት የሚገልጹት ክርስቲያኖች በክርስቶስ ያላቸውን አንድነት ነው እርሱን ከማመን የተነሣ ስለሚኖራቸው አንድነት ከተመለከትን የዚህ አንድነት ፍጻሜ ክርስቲያኖች ሁሉ እንደ አንድ አካል መሆናቸው ነው::

እንደ አንድ አካልም የሚያደርጋቸው የመላእክትን ሳይሆን የአብርሃምን ዘር ይዞ በተገለጠው በኢየሱስ ክርስቶስ ባላቸው እምነት ለዘላለማዊ ድህነታቸው በመስቀል ላይ የተሠዋላቸውን የበጉን ቅዱስ ሥጋ ሲበሉና ክቡር ደሙን ሲጠጡ ነው:: ስለዚህ ሁላቸው ከተቀበሉት ከአንዱ ከክርስቶስ ሥጋና ደም የተነሣ እንደ አንድ አካል ይሆናሉ:: እንደየተሰጣቸውም ጸጋ እንደ አንድ አካለ ልዩ ልዩ ብልቶች ያገለግላሉ::

ገ ፅ 32



ይህ ደግሞ በክርስቲያኖች መካከል መለያየት መበዳደል እንዳይኖር ያደርጋል:: በወንድሙ ላይ በክፋት የሚነሣሣ በክርስ ቶስ ላይ ይነሣሣል፣ ደግሞም ወንድሙን የሚጠላ በክርስቶስ ያለውን አንድነት ረስቶታል እንጂ ራሱን ይጠላል::

ሕይወታችንን ከምሬቱ አርቆ ያጣፈጠ አማናዊው ወይን ኢየሱስ ክርስቶስ በዮሐንስ 15 ከቁጥር 1 ጀምሮ በተጻፈው ትምህርቱ የክርስቲያኖችን አንድነት በወይን መስሎ ሲገልጥ እንዲህአለ «እኔ የወይን ግንድ ነኝ፤ እናንተም ቅርንጫፎች ናችሁ» /ዮሐ. 15፥5/

ስለዚህ ስለተጠመቅን ብቻ ሳይሆን ከተቀበልነው ከመድኃኒ ታችን ከክርስቶስ ሥጋና ደም የተነሣ ለልዩ ልዩ ጸጋ ብንጠራም በየትኛውም ዓለማት ብንኖርም እንደ አንድ አካል የሚያደርገንን ጸጋ አግኝተናል::

## በሥጋ ወደሙ እንማጸንበታለን

ጌታችን መድኃኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ እንዲህ አለ «በዚያን ቀን በስሜ ትለምናላችሁ እኔም ስለ እናንተ አብን እንድለምን የምላችሁ አይደለሁም:: እናንተ ስለ ወደዳችሁኝ ከእግዚአብሔርም ዘንድ እኔ እንደወጣሁ ስላመናችሁ አብ እርሱ ራሱ ይወዳችኋልና» ዮሐ. 16÷26 ይህን ቃል አስተዋላችሁ? እንዲሁ ነው:: በስሙ እንደምንማጸንበትና እንደምናመሰግንበት ሁሉ በሥጋና ደሙ ፍጹም ተማፅኖና ምስጋና እናቀርብበታለን:: በክርስቶስ ሥምህ በቅዱስ ሥጋህ በክብር ደምህ ይቅር በለን ጠብቀን እያልን::

በኛ ዘመን ክርስቶስ ስለ እኛ በአባቱ ፊት ይማጸንልናል:: ይማልድልናል እያሉ በሥጋዌው ዘመን ለካሣ በዚህች ዓለም የፈጸመውን ዛሬም በአባቱ ቀኝ ከተቀመጠ በኋላና «የዘላለምን ቤዛነት አግኝቶ አንድ ጊዜ ፈጽሞ ወደ ቅድስት በገዛ ደሙ ገባ





እንጂ.» ተብሎ ከተጻፈ በኋላ /ዕብ. 9÷12/ እንደሚፈጽም በመቁጠ ር የሚከራከሩን ሰዎች በትክክል የክርስቶስ ሰው የመሆን ምሥጢ ርና የካሣነት አገልግሎት ያልገባቸው ናቸው::

ቤተ ክርስቲያን በኢየሱስ ክርስቶስ ስም የባሕርይ አባቱን ታመሰግናለች «በአንድ ልጅህ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም አስቀድመን አንተን እናመሰግናለን» እያለች እንዲሁ በስሙም ትማጸናለች «አምላካችን እግዚአብሔር የጌታችንና የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ አባት ካህኑን አሮንን የመረጠው በሚመሰክሩበትም ድንኳን በአንድነቱ ጉባኤ መካከል ያቆመው በመቅደሱ ቅድስናውን ይፈጽም ዘንድ ይህችውም ቅድስተ ቅዱሳን ናት::» /ሥርዓተ ቅዳሴ/ እያለች::

እንዲሁ ሁሉ ባቀረበችው መሥዋዕት በቅዱስ ሥጋውና በክብር ደሙ ለሕዝብ ተማጽኖ ታቀርብበታለች:: ሕዝብም በተቀበለው ሥጋና ደም አምላኩን ይማጸናል::

ካህኑ ሲቀበል «አ እግዚእየ ኢየሱስ ክርስቶስ ኢይኩን ዝንቱ ምሥጢርከ አበሳ ላዕሌየ አላ ይኩን ለአንጽሖ ነፍስየ ወሥጋየ» ትርጓሜው «ጌታዬ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆይ ይህ ምሥጢ ርህ በእኔ በደል አይሁንብኝ ሥጋዬንና ነፍሴን ለማንጻት ይሁንልኝ እንጂ::» በማለት ይማጸንበታል:: ይማለድበታል::

ሕዝብንም ሲናዘዝና ሲባርክ እንዲህ ይላል «በዚች ቅድስት ቤተ ክርስቲያን መጥታችሁ ተሰብስባችሁ የጸለያችሁ የጌታችንን የኢየሱስ ክርስቶስን ቅዱስ ሥጋውን የበላችሁ ክቡር ደሙንም የጠ ጣችሁ በማወቅ ወይም ባለማወቅ የሠራችሁትን ኃጢአታችሁን ይቅር ይበላችሁ:: ሥጋ መለኮት ስለሚባል ሥጋው የሕግና የሥርዓት ደም ስለሚሆን ደሙ የአሸናፊ የእግዚአብሔር ልጅ በድንጋሌ ሥጋ በድንጋሌ ሕሊናም ኅትምት የምትሆን የማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስ ባለፈው ይቅር ይበላችሁ በሚመጣውም ይጠብቃችሁ ለዘላለሙ::» /የሐዋርያት ቅዳሴ/





እንደዚሁ ሁሉ ሕዝብም በሥጋ ወደሙ ይማጸኑበታል፤ ያመሰግኑበታል:: ይኸውም «እግዚአብሔር እኛን ባሮቹን በሰላም ይባርከን የተቀበልነው ሥጋህና ደምህ ለሥርየት ይሁነን:: የጠላትን ኃይል ሁሉ በመንፈስ እንረግጥ ዘንድ አሠልጥነን ምሕረትን የተመላች ክብርት የምትሆን የእጅህን በረከት ሁላችን ተስፋ እናደርጋለን:: ከክፉ ሥራ ሁሉ አርቀን በበጎውም ሥራ ሁሉ አንድ አድርገን::

ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙንም የሰጠን ቡሩክ ነው:: ጸጋን ተቀበልን ደኅንነትንም በኢየሱስ ክርስቶስ በመስቀለ ኃይል አገኘን:: አቤቱ ከመንፈስቅዱስ የተገኘ ጸጋን ተቀብለን አንተን እናመሰግናለን::» /የሐዋርያት ቅዳሴ/ በማለት ነው::

ደግሞም በቅዳሴ ዲዮስቆሮስ ካህኑ ኅዳፌ ነፍስ ሲደግም እንዲህ ይማጸናል:: «በከመ ደመርከ ሥጋ ወልድከ ውስተ ሥጋ ዚአነ ወበከመ ቶሳሕከ ደመ መሚሕከ ውስተ ደመ ዚአነ ከማሁ ደምር ፈሪሆተከ ውስተ አልባቢነ ወሥነ አምልኮትከ ውስተ ሕሊናነ::» ትርጓሜው «የልጅህን ሥጋ ከእኛ ሥጋ ጋራ አንድ እንዳደረግህ ያንተን መሚሕ ደምም ከእኛ ደም ጋራ አንድ እንዳደረግህ እንዲሁ አንተን መፍራትን በልቡናችን በጎ አምልኮት ህንም በሕሊናችን ጨምር» ማለት ነው::

በተጨማሪም ዲያቆኑ በዜማ ሲማጸን «ነአኵቶ ለእግዚአ ብሔር ቅድሳቶ ነሢአነ ከመ ለሕይወተ ነፍስ ይኩነነ ፈውስ ዘተመጦነ ንስእል ወንትመሐፀን እንዘ ንሴብሖ ለእግዚአብሔር አምላክነ»:: እያለ በተሰዋው መሥዋዕት /በክርስቶስ ሥጋና ደም/ ይማጸናል፤ ያመሰግናል:: ትርጓሜውም እንዲህ ማለት ነው «ሥጋውን ደሙን ተቀብለን እግዚአብሔር እናመሰግነዋለን:: ለነፍሳችን አነዋወር መድኃኒት ይሆን ዘንድ የተቀበልን እኛ አምላካችን እግዚአብሔርን እያመሰገንን እንለምናለን አደራም እንላለን» /የሐዋርያት ቅዳሴ ቁ. 130/





ይህንን በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተገኘ ጸጋና ሥርዓት አስተውላችሁ ታውቃላችሁ? እውነት እላችኋለሁ ለዓለም ይቅርታና ድህነት በተሰጠበት በኢየሱስ ክርስቶስ ደም መማፀን ምንኛ ልዩ እድል ነው! ለዚህ የጠራን የሰማያት አምላክ ሥሙ የተመሰገነ ይሁን::

# ምዕራፍ አሥራአራት

## የቅዱስ ቁርባን ስጦታ

## በእኛ ላይ ያለው የፍቅሩ ማረጋገጫ ነው

«እናንተ ደካሞች ሸክም የከበዳችሁ ሁሉ ወደ እኔ ኑ እኔም አሳርፋችኋለሁ:: ቀንበሬን በላያችሁ ተሸከሙ... ለነፍሳችሁ እረፍት ታገኛላችሁ
ማቴ. 11፡28

እግዚአብሔር የቅዱስ ቁርባንን ሥርዓት የሠራልን ማለትም መድኃኒታችን ኢየሱስ በመስቀል ላይ ቅዱስ ሥጋውን ክቡር ደሙን የሠዋልን ለእኛ ካለው ጽኑ ፍቅር የተነሣ ነው:: «በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአብሔር አንድያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለሙን እንዲሁ ወዶአልና» /ዮሐ. 3፥16/ ስለዚህ ቅዱስ ቁርባንን ከልብ በመነጨ የቃሉ መሠረት ባለው በታላቅ መንፈሳዊ አክብሮት መቀበል ይገባል::

እራሱን ለቅዱስ ቁርባን የሚያዘጋጅ ክርስቲያን ክርስቶስ በእርሱ ላይ ያለውን ፍቅር በመረዳት ቸርነቱን በመደገፍ ሊሆን ይገባዋል:: «እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቸርነትና ጭከና ተመልከት ጭከናው በወደቁት ላይ ነው:: በቸርነቱ ግን ጸንተህ ብትኖር የእግዚአብሔር ቸርነት በአንተ ላይ ነው» /ሮሜ. 11፥22/ በተጨማሪም መንፈሳዊነት ጣዕምና ፍቅር የሞላባቸው ቃላቱ ወደ ቅዱስ ቁርባን ለመቅረብ ያነሳሱናል፣ ያዘጋጁናል:: በእርግጥ ቅዱስ ቁርባንን መቀበል ስናስብ በኃጢአት የቆሸሸችው ኅሊናችን ትወቅሰናለች:: የክፋቶቻችንና የኃጢአቶቻችን ብዛት ሊያሳፍሩን ይችላሉ:: በእርግጥም ያስፈሩናል:: ይሁና ግን እኛ ልናስበው የሚገባው የኃጢአተኞችን መሸፈኛ የሆነውን ለእኛ መዳን ያለውን





ፍቅርና «ሸክማችሁ የከበዳችሁ እናንት ደካሞች ሁሉ ወደ እኔ ኑ» /ማቴ. 11÷28/ የሚለው የምሕረት ጥሪውን ነው::

ነገር ግን ልብ ልንለው የሚገባው ወደዚህ ታላቅ ምሥጢር /ቅዱስ ቁርባን/ ስንቀርብ የፍቅሩ ጥሬ እንዳለ ሆኖ በጽኑ እምነት በመንፈሳዊነት በተስፋና በንጹሕ ፍቅር ተነሣስተን መሆን አለበት እንጂ በቀላል ምክንያት በከንቱ ምኞትና በሥጋዊ መሻት ያለ ምክረ ካህንና ያለንስሐ መሆን የለበትም:: እንዲህ ከሆነ ቅዱስ ቁርባን መንፈሳዊ ጸጋን ይሰጣል:: ነፍስ በኃጢአት ምክንያት ያጠፋችውን ኃይል ይመልስላታል:: በኃጢአት የተበላሸውን የነፍስ ደም ግባት ይመልሳል:: በእውነት የቅዱስ ቁርባን ምስጢር ታላቅ ነው:: ለነፍስ ብቻ ሳይሆን ለደካማ ሥጋም ኃይልና ብርታትን ቅድስናን ይሰጠዋል::

ይህንን ዘላለማዊ ክብርና ድህነት የምናገኝበትን የፍቅር ስጦታ /ቅዱስ ቁርባንን/ ለመቀበል በታላቅ የፍቅር ስሜትና በበቂ የንስሐ ዝግጅት መነሣሣት ሲገባን ቀዝቃዞችና ችላ ባዮች በመሆናችን እጅግ ልናዝንና ልናለቅስ ያለመታከትም ልንጸልይ ይገባናል:: ምክንያቱም ቅዱስ ቁርባን ቅድስናችንና መድኃኒታችን ነው:: የኃጢአተኞች መዳኛ የቅዱሳንም ዘላለማዊ ደስታ እርሱ ነውና::

በጥቂቱ የማይገመቱ ሰዎች ይህንን በሰማያት የሚያድሩትን ሁሉ ደስ የሚያሰኘውንና ዓለምን ሁሉ የሚጠብቀውን እና የሚያድነውን ምሥጢር አቃልለው ሲመለከቱትና ሰው ሠራሽ ሥርዓት አድርገው ሲገምቱ ከመፍረድ ይልቅ እጅጉን ልናዝንላቸው ይገባል:: በማወቅም ይሁን ባለማወቅ አመፃቸው በፍቅሩ ላይ ነውና ከዚህም የተነሣ ለሚያጡት ክብር ግምት መስጠት አይቻልም::

እስኪ ይህንን ነገር ልብ በሉት! ይህ የከበረ ምሥጢር የድህነት መገኛና የፍቅር ስጦታ በአንድ ቦታ ብቻ በአንድ ካህን ብቻ የሚሠዋ ቢሆንና ለሚሻውም ሁሉ ዋጋ የሚያስከፍል ቢሆን





ኖሮ ምን ያህል ሰዎች ወደዚያ ቦታና ካህን ሄደው ነገሩን ለማየትና የዋጋ ድርድር ለማድረግ ሲጨናነቁ እናገኛቸው ነበር?

ግን እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን አንድ ብትሆንም የጸጋውን ታላቅነት ለመግለጽና ለሚሹት ሁሉ ፍቅሩን ለማድረስ ቤተ ክርስቲያን ከሥርዓቷና ከሕጓ ለውጥ ነውጥ ሳይኖርባት በዓለም ዙሪያ ሁሉ እየተተከለች ቅዱስ ቁርባን በዓለም ሁሉ ላይ እንዲሠዋና ብዙ ካህናትም ተገኝተው አማናዊውን መሥዋዕት የክርስቶስን ሥጋና ደም በዓለም ዙሪያ እንዲሠውት አደረገ:: ለዚህም መሥዋዕት የሚጋበዙት ደካሞችና እንዲሁ ያለ ዋጋ ሊቀበሉ ለተዘጋጁ አማኞች ሆነ «ጥበብ ቤትዋን ሠራች ሰባቱንም ምሰሶዎችዋን አቆመች ፍሪዳዋን አረደች፣ የወይን ጠጅዋን ደባለቀች፣ ማዕድዋን አዘጋጀች፣ ባሪያዎችዋን ልካ በከተማይቱ ከፍተኛ ሥፍራ ላይ ጠራች፣ አላዋቂ የሆነ ወደዚህ ፈቀቅ ይበል አእምሮ የጐደላቸውንም እንዲህ አለች፤ ኑ እንጀራዬን ብዙ የደባለቅሁትንም የወይን ጠጅ ጠጡ:: አላዋቂነትን ትታችሁ በሕይወት ኑሩ፣ በማስተዋልም መንገድ ሂዱ::» /ምሣሌ 9÷1-5/

ስለዚህ ቅዱስ ቁርባንን የማይቀበል ሰው ከሕይወት ይሸሻል:: ራሱንም ከኃጢአት ሳያነፃ በማይገባ ሁኔታ ከቆረበ ደግሞ አምላኩን መበደል ይሆንበታል:: ይህ እንዳይሆን ተግቶ መጸለይ በምክረ ካህን መምራትና የክርስቶስ መንግሥት ወንጌል ራስን ማስገዛት ይገባል:: በተጨማሪም ቅዱስ ቁርባን ከመቀበል በፊት ኅሊናን መመርመርና በንጽሕና መዘጋጀት ተገቢ ነው:: ልብ በል/ በአጠቃላይ ስለ ኃጢአቶችህ ሁሉና ስለ ሠራኸው በደል ማዘን ይገባሃል:: በተለይም በየዕለቱ በምታደርጋቸው ኃጢአቶች በሚገባ መጸጸትና ማልቀስ በካህኑም ፊት መናዘዝ ይገባሃል:: ቢቻልህ ሁል ጊዜ በልብህ ውስጥ ያለውን ክፉ ምኞትና ፍላጐት እንዲሁም ደካማነትህን በሙሉ ለአምላክህ ግለጽለት በቅዱስ ቁርባንም ተወስነህ ስትኖር በበቂና በከባድ ምክንያት ካልሆነ በቀር ቅዱስ ቁርባንን መተው አይገባም:: ያም ሆኖ ቶሎ የሚስተካከልበትን





ሁኔታ ከንስሐ አባትህና ከጸሎት ጋር ፈልገህ እንቅፋቱን ከሕይወትህ አርቅ:: እንዲህ ብታደርግና እስከ መጨረሻው ታምነህ ብትገኝ የሕይወትን አክሊል እሰጥሀለሁ ይልሃል::

## በሥጋ ወደሙ ተወስነው ስሚኖሩ

«እስከ መጨረሻ የሚጸና እርሱ ይድናል» ማቴ 24

የክርስትና ሕይወት ግብ እስከ መጨረሻ ታምኖ መገኘት ነው:: እስከ መጨረሻ ታምኖ ለመገኘት ደግሞ አይነት የማይገኝለት ጽናት ነው:: ጌታችን ለደቀ መዛሙርቱ የነገራቸው ይህንኑ ነው:: ክህነትን ለሚያህል ሥልጣን ወንጌልን ለሚያህል አገልግሎት ጠርቶ ወደ ዓለም ሲልካቸው የሚጠብቃቸው ለእግራቸው የአበባ ምንጣፍ ለአንገታቸው የአበባ ጉንጉን ሳይሆን ለሰውነታቸው እሳት ለአንገታቸው ስለት ነውና በሚገጥማቸው በማናቸውም መከራ የተሰጣቸውን እንዳይጥሉ እስከ መጨረሻው የሚታገስ እርሱ ይድናል ብሏቸዋል

አንተም ልብ ልትለው የሚገባህ ዓለሙን ያሸነፈው ጌታህ ካንተ ጋር መሆኑን ነው በብዙ ተጋድሎ በእግዚአብሔር ፍቅርና ቸርነት በቅተህ በሥጋ ወደሙ መወሰንህን በየትኛውም ጊዜና ቦታ አትዘንጋው የራስህም አክሊል እንዳይወድቅ ተጠንቀቅ::

ቀሪ እድሜህ በጽናት እንዲፈጸም በዚህች ምድር ላይ የቀረህና የሚያጓጓህ ነገር እንደሌለ እራስህን አሳምን እርሱ ካንተጋር ነውና ሁሉ ካንተ ስለመሆኑ አትጠራጠር:: ሰርቶ ለማግኘት፣ ነግዶ ለማትረፍ፣አርሶና ዘረቶ ለማምረት፣ ተምሮ ለማወቅ፣ አጭቶ ለማግባት፣ አግብቶ ለመውለድ፣ ወልዶ ለማሳደግ፣ አሳድጎ ለመዳር፣ የማትከለከልና እንዲያውም እነኚህን ቀንበሮች ብቻህን እንዳትሸከም ኑሮህን ሁሉ በበረከት እንዲያልፍ አምላክህ ካንተ ጋር መሆኑን በማሰብ ትምክህትህ በእግዚአብሔር ላይ ሆኖ ህጉንና ሥርዓቱን ጠብቆ በዚህ ሁሉ አምላክህ ራስ እንጂ

ጅራት አያደርግህም /ዘሌ. 26፥3/ የሰማያት በረከትም ሁሉ በቤትህ በልጆችህና በንብረትህ ላይ ይሆናል።

የዲያቢሎስ ውጊያ በንቃት ትከታተለው ዘንድ የእግዚአብሔር ቃል የሚመክረውን ምክር ሁሉ ተጠቀምበት የሚገጥምህን ፈተና ቸል አትበል ሁል ጊዜ ከንስህ አባትህ ጋር መነጋገር አትተው የሚገጥምህን ሁሉ ለቤተክርስቲያን ንግራት /ማቴ. 18፡17/ ከዚህ ከበቃህበት ክብር በኋላ ከዚህ ክብር ሊያስወጣህ የሚችል ለሕይወትህ ተቃራኒ የሆኑ ልዩ ቦታና ልዩ ተግባር በፊትህ የተረገጠ እንዲሆን ሁል ጊዜ ጌታ እንዳለው ጸልይ «ወደ ፈተና እንዳትገቡ ተግታችሁ ጸልዩ» /ሉቃ. 22-40፥46/

በዚህ መጽሐፍና በሌሎች የቤተክርስቲያናችን መጽሐፎች ቅዱስ ቁርባንን ከመቀበል በኋላ የሚደረግ መንፈሳዊ ጥንቃቄዎች የሚለውን ሁል ጊዜ አስተውላቸው።

## በሥጋ ወደሙ ለመወሰን ስተነሳሱ

«የመዳን ቀን አሁን ነው» /2ቆሮ. 6፡2/

በሥጋ ወደሙ ለመወሰን የተነሳሳን መነሳሳታችን ወደ ዝግጅት እንዲደርስ ዝግጅታችን ፍሬ እንዲያፈራ የሐዋርያት ቃል ልብ ልንል ይገባል የመዳናችን ቀን ዛሬ መሆኑን።

ማንኛውም ክርስቲያን በውስጡ ያደረው ቅዱስ ቁርባንን የመቀበል ፍላጐት የመንፈስ ቅዱስ ፍሬ ሊሆን ይገባል ለዚህም ደግሞ ለምን መቀበል ፈለግሁ ስለምቀበለው ምን ያህል ተረድ ቻለሁ ከተቀበልኩ በኋላ የሚጠብቀኝ ሕይወት ምን ይመስላል የሚሉትንና መሰል ጥያቄዎችን የመመለስ ብቃት እንዲኖረው ወደ በቂ ዝግጅት ራሱን ማድረስ ይኖርበታል ይህ ደግሞ የጸና አቋም እንዲይዝ ያደርገዋል።

ቅዱስ ጴጥሮስ እንዲህ አለ «ጌታ ሆይ ወደ ማን እንሄዳለን» /ዮሐ. 6፡68/ ይህንን አቋሙን የገለጠው ከክርስቶስ የሚገኘውን ዘላለማዊ ድህነት ላለማጣት ነው ተከትሎም እንዲህ በማለት





የተናገረው ቃል ያረጋጋጥልናል «አንተ የዘላለም ሕይወት ቃል አለህ» /ዮሐ. 6፥68/ ብዙዎች ግን «ሥጋዬ እውነተኛ መብል ደሜ እውነተኛ መጠጥ ነው» የሚለውን የሕይወት ቃል ሸሹ ይህ ሰው ሥጋውን እንበላ ዘንድ ደሙን እንጠጣ ዘንድ እንዴት ሊሰጠን ይችላል የሰው ሥጋ ቢበሉት የሰው ደም ቢጠጡት ደዌ እንጂ እንዴት ሕይወተ ሥጋ ወነፍስ ይሆናል እያሉ በእነርሱም ላይ የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ተጽፏል «ከዚህም የተነሣ ከተከተሉት ብዙዎች ወደ ኋላ ተመለሱ ወደ ፊትም ከእርሱ ጋር አልሄዱም።» /ዮሐ. 6፥66/

እንደዚሁ አንተም ወደ ኋላ እንዳትመለስ ለሥጋ ወደሙ ያለህ መነሳሳት በምኞት ብቻ አይቀር መነሳሳትህ ከሥጋና ከደም ሃሳብ የተነሳ አይሁን ራስህን ለቃሉ ከማቅረብህ ከማስገዛትህ እና ከምክረ ካህን የተነሳ ይሁን።

ወደ ቅዱስ ቁርባን ብትቀርብ እንዲህና እንዲያ ትሆናለህ እያለ ከጆሮህ ሥር ለሚያንሾካሹክ ሰይጣን እድል ፈንታ አትስጠው ሰዎችንም ተጠቅሞ የሚያደርገውን ጉትጐታ ቸል በለው ይልቁንም በጸና እምነት ለቅዱስ ቁርባን ዝግጅት ራስህን እያነሳሳህ «አንተ ሰይጣን ከኋላዬ ሂድ በል» በለው።

## ከሥጋ ወደሙ ስርቀው ለሚኖሩ

«ለቤተክርስቲያን ንገራት» /ማቴ. 18፥17/

ማንኛውም ክርስቲያን ስለ ቅዱስ ቁርባን ቢረዳ ከቅዱስ ቁርባን አይሸሽም። አንድን ሰው ለምን ሥጋ ወደሙ አትቀበልም? ብንለው መልሱ ጠልቼው መሰለህ ይህ ይስተካከልልኝ እንዲህና እንዲያ ያለ ችግር ስላለብኝ እንጂ ይላችኋል የእግዚአብሔር ቃል ለዚህ መልስ አለው መልሱም ይህ ነው። «ለቤተ ክርስቲያን ንገራት» /ማቴ. 18፥17/





በዚህች በያዝናት ዓለም ላይ ያለ ችግር ለማለፍ የሚያስብ ሰዎች ሁሉ ልዩ በሆነ የዲያቢሎስ ፈተና ላይ ወድቀዋል ምክንያቱም ይህ አሳባቸው ከአሳብ በላይ አይዘልም እንዲያውም ክርስቲያኖች በዓለሙ ዘንድ እንደአምላካቸው ተጠልተው ተንቀውና ተሰድበው መኖራቸውን መዘንጋት የለባቸውም ቃሉ እንዲል «ዓለም ቢጠላችሁ ከእናንተ በፊት እኔን እንደ ጠላኝ እወቁ ከዓለምስ ብትሆኑ ዓለም የራሱ የሆነውን ይወድ ነበር ነገር ግን እኔ ከዓለም መረጥኋችሁ እንጂ ከዓለም ስለ አይደላችሁ ስለዚህ ዓለም ይጠላችኋል» ዮሐ. 15፥18/

ስለዚህ ማናቸውንም ችግራችንን ወደ እግዚአብሔር ላለማቅረብ ምክንያት የምናደርግ ከሆነ ስህተታችን እጅግ ከሚባለው በላይ ነው። በእርግጥ ሕይወታችን የተዘበራረቀና ለእግዚአብሔር መቅረብ የማይገባው መስሎ ሊሰማን ለቤተክርስቲያን ልንነግራት በትምህርቷና በምክሯ ራሳችንን ከችግር ልናላቅቅ ይገባናል እንጂ በመሸሽ መኖራችን እግዚአብሔርን ከመፍራታችን የተነሳ የመነጨ አይደለም።

ማንም ሰው ወደ እግዚአብሔር ሊቀርብና የዕለት ተዕለት ሕይወቱ እግዚአብሔርን በማምለክና በማስደሰት ላይ የተወሰነ እንዲሆን የሚያደርገው ቃሉ የገባውን ያህል ነው እንደዚሁ ቅዱስ ቁርባንን በመቀበል ለክብር የመዘጋጀቱ ሃሳብ በክርስቲያኑ ውስጥ ሊጸነስ የሚችለው የታመነውን ያህል ነው።

አምላክህ ታደርገው ዘንድ ያዘዘህንና ትልቁን የድህነትህን ጉዳይ እስከ መቼ እርቀህና ስለ እርሱ ሳታስብ ትኖራለህ፡ይልቁንስ የራቀህን ሁሉ መቋቋም ያልቻልከው ብቻህን ከመሆንህ የተነሳ እንደሆነ አውቀህ ወደ አምላክህ ቅረብ «ያለ እኔ ምንም ልታደርጉ አትችሉምና» /ዮሐ. 15፡5/ ይልቁንስ በጊዜያዊነት በእንግድነት የምትኖርበት የዚህች ዓለም ኑሮ ሳይፈጸም ሥጋህ ወደ አፈር ነፍስህም ወደ ሰጣት ወደ እግዚአብሔር ሳትመለስ የዚህ ኪዳን ባለቤት ሁን «የሰው ልጅ ሥጋ ካልበላችሁ ደሙንም





ካልጠጣችሁ በራሳችሁ ሕይወት የላችሁም ሥጋዬን የሚበላ ደሜን የሚጠጣ የዘላለም ሕይወት አለው እኔም በመጨረሻው ቀን አስነሳዋለሁ።» /ዮሐ. 6፥53/ /መክብብ 12፥7/

## ቅዱስ ቁርባን የምንቀበልባቸው ሰዓታት

ማንኛውም ክርስቲያን እራሱን በበቂ ዝግጅት ባዘጋጀባቸው እራሱን ለካህን ባሳየባቸውና ምክረ ካህን ባገኘባቸው ጊዜያት ወደ ቅዱስ ቁርባን መቅረብ ይችላል /ሉቃ. 5፥14/

እንግዲህ ሳለ ቅዱስ ቁርባን በሚገባ ከተረዳን ከተቻለ በየሳምንቱ እሑድና በታላላቅ በዓላት መቁረብ ይገባል።

ይህ ካልተቻለም በየአርባ ቀኑ ሥጋውን ደሙን መቀበል ተገቢ ነው። በተለይም በልደት፣ በጥምቀት፣ በጸሎተ ሐሙስ፣ በበዓለ ትንሣኤና፣ በዘመነ ትንሣኤ በደብረ ታቦር በሌሎችም ቅዱሳን እና መላእክት በዓላት ሥጋውን ደሙን /ቅዱስ ቁርባን/ መቀበል ተገቢ ነው።

## ቅዱስ ቁርባንን ከመቀበል በፊት የሚጸለይ የእምነት ቃል

አምናለሁ አምናለሁ አምናለሁ እስከ መጨረሻይቱ እስትንፋስ እታመናለሁ። በሁለት ወገን ድንግል ከምትሆን ከሁላችን እመቤት ከቅድስት ድንግል ማርያም የነሳው የጌታችንና የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው ደሙ ይህ እንደሆነ ያለ መቀላቀልና ያለመጨመር ያለመለወጥና ያለመለየት ከመለኮቱ ጋር አንድ ያደረገው በጴንጤናዊ ጲላጦስ ዘመን ባማረ ምስክርነት ምስክር የሆነ ስለ እኛና ስለ ሁላችንም ሕይወት አሳልፎ የሰጠው።

አሜን

ገ
ፅ
3
5



አምናለሁ አምናለሁ አምናለሁ መለኮቱ ከሰውነቱ እንደ ዓይን ቅጽበት ያህል እንኳን እንዳልተለየ እታመናለሁ ማስተሥሪያ ሊሆን አምነው ለሚቀበሉ ሁሉ አሳልፎ ሰጠው እንጂ::

አሜን

አምናለሁ አምናለሁ አምናለሁ የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋው ደሙ ይህ እንደሆነ እታመናለሁ:: ክብርና ምስጋና ስግደትም ቸር ከሚሆን ከሰማያዊ አባቱ ጋር ማሕየዊ ከሚሆን ከመንፈስ ቅዱስ ጋር የሚገባው ይህ ነው:: ዛሬም ዘወትርም ለዘላለሙ::

አሜን

/የሐዋርያት ቅዳሴ ቁ. 101-103/

ወስብሐት ለእግዚአብሔር

አዘጋጅና አሳታሚ
ዲ/ን የሺጥላ ሞገስ ኪዳኔ
አዲስ አበባ





## ዋቢ መጻሕፍት

1. ወንጌል ቅዱስ ንባብና ትርጓሜው /1916 ዓ.ም./
2. ሰማንያ አሐዱ መጽሐፍ ቅዱስ /አማርኛ/ /1980 ዓ.ም./
3. መልዕክታተ ጳውሎስ /አንድምታ/ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት /1989 ዓ.ም./
4. መዝሙረ ዳዊት /አንድምታ/ ተስፋ ገብረሥላሴ ማተሚያ ቤት /1989/
5. መጽሐፈ ቅዳሴ /አንድምታ/ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት /1988 ዓ.ም./
6. አስራ አራቱ መጽሐፈ ቅዳሴ
7. ትምህርተ መለኮት ከአሥራት ገብረማርያም /1991/ ዓ.ም.
8. የመጽሐፍ ቅዱስ መዝገበ ቃላት /1992 ዓ.ም./ አዲስ አበባ
9. ስምዐ ጽድቅ ጋዜጣ በተለያዩ ወራት የወጡ /ማኅበረ ቅዱሳን/
10. ምሥጢሬን ላካፍላችሁ /1፣2/ /በማኅበረ ቅዱሳን/
11. ዲያብሎስና ውጊያዎቹ በቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ትርጉም አያሌ ዘኢየሱስ /1995 ዓ.ም./
12. ትምህርተ ሃይማኖት ኦርቶዶክሳዊት ከአባ ገብርኤል ሊቀ ጳጳስ /1991 ዓ.ም./
13. የእምነት ሕይወት በቅዱስነታቸው አቡነ ሺኖዳ ትርጉም ወንድወሰን ሶርሳ /1995 ዓ.ም./
14. ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን /በሊቀ ካህናት ክንፈገብርኤል አልታዬ/